# « ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ »



የግሸን ደብረ ከርቤ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን

- ✠ ፲፱፻፺፰ ሊታወጉት በኢትዮ
- ✠ ለተመረጡ ኢጲስ ቆጶሳት ሥርዓተ ሢመት ተፈጸመ
- ✠ ድንግል ማርያም በምድረ ግብፅ
- ✠ በገዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ጠበል ፲፯ ኢአማንያን በክርስትና እምነት ተጠመቁ፤ ፲፱ መናፍቃን ተመለሱ፤

ቊጥር ፹፪ ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም
አዲስ አበባ


## የ፲፱፻፺፰ ዓ.ም አጽዋማትና በዓላት

### ዘመነ ማርቆስ ወንጌላዊ

ዓመተ ዓለም ፯ሺህ ፭፻፺፰
ዓመተ ምሕረት ፩ሺህ ፱፻፺፰

አጽዋማትና በዓላት

| | |
|---|---|
| አበቅቴ | ፩ |
| መጥቅዕ | ፳፱ |
| የዕለት ተውሳክ | ፮ |
| ጾመ ነቢያት ኅዳር | ፲፭ |
| ጾመ ነነዌ የካቲት | ፲ |
| ዐቢይ ጾም የካቲት | ፳ |
| ደብረ ዘይት መጋቢት | ፲፯ |
| ሆሣዕና ሚያዝያ | ፰ |
| ስቅለት ሚያዝያ | ፲፫ |
| ትንሣኤ ሚያዝያ | ፲፭ |
| ርክበ ካህናት ግንቦት | ፱ |
| ዕርገት ግንቦት | ፳፬ |
| ጰራቅሊጦስ ሰኔ | ፬ |
| ጾመ ሐዋርያት ሰኔ | ፭ |
| ጾመ ድኅነት ሰኔ | ፯ |
| ጾመ ፍልሰታ | ፩ |



### የሕዝብ በዓላት

- መስከረም ፩ ቀን እሑድ
- ርእሰ ዐውደ ዓመትና የዘመን መለወጫ በዓል
- መስከረም ፲፯ የመስቀል በዓል
- ታኅሣሥ ፳፱ የልደት በዓል
- ጥር ፲፩ የጥምቀት በዓል
- የካቲት ፳፫ የዓድዋ ድል መታሰቢያ
- ሚያዝያ ፲፫ ስቅለት
- ሚያዝያ ፲፭ ትንሣኤ
- ሚያዝያ ፳፫ ሜይዴይ
- ሚያዝያ ፳፯ የአርበኞች (የድል በዓል)
- ግንቦት ፳ ኢሕአዴግ አዲስ አበባ የገባበት



www.ethiopianorthodox.org

# ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ

ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት፣ ታሪክና ባህል፣ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ዜና ለሕዝበ ክርስቲያን የሚያቀርብ ስለሆነ «ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ» ተብሎ ተሰይሟል።

## [ማውጫ]


❖ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ያስተላለፉት ቃለ ምእዳን ............ ፫

❖ ርእሰ አንቀጽ ............ ፬

❖ ስተረመጡ ኤጲስ ቆጶሳት ሥርዓተ ሢመት ተፈጸመ ............ ፮

❖ ፲፱፻፺፰ ሊቃውንት በኒቅያ ............ ፱

❖ መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም በደመራ በዓል ላይ በመስቀል አደባባይ ስለፈተጸመው አሳዛኝ ድርጊት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ ............ ፲፪

❖ ግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ............ ፲፫

❖ ጸድቁ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ ............ ፲፬

❖ ዘመነ ማርቆስ ............ ፲፮

❖ ድንግል ማርያም በምድረ ግብፅ ............ ፲፰

❖ አቡነ አረጋዊ ............ ፲፱

❖ ክረምት እንዴት አለፈ? ............ ፳፩

❖ በገዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ጠበል ፲፮ ኢ-አማኒያን በክርስትና እምነት ተጠመቁ ፲፱ መናፍቃን ተመለሱ ............ ፳፬

❖ «የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው» ............ ፳፱

❖ ሸር ሜዳ የፈውስ ሜዳ ............ ፴፩

❖ ቅዱሳን መላእክት ............ ፴፮



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መመሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍሉ እየተዘጋጀ በየወሩ አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ።



ዋና አዘጋጅ፡-

ሊቀ ልሳናት ነቅዐ ጥበብ ወንድም

ም/አዘጋጅ፡- መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

☎ 57 81 66፡ ✉ 1283

አዲስ አበባ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም




ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት


www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ በ፲፱፻፺፰ ዓ.ም የዘመን መለወጫ ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን



በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

- በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ በገጠርና በከተማ፣
- ከሀገራችንም ውጭ በተለያዩ አህጉር የምትኖሩ፣
- እንደዚሁም የሀገርን ዳር ድንበር ለመጠበቅና ለማስከበር በየጠረፉ ያላችሁ፣
- በሕመም ቁራኛ፣ በደዌ ዳኛ ተይዛችሁ በየሆስፒታሉ የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት በሙሉ፤

የዘመናት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ስምንት ዓመተ ምሕረት በሰላም አሸጋገራችሁ!!

## ‹‹ባርክ እግዚኦ ዐውደ ዓመት በኂሩትከ››

አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ዐውደ ዓመቱን በቸርነትህ ባርክልን (ቅዱስ ያሬድ)

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ባለፈው ዓመት ስላደረገልን ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባል፤ በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ በአዲስ መንፈስ አዲስ ሥራ ለመሥራት እንድንችል ያረዳን ዘንድ ጸሎት ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡

ትናንት ያለፈው ዓመት ምን ሥራ እንደ ተሠራበት ምን ዐይነት ታሪክ እንደ ተመዘገበበት እናውቃለን፡፡ ዛሬ የሚጀምረው ዓመት ግን ምንም ዓይነት ሥራ ያልተሠራበት አዲስ ነው፡፡

ስለሆነም ዛሬ በአዲስነት በተቀበልነው ዓመት ሀገርንና ወገንን የሚጎዳ ሥራ እንዳንሠራበት፣ በተተኪው ትውልድ ዘንድም የሚያስወቅስ ታሪክ እንዳናስመዘግብበት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ አዲስ ዓመትን መመኘት ብቻ የሕይወት ዋስትና አይሆንም፡፡ በአዲስ ሕይወት ለመኖር አዲስ ሥራ ለመሥራት መመኘትና ምኞትን በተግባር መፈጸም ያስፈልጋል፡፡

የዘመን መለወጥ ቍጥር መጨመር ካልሆነ በቀር በየዓመቱ ያው ነው፡፡ ዘመን በተሰወጠ ቁጥር ሰውና ሌላው ነገር ሁሉ ያረጃል እንጂ ዘመን አያረጅም፡፡ ዘመኑ አዲስ የሚሆነው በአዲስ መንፈስ አዲስ ሥራ ሲሠራበት ብቻ ነው፡፡

## የተወደዳችሁ የመንፈስ ልጆቼና ወገኖቼ!

አዲሱ ዓመት የበረከትና የደስታ፣ የፍቅርና የሰላም፣ የጤናና የብልፅግና፣ በጎ ነገርን ሁሉ የተሞላ ዓመት እንዲሆንልን የሰላም ሰዎች መሆን ይኖርብናል፡፡ ሁሉም ኅብረተ ሰብእ ስለ ሰላም ካሰበ፣ ከተናገረና ከሠራ ዘመኑ የሰላም ዘመን ይሆናል፡፡

‹‹መልካም ዘመንን ለማየት የሚወድ ... ሰላምን ይፈልግ›› ተብሎ እንደ ተነገረ ሰላምን ለማስፈን ከሁላችንም ሰላማዊ የሆነ የመንፈስ አንድነት ይጠበቃል፡፡

በሀገራችን ውስጥ የተለያየ እምነት ያላቸው ማኅበረሰቦች ሁሉ ስለ ሰላም አንድ ልብና አንድ ቃል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ሰላምን በተመለከተ የሃይማኖት ልዩነት ሊኖር እንደማይችል ሁሉም ያውቃል፡፡ ስለዚህ የሀገርን ሰላም በተመለከተ የሚጠየቀው ጉዳይ ማንኛውም ኅብረተሰብእ መተባበር ይኖርበታል፡፡

ስለ ሰላም ያለን ምኞትም ወደ ፍጻሜ ሊደርስ የሚችለው በሰላም ሆነን እግዚአብሔርን ስንለምን ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ሰላምም ነው፤ ሰውም ፍቅርና ሰላምን አጽንቶ መያዝ አለበት፡፡

በዘመናችን በኤች አይ ቪ ኤድስ ምክንያት ኅብረተሰብእ ይልቁንም እምራቹ ዜጋ እየተጎዳ መሆኑ ዘወትር ይነገራል፡፡ ነገር ግን የኅብረተሰባችን ችግር ይህ ብቻ አይደለም፤ በልዩ ልዩ የተፈጥሮ ችግሮችና ጎጂ ባህል ኅብረተሰቡ እየተጎዳ ነው፡፡ በጎጂ ባህልና ልማድ ጉዳት የሚደርስባቸው በተለይ ሕፃናትና እናቶች ናቸው፡፡

ኤች አይ ቪ ኤድስን በተመለከተ እስካሁን ድረስ በተደረገው እንቅስቃሴ መጠነኛ ውጤት መታየቱ እየተነገረ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መንግሥትም ሆነ ሌሎች ድርጅቶች፣ ግለሰቦች ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስና ስለ ጎጂ ባህሎች ኅብረተሰቡ እስካሁን ካሳየው የጠባይ ለውጥ የበለጠ እስከሚያሳይ ድረስ ተስፋ ባለመቁረጥ ዛሬም ነገም ምክርና ትምህርት መስጠት ይጠበቅብናል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ይህን ችግር በተመለከተ እስካሁን ተገቢውን ትምህርት በመስጠት ላይ ትገኛለች፡፡ ዛሬም በአዲሱ ዓመት ይህን መልእክት ስናስተላልፍ ኅብረተሰቡ የሚተላለፈውን መልእክት ተቀብሎ ተግባራዊ እንዲያደርገው መልእክታችንን በአጽንኦት እናስተላልፋለን፡፡

- እግዚአብሔር አምላካችን ዐውደ ዓመቱን በቸርነቱ ይባርክልን፤
- አዲሱን ዘመን የሰላም፣ የደስታና የጤና ዘመን ያድርግልን፤
- ለሀገራችንና ለመላው ዓለም ሰላሙን ይስጥልን፤
- ሕዝባችንን በፍቅር፣ በአንድነትና በስምምነት ያጽናልን፤
- እግዚአብሔር አምላክ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ይባርክ ይቀድስ አሜን፡፡

መልካም አዲስ ዓመት ያድርግልን!

አባ ጳውሎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
ጳጉሜን ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ‹‹እግዚአብሔር የፈቀደውን ሁሉ አደረገ››

በክርስትና እምነት ትምህርት ማንኛውም ሥልጣን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና ምርጫ እንደማይፈጸም ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ፤ ልበ ንጹሐን መምህራንም ምሥጢሩን ከነታሪኩ አጉልተውና አስፍተው በየጊዜው ያስተምራሉ።

በብሉይ ኪዳን ነቢያትና ደቂቀ ነቢያት በእግዚአብሔር ፈቃድ ተጠርተው ኃላፊያቱንና መጻእያቱን ተንብየዋል፤ በሐዲስ ኪዳንም ቅዱሳን ሐዋርያት አልጫውን ዓለም በትምህርታቸው እንዲያጣፍጡ ከተለያዩ የሥራ ቦታዎች ለሐዋርያዊ አገልግሎት ተመርጠው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕላዌና ሰቤዘ ዓለም መምጣቱን ለመመስከር በቅተዋል።

በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው፤ በትንቢተ ነቢያት የታወቀችው፤ በትምህርተ ሐዋርያት የታነጸችው፤ በደመ ሰማዕታት የጸናችው ጥንታዊት፤ ሐዋርያዊትና ብሔራዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እምነቷን፣ ትምህርቷን፣ ሥርዓቷንና ትውፊቷን ሳታፋልስ እንድትጓዝ ለማድረግ ‹‹መከሩ ብዙ ነው ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው፤ ሠራተኛ እንዲጨምር የመከሩን ባለቤት ጠይቁት›› የሚለውን አምላካዊ ቃል በሥራ በመተርጐም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ መንበርነት የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ከሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ፴፪ አበው ቆሞሳት አወዳድሮ በተገኘው የድምፅ ብልጫ ፲፯ ኤጲስ ቆጶሳትን መርጦ ሥርዓተ ሢመቱ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተከናውኗል። እስከአሁን ድረስም በቅዱስነታቸው አንብሮ እድ የተሾሙት ጳጳሳት ፺፬ መሆናቸውም ታውቋል።

ቅዱስ ፓትርያርኩ የኤጲስ ቆጶሳቱን ምርጫ ወቅታዊነትና አስፈላጊነት ሲገልጹ ‹‹እግዚአብሔር የፈቀደውን በጊዜው የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት አለብን፤ በዚህ ምርጫ በእጩነት የቀረቡትና የተጠቆሙት ሊቃውንት መነኮሳት ብዙዎች ናቸው፤ የሁሉንም የግል ማኅደር በጥልቀት መርምረንና በስፋት ተወያይተን በእግዚአብሔር ፈቃድ መርጠናል ... የተመረጡት ኤጲስ ቆጶሳት ሕዝቡን ለማገልገል ስለሆነ ሁሉንም በእኩልነት እያዩ ሊሠሩ እንደሚገባቸው ከአስገነዘቡ በኋላ የእምነት ተከታዮች ቍጥር ከ፵ ሚሊዮን በላይ በመሆኑ አሁን የተመረጡት ኤጲስ ቆጶሳትን ጨምሮ ለሁሉም ይበቃሉ ማለት ሳይሆን በቀጣይ ተጨማሪ ኤጲስ ቆጶሳት እንደሚያስፈልጉ በአባታዊ መመሪያቸው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥና በውጭ አህጉራት የምትፈጽመው መንፈሳዊ አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን የአባቶች ጳጳሳት መመረጥ ለእምነት ተከታዮቿ ጥያቄ እንደሚመልስ ግልጽ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ረዓይኬ አባግዕየ›› የሚለውን ቃል በማስተማሩ ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ የሐዋርያትን ትምህርት በመቅሰም ‹‹ሜመክሙ እግዚአብሔር ጳጳሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ ከመትርዓዩ ቤተ ክርስቲያኖ እንተ አጥረያ በደሙ፤ እግዚአብሔር አምላክ በደሙ የዋጃት ቤተ ክርስቲያኑን እንዲጠብቁ ጳጳሳትን ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾማቸው›› ሲል በዝማሬ ድርሰቱ ገልጾታል።

ስለዚህ ሁሉም የአንድነት ቤቱን ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ትውልዱን ከባዕድ እምነትና የጥፋት ተግባራት ለማዳን የራስን አጥፍቶ የሌላ ተበዳሪ እንዳይሆን ሰመከላከል የነበረት አገልግሎት የሚፈጸምበት ወቅቱ አሁን ስለሆነ ጥሪውን ምእመናን ሁሉ ተቀብለው ለሥራ እንዲሠለፉበት ያስፈልጋል።፨



# ለተመረጡ ኤጲስ ቆጶሳት ሥርዓተ ሢመት ተፈጸመ

በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የተመረጡ የ፲፯ ኤጲስ ቆጶሳት ሢመተ ጵጵስና ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በቅዱስ ፓትርያርኩ አንብሮተ እድ ተፈጸመ። ከበዓለ ሢመቱ ዕለት አስቀድሞ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ከቀኑ ፱ ሰዓት ጀምሮ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና ሥርዓተ አስኬማ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም አዲስ ለተሾሙት ኤጲስ ቆጶሳት ተፈጽሟል።

ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ከጥዋቱ ፲፪:፲፭ ሰዓት ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፤ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፤ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መሪነትና በብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ተራዳኢነት የቅዳሴ ሥርዓቱ ተከናውኗል። ከዚያም የተሿሚ ኤጲስ ቆጶሳት ሥርዓተ ጸሎት በቅደም ተከተል የተፈጸመ ሲሆን በሥርዓተ ጸሎቱ ወቅትም የተሿሚ ኤጲስ ቆጶሳቱ ስምና ሀገረ ስብከት በቅዱስነታቸው ቃለ በረከት ተገልጿል። የሥርዓተ ሢመቱ ጸሎትም ሲያበቃ ምስባከ ተሰብኮ ወንጌል ከተነበበ በኋላ በቅዱስነታቸው የሚመራው የቅዳሴ ጸሎት ቀጥሎ በዓሉን በማስመልከት ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በመጣው መርሐ ግብር ሰዓቱን ጠብቆ ተከናውኗል።

በመርሐ ግብሩ ቅደም ተከተል መሠረት ከጠዋቱ ፫ ሰዓት ቅዱስነታቸው ከብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትና ከተሿሚ ኤጲስ ቆጶሳት ጋር በመሆን በዓውደ ምሕረቱ ተገኝተዋል። በመቀጠልም ክቡር ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በበዓሉ ሥፍራ ሲደርሱ ቅዱስነታቸው አቀባበል አድርገውላቸዋል። ፕሬዝዳንቱ በዓውደ ምሕረቱ ላይ በመገኘት ለበዓሉ የተዘጋጀውን ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ዝግጅቶች ተከታትለዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በበዓሉ ላይ ባስሙት ቃል ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በዚህ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ ሆነው ያደጉባትንና ሲያገለግሏት የኖረችውን ቤተ ክርስቲያን ለማገልገል በቁርጠኝነት ሲንቀሳቀሱና በዐበይት በዓላቶቻችን ላይ ሁሉ እየተገኙ በክብር ላይ ክብር ስለጨመሩልን እግዚአብሔርን እመሰግነዋለሁ ካሉ በኋላ የኤጲስ ቆጶሳቱን ምርጫ ወቅታዊነትና አስፈላጊነት ሲገልጹ፤ እግዚአብሔር የፈቀደውን በጊዜው የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት አለብን፤ በመሆኑም በዚህ ምርጫ በእጩነት የተጠቆሙት ሊቃውንቶችና መነኮሳቶች ብዙ ናቸው ያሉት ቅዱስነታቸው የሁሉንም ፋይል መርምረንና በስፋት ተወያይተን በእግዚአብሔር ፈቃድ እነዚህን መርጠናል ብለዋል።

በመጨረሻም እነዚህ ኤጲስ ቆጶሳት የተመረጡት ሕዝቡን ለማገልገል ስለሆነ ማንንም ሳይለዩ ወገንን ሳይመርጡ ሊሠሩ እንደሚገባቸው የጠቆሙት ቅዱስ ፓትርያርኩ ተመራጭ ኤጲስ ቆጶሳቱ የተመረጡት በሕዝቡ ጠያቂነትና በቋንቋው ባለቤትነት ስለሆነ በሚሄዱበት ሁሉ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅባቸዋል ካሉ በኋላ የምእመናኖቻችን ቍጥር ከ፵ ሚሊዮን በላይ በመሆኑ አሁን የተመረጡትን ኤጲስ ቆጶሳትን ጨምሮ እንድ ኤጲስ ቆጶስ ለ፫ና ለ፬ ሚሊዮን ሕዝብ ስለማይሆን በቀጣይ ተጨማሪ ኤጲስ ቆጶሳት እንደሚያስፈልጉ ጨምረው ገልጸዋል።

ከቅዱስነታቸው ንግግር ቀደም ሲል ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በዓሉን በማስመልከት ባደረጉት ንግግር የኢትዮጵያ መንግሥት ከሃይማኖት ገለልተኛ መሆኑን ገልጸው እኔ እዚህ የመጣሁት መንግሥትን በመወከል ሳይሆን በግል እምነቴና ቤተ ክርስቲያኔ በምታከናውነው ሃይማኖታዊ በዓል ላይ ለመገኘት ነው ብለዋል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊና የልማት ሥራዎችን እንዳታከናውን በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ይገጥማት እንደነበር አይተናል ያሉት ፕሬዝዳንቱ በአሁኑ ጊዜ ግን አንዳንድ ሁኔታዎች እየተስተካከሉ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የእምነት ተከታዮች ያሏት እንደመሆኗ መጠን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ተወላጆችን በአባትነት መምረጧ ትክክለኛና ወቅታዊም ነው ብለዋል።

በመቀጠልም ፕሬዝዳንቱ በማንኛውም መካከል ልዩነት መፈጠር እንደሌለበት ገልጸው ክርስቶስ እኔ ፍቅር ነኝ ተፈቃቀሩ እለ እንጂ እንዲህ አድርጉልኝ አላለም፤ በአንተ ላይ ሊደረግብህ የማትፈልገውን በባልንጀራህ ላይ አታድርግ ነው ያለው ካሉ በኋላ የዛሬ ተመራጭ ኤጲስ ቆጶሳት ወደፊት ዘርፈ ብዙ ሥራ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። በመጨረሻም ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታከናውነው ማንኛውም ሥራ ላይ በማንኛውም ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ጐን መሆናቸውን ገልጸዋል።

በፕሮግራሙ መክፈቻ ላይ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ የከንባታ ሀድያና ጉራጌ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ባሰሙት



www.ethiopianorthodox.org

ቃል ፕሬዝዳንት ግርማ የቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረሻ ሥልጣን በሆነው በ፲፯ቱ ኤጲስ ቆጶሳት በዓለ ሢመት ላይ በመገኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸው የአሁኑ ኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ በአሁኑ ወቅት መካሄዱ ወቅታዊና አስፈላጊ ነው፤ ይሁን እንጂ እንደ ምእመናኖቻችን ብዛት አሁን የተመረጡት ኤጲስ ቆጶሳት በቂ አይደሉም ብለዋል። ስለሆነም ወደፊት ተጨማሪ ኤጲስ ቆጶሳት የሚያስፈልጉ መሆኑን ጠቁመው የአሁኖቹ ተመራጮች ለቅዱስ ፓትርያርኩና ለቅዱስ ሲኖዶስ አጋዥ በመሆን የበለጠ ሥራ እንዲሠሩ ያደርጋሉ ብለዋል። በመጨረሻም የተመረጡት አዲሶቹ ኤጲስ ቆጶሳት ስፊ ሥራ እንደሚጠብቃቸው ጠቁመው መጪው የሥራ ዘመን መልካም እንዲሆንላቸው እግዚአብሔርን እንለምናለን በማለት ንግግራቸውን ደምድመዋል።

ከብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳቱ ንግግር በመቀጠል ከተመራጭ ኤጲስ ቆጶሳት መካከል ብፁዕ አቡነ ሉቃስ በክልል ትግራይ ምዕራባዊ ዞን የሰቲት ሑመራ ጳጳስ ተመራጭ ኤጲስ ቆጶሳቱን በመወከል ለወደፊት በሚጠብቃቸው ሥራ ሁሉ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንንና ሕገ ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅ ለመሥራት ቃል ገብተዋል።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ቃለ ምዕዳንና ቡራኬ ሰጥተው የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል፤ በበዓሉ ላይ አምባሳደሮች፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎች፣ የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

በተያያዘ ዜና በዚሁ ዕለት ከሰዓት በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ጥበባዊ እድሳት የተደረገለት የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ምረቃ ሥነ ሥርዓት ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ ክቡር አቶ አርከበ እቁባይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጊዜያዊ ከንቲባ፣ አምባሳደሮች፣ የጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎች፣ የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ከአቶ አርከበ ጋር በመሆን እድሳት የተደረገለትን ሐውልት መመረቁን የሚያበሥረውን ሪቫን ከቆረጡ በኋላ የሐውልቱን አካባቢ ለማስጌጥ የተሠራውን ሥራ ተዘዋውረው ተመልክተዋል፤ በመቀጠልም ክቡር አቶ አርከበ የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ ከንቲባ ባደረጉት ንግግር በወራሪው ጣሊያን ሐምሌ ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም የተገደሉት ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ይህ የመታሰቢያ ሐውልት የተሠራው ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ.ም ነው፤ ካሉ በኋላ ይኸው ሐውልት የከተማችን መለያ ምልክት ከሆኑት ታሪካዊና ዘመናዊ ሐውልቶች አንዱ ነው፤ በመሆኑም በከተማችን የሚገኙ ሐውልቶችን ተንከባክቦ የማቆየት ኃላፊነት የሁላችንም ነው ብለዋል።

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሐውልትና አደባባይ ከፍተኛ ወጪን በመመደብና ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በማደስ ያደረገችው አስተዋጽኦ በአርአያነት የሚጠቀስ ነው ካሉ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ አደባባዮችን ከማስዋብ ባሻገር ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋት የተለያዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲስፋፉና ከአዲስ አበባ አስተዳደር ጋር በመሥራት እያደረገች ያለችውን ከፍተኛ ትብብርና ለከተማችን መሻሻል የምትጫወተውን ሚና አድናቆቴንና ምስጋናዬን አቀርባለሁ በማለት ንግግራቸውን ደምድመዋል።

በመቀጠል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፤ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፤ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባሰሙት ቃል የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ከተሠራ ከ፷ ዓመት በላይ ያስቆጠረ መሆኑን ገልጸው ክቡር ከንቲባው ስለከተማይቱ ማስዋብና መነቃቃት ባደረጉት እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያናችንም ተሳታፊ እንድትሆንና የሃይማኖትም የሀገርም ሰማዕት የሆኑት አባት ሐውልትና አካባቢን ማስዋብ በይበልጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከታት ስለሆነ ሥራውን ለመሥራት ችለናል ብለዋል።

ቅዱስ ፓትርያርኩ በማያያዝም እንደገለጹት ወራሪዎች ለአምስት ዓመታት በኢትዮጵያውያን ላይ አሠቃቂ እልቂት ሲፈጽሙ ከቆዩ በኋላ ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን እንጂ የፋሽስቶች አይደለችም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም ለፋሽስቶች እንዳይገዛ ምድርም እንዳትቀበላቸው በማውገዛቸው ሕዝብ በተሰበሰበት አደባባይ ላይ በጥይት ደብድበው ገደሏቸው ካሉ በኋላ በግፍ የተገደሉት የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፴፯ ዓ.ም በግርማዊ ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ተመሥርቶ በአሁኑ ጊዜ እድሳት ስላስፈለገው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትብብር በልዩ ኪነ ጥበባዊ አሠራር ተሠርቶ ለምርቃት በቅቷል በማለት አባታዊ ንግግራቸውን ደምድመዋል።

ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ በምእመናን ዘንድ በተለምዶ ሰማዕት እየተባሉ እንደሚጠሩ የሚታወቅ ነው፤ ይሁን እንጂ በቅዱስ ፓትርያርኩና በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት ከዛሬ ጀምሮ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሊቀ ጳጳስ ሰማዕተ ጽድቅ ዘኢትዮጵያ ተብለው በይፋ እንዲጠሩ የተወሰነ መሆኑ ተገልጾአል። የሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልት እድሳት ምረቃ በዓልን ልዩ የሚያደርገው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የተመረጡት የ፲፯ ኤጲስ ቆጶሳት በዓለ ሢመት በተከበረበት ዕለት መመረቁ ነው።

እስክንድር ገ/ክርስቶስ



## ፲፯ቱ ኤጲስ ቆጶሳት የተሾሙባቸው አህጉረ ስብከትና ስመጵጵስና



ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል
የከፋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል
የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት
የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ
ረዳት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ሉቃስ
የሰቲት ሁመራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ
የትግራይ ደቡባዊ ዞን ሀገረ ስብከት



ብፁዕ አቡነ አብርሃም
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ
ተልእኮ መምሪያና የደብረ ኃይል ቅዱስ
ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን የበላይ ኃላፊ ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ዳንኤል
የአሶሳ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ያሬድ
የምሥራቅ ወለጋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ሚካኤል
የትግራይ ሰሜናዊ ምዕራብ ዞን
ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ሄኖክ
የምዕራብ ወለጋ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ ቀሌምንጦስ
የምሥራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ዕንባቆም
የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ሰላማ
የርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም
ጽዮንና የትግራይ ማዕከላዊ ዞን
ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ
የመቀሌ ደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል
ካቴድራልና የከሣቴ ብርሃን ሰላማ
መንፈሳዊ ኮሌጅ የበላይ ኃላፊ ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ
የዋግ ሕምራ ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ
የትግራይ ምዕራባዊ ዞን
ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ
የነገሌ ቦረና
ሀገረ ስብከት ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ
ኤዎስጣቴዎስ
የምዕራብ ሐረርጌ



# ፫፻፲፰ ሊቃውንት በኒቅያ

ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት የምንላቸው መንፈስ ቅዱስ ከብዙ መናፍቃን ውስጥ የመረጣቸውንና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያደረጋቸውን እውነተኞችን መምህራንን ነው።

ታሪኩን ስንመለከት የንግሥት እሌኒ ልጅ ታላቁ ቈስጠንጢኖስ ከክርስቲያናዊቱ እናቱ ከእሌኒ ባገኘው መንፈሳዊ ዕውቀት ፀረ ሕዝብና ፀረ ክርስትና የሆነውን መክስምያኖስን በመስቀል ኃይል ድል ነሥቶ በሮሜ በነገሠበት ወራት ወልድ ፍጡር የሚል አርዮስ የሚባል ክፉ መናፍቅ ተነሣ። ከእሱ ቀደም ብለው መክስምያኖስና ዲዮቅልጥያኖስ የሚባሉ ሁለት ዐላውያን ነገሥታት ተነሥተው አብያተ ክርስቲያናት ይትዐፀዋ አብያተ ጣዖታት ይትረኃዋ አብያተ ክርስቲያናት ይዘጉ፣ አብያተ ጣዖታት ይከፈቱ ብለው አወጁ። በዚህ ጊዜ የክርስቲያኖች አንገት እንደ በግ ታርዶ ደማቸው እንደ ጐርፍ ወርዶ ነበር።

ንጉሡ ቈስጠንጢኖስ አዋጁን በአዋጅ መልሶ የጣዖታት ቤቶች ይዘጉ፣ አብያተ ክርስቲያናት ይከፈቱ ብሎ በማወጁ ክርስቲያኖች ደስ ስላላቸው የአርአያ መስቀሉን፣ የጥናውን፣ የጸሕሉን ስብር ባሪ፣ የልብሰ ተክህኖውን ቅዳጅ ይዘው መስቀል ኃይላችን፣ ብንዋጋ ድል መንሻችን፣ ብንመክት ጋሻ መከታችን፣ መስቀል መግረሬ ፀር እያሉ ተቀብለውታል። እሱም ቀድሞ እናቱ ያስተማረችው ኋላም በጸፍጸፈ ሰማይ ያየው የመስቀል ምልክት (አርአያ) አሁን ደግሞ ምእመናን ይዘው የተቀበሉት አንድ ሆኖ ቢያገኘው ሃይማኖቱን ተረዳውና የደከሙትን ምእመናን እሱ እየሄደ ይጠይቃቸዋል፤ የበረቱት እነርሱ እየሄዱ ይጠይቁታል። መናፍቁ አርዮስ እለእስክንድሮስን ይከስ ነበር፤ እለእስክንድሮስ ሕፃን ስለነበር ሲጠይቀው ሄዶ ሳለ ተጨዋውቶ ሲሰናበተው ንጉሡ መምህር የጮኽብህ ሰው አለ አለው፤ እለእስክንድሮስም ነገሩ ገብቶት ማነው? አርዮስ ነውን አለው፤ ንጉሡም አዎን አለው፤ እለእስክንድሮስ እንግዲያውስ አፋርዱኝ አለው፤ ለጊዜው አርዮስ ቢፈለግ ጠፋ ኋላ ግን እንደዛሬዎቹ መናፍቃን መንደር ለመንደር ሲያውደለድል ተገኘና መጣ፤ እለእስክንድሮስ በሕግ ገጠመው ንጉሡ የእለእስክንድሮስ ነገሩ እውነት የአርዮስ ነገሩ ሐሰት እንደሆነ ስተለተረዳ እለእስክንድሮስን ጉባኤ ላቁምልህ? አለው፤ እለእስክንድሮስም እውነትን የያዘ አይፈራምና ወተፈስሐ በጉባኤ ማኅበር ይላል ጉባኤ ይደረግ በመባሉ ደስ አለው፤ ምክንያቱም መንደር ለመንደር እያውደለደለ ምእመናኑን ከሚያሳስት ሐሰተኛነቱ በጉባኤ ሲገለጥበት ያፍራል ብሎ ነው።

ቈስጠንጢኖስም ጉባኤ በኒቅያ ይሁን ብሎ አዋጅ ነገረ፤ ስለምን ቢባል ሰፊ ሜዳ እንደ ወግዳ እንደ ሚባለው ሲቃን ጳጳሳቱን ከነካህናቱ፣ ንጉሡን ከነሠራዊቱ፣ አካታ የምትይዝ ስለሆነች ነው። ከዚህ በኋላ ከሚያዝያ ማርያም እስከ መስከረም ማርያም ጉባኤው ተሟልቶ እንዲሰባሰብ አዋጅ ታወጀ፤ እርቆ የቀጠረው የታመመው ድኖ፣ የታከተው አዝግሞ እንዲደርስ ነው፤ የመስከረም ማርያም ጉባኤ ተሟልቶ እስከ ኅዳር ፱ ቀን ድረስ ሱባኤ ተያዘ ከዚህ በኋላ ሃይማኖታችሁን፣ ስማችሁንና ሀገራችሁን ጽፋችሁ ስጡኝ አላቸው።

ይህ ሊሆን የቻለው በመቃርዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም ምክንያት ነው፤ መቃርዮስ ኤጲስ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም ሃይማኖታችሁን ጽፋችሁ አምጡ ስለተባለ የሃይማኖቱ መግለጫ የሆነውን የሐዋርያትን አመክንዮ ይዞ ሄዶ ነበር፤ አርዮሳውያኑ ምእመናኑን ይዘው ሲያስቃዩአቸው ስለአየ ሁለት ዲያቆናት አስከትሎ በመሄዱ እነዚህን ዲያቆናት ወደቤታቸው የሚመልስልኝ ይህንን መጽሐፍ የሚወስድልኝ ባገኝ እኔስ ከዚሁ በሰማዕትነት ብሞት እወድ ነበር ብሎ ሲያስብ መልአኩ ተገልጾ ሰማዕትነት አማረህ አለው? እኒህ ዲያቆናት የሚመልስልኝና ይህንን መጽሐፍ የሚወስድልኝ የለም እንጂ አዎን አለው፤ መልአኩም እኔ እወስድልሃለሁ አንተም የወደድኸውን አድርግ ብሎ የሃይማኖቱ መግለጫ የሆነውን የአመክንዮውን መጽሐፍ ይዞለት ሄደ። ለንጉሡ የሚነግርለት አጥቶ ሰባት ቀን ሰነበተ፤ በሰባተኛው ቀን እንደ እሳት አየተን በገበገ ሄደ፤ እረ ዛሬስ የማንች



www.ethiopianorthodox.org

ሰው ሰው መጣብን ብለው ነገሩት፤ ተውት የተበደለ ደሃ ይሆናል አላቸው። ጉብዩ እንዲህ ያለውንማ መንግሥት አላውያንስ ፴ ዘመን ነግሠውበት አልነበረምን? ከእን ጨት መርጦ ስታቦት ከሰው መርጦ ለሹመት እንዲሉ አንተን መርጦ ያነገሠህ ፍርድ ጎደለ፤ ደሃ ተበ ደለ እንድትል አይደለምን? በዚ ህም ላይ ይህንን የመሰለውን ሃይማኖት ተቀበል ሌላውን እንዳ ትቀበል ተብሰሃል ብሎ መልእክ መሆኑን ለማጠየቅ ግንቡን ሰን ጥቶ ዐረገ፤ ከዚህ በኋላ ሃይማ ኖት በ፫፻፲፰ ሊቃውንት ይጽና ብሎ አዋጅ ነገረ፤ ከነዚህም ሊቃ ውንት መከራ ያልተቀበለ፤ ተአም ራት ያላደረገ የለም፤ ይልቁንም ቶማስ ዘመርዓስ ፳፱ ዓመት አጽቅ አጽቁን እየቈረጠ ለጣኦት ሲሰ ጡት ኑረዋል፤ (አላውያን) ጌታም ከ፫፻፲፰ቱ ጋር ፫፻፲፱ኛ ሆኖ ነገ ራቸውን ያቃናላቸው ነበር። እለ እስክንድሮስ አጽንቶ ተከራክረው፤ ምክንያቱም ለጴጥሮስ ተፍጻሜተ ሰማዕት አርዮስ፤ አኪላስና እለእስ ክንድሮስ የሚባሉ ፫ ደቀ መዛሙ ርት ነበሩት፤ ደቀ መዛሙርቱ እሊህ ብቻ ባይሆኑም ሁኔታው የሚመ ለከታቸው ፫ቱን ብቻ ነውና ነው። አርዮስ ዕቃ ቤት ጉብዩ መጻሕፍ ትን ይመለከት ነበርና ምሳሌ ሰሎ ሞንን ሲመለከት ትቤ ጥበብ ፈጠ ረኒ እግዚአብሔር መቅድመ ኩሉ ተግባሩ ከሚል ንባብ ደረሰ፤ ትር ጉሙ ጥበብ እግዚአብሔር የሥ ራው ሁሉ በኩር አደረገኝ አለች ማለት ነው። ታዲያ ይህ ምሥ ጢር የእኛ ባሕርይ አካላዊ ቃልን ተዋሕዶ በኩረ ምእመናን የምእ መናን አብነት መሆኑን የሚናገር ሲሆን ሮሜ. ፰፥፳፱ ከመምህሩ ሳይጠቅ በራሱ ትርጉም ጥበብ ወልድ ነው እግዚአብሔር ፈጠረኝ ማለቱ ነው ብሎ በመውሰድ ወልድ ፍጡር ነው ብሎ ካደ።

ከመምህሩ ቢጠይቅ ኖሮ የ፫ቱም ስም እንጂ የአብ ብቻ አለመሆኑን ይረዳ ነበር፤ ምክንያቱም አካላዊ ቃል የተዋሐደውን የእኛን ባሕ ርይ የፈጠሩት አብ ወልድ መን ፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አንድ እግዚአብሔር መሆናቸውን ይረዳ ነበር ማለት ነው። መምህሩ ቅ/ጴጥ ሮስ ሰምቶ በመጀመሪያ ምክር ሰጠው፤ ኋላ ግን የማይመለስ መና ፍቅ መሆኑን ጌታ ገለጸለትና አው ግዞ ለይቶ አርዮስ የማይመለስ መናፍቅ መሆኑንና ራሱ ቅዱስ ጴጥሮስ ካለፈ በኋላ አኪላስ እንደ ሚሾመውና በውዳሴ ከንቱ ተጠ ልፎ አርዮስን ከግዘቱ እንደሚ ፈታውና እንደሚቀሰፍ ኋላ ግን በኒቅያ በንጉሡ በቈስጠንጢኖስ ሰብሳቢነት ሰፊ ጉባኤ እንደሚደ ረግና እሱ አፈጉባኤ ሆኖ ተከራ ክሮ እንደሚረታው እለእስክንድ ሮስ ከመምህሩ ተረድቶ ነበርና ስለዚህ የነገሩ ሁነኛ የጦሩ አርበኛ እንዲሉ ገጠመው ጉባኤውም ተከ ራከር ብሎ እለእስክንድሮስን አፈ ጉባኤ አድርጎታል። አርዮስ የፍ ጥረቱ በኩር አደረገኝ ብሏል አለ፤ እለእስክንድሮስ ደግሞ ሲመልስ ተራሮች ኮረብቶች ሌሎችም ሳይ ፈጠሩ አስቀድሞ ወለደኝ ይልብ ሃልስ አሳው፤ አርዮስም አምን ይፈጥረዋልም፤ ይወልደዋልም ብሎ መለሰ፤ እለእስክንድሮስ ደግሞ ምነው እኛ የምንወልደውን አንፈ ጥረውም፤ የምንፈጥረውን አንወ ልደውምሳ ዳግመኛ ሐዋርያው ወን ጌላዊ ሲጽፍ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ ወኢምንትኒ እንኳን መው ለድ መፍጠር እሱ አስቀድሞ ምንም ምን የሆነም የተደረገም ነገር የለም ይልብሃልስ ብሎ ረቶታል።

አርዮስም ባለመመለሱ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ስለገዘቱትና ንጉሡ በዓዋጅ ስለለየው የእነሱ ግዘት ሰይፍ ሆኖ ስለቆራረጠው አንጀቱ ከ፫፻፲፰ ተቆራርጦ ከደጀ ሰላም ተዘርግፎ ተገኝቷል። ከዚህ በኋላ ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት ብዙ ድርሰት ደርሰዋል፤ ብዙ ተግሣጽ ጽፈዋል፤ ከብዙውም ጸሎተ ሃይማኖትን ለምእመናን፤ ሕንጻ መነኮሳትን ለመ ነኮሳት፤ ግሩም ትዳሴን ለቀሳው ስት ተናግረዋል። እኛ ግን ለም እመናን የሃይማኖታቸው ማጽኛ እንዲሆናቸው ብለው ለምእመናን የተናገሩትን ጸሎተ ሃይማኖት ብቻ ለምእመናን በቤተ ክርስቲያናችን ዘይቤ (አባባል) እንጽፋለን።

## ጸሎተ ሃይማኖት

በባሕርይ በሕልውና ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ አም ላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን፤ ዓለምን በፈጠረና እንደ ጥና እንደ እንቁላል በመ ሐል እጁ በያዘ የሚታየውን ግዙ ፉን፤ የማይታየውን ረቂቁን በፈ ጠረ በእግዚአብሔር አብ እናምና ለን፤ በባሕርይ በሕልውና ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ጌታ በሚሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስ ቶስ እናምናለን፤ ተቀዳሚ ተከ ታይ በሌለው የአብ የባሕርይ ልጅ በሚሆን ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር እንደ እሱ በነበረ ከብርሃን አብ በተገኘ በብርሃን ወልድ፤ ከባሕርይ አምላክ ከአብ የተገኘ በባሕርይ አምላክ በወልድ በተወ ለደ እንጂ ባልተፈጠረ በወልድ፤ በሥልጣን በጌትነት በባሕርይ ከአብ ጋር አንድ በሚሆን ሁሉ በእሱ ቃልነት በእሱ ህልውና በተፈጠረ ያለ እርሱ ቃልነት ያለእርሱ ህል ውና ምንም ምን የተፈጠረ የሆነ የሌለ በሰማይም ያለ በምድርም ቢሆን ያለ እርሱ የተፈጠረ የሆነ የሌለ ስለ እኛ እኛን ለማዳን ከሰ ማየ ሰማያት ወርዶ በግብረ መን ፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው በሆነ የ፴ ዓመት ሰው (ጐልማሳ) ሆኖ የጳንጦስ ሰው ጲላጦስ በነገሠበት ወራት ስለእኛ ተሰቀለ ስለ እኛ መከራ ተቀብሎ ሞተ ተቀበረ ንጹሐት ክቡራት በሚሆኑ መጻሕፍት እንደተጻፈ በሦስተ ኛው ቀን ተነሣ በብርሃን በትዳሴ በክብር በሥልጣን ወደ ሰማየት ዐረገ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ዳግ መኛ በብርሃን በሥልጣን በጌት ነት ይመጣል፤ በሕያዋንና በሙ ታን ይፈርድ ዘንድ ሕያዋን ጻድ ቃን፤ ሙታን ኃጥአን ናቸው። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፤ ሐተታ የፍጡር ግዛቱ ውሱን ነው እሱ ግን የባሕርይ አምላክ ነውና ግዛቱ ለዘለዓለም መንግ ሥቱ ለዘለዓለም ነውና፤ እስከዚህ ያለውን ክፍል የተናገሩት ሠለስቱ ምዕት ናቸው። አርዮስ በተረታ በ፶፰ ዓመቱ ደግሞ መቅዶንዮስ የሚባል መናፍቅ ለአብ መንበር እንዳለው እግዚአብሔርስ ይደነ ብር ዲበ መንበሩ ቅዱስ ማለትም እግዚአብሔር በልዩ ዙፋኑ ጸንቶ ይኖራል ብሎ መጽሐፍ ይናገ ራል፤ ለወልድም መንበር እንዳ ለው መንበርከ እግዚኦ ለዓለመ ዓለም ማለት ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው ብሎ መጽሐፍ ይናገራል፤ ለመንፈስ ቅዱስ ግን መንበር እን ዳለው መጽሐፍ የተናገረበት ቦታ የለምና መንፈስ ቅዱስ ሕፁዕ ነው ብሎ ተነሣ፤ ንጉሡ ዘየዐቢ ቴዎ ዶስዮስ ታላቁ ቴዎዶስዮስ በቊስ ጥንጥንያ ጉባኤ ይሁን ብሎ አወጀ፤ በዚህ ምክንያት ፩፻፶ ሊቃ ውንት ተሰባሰቡ፤ አፈ ጉባኤው ጢሞቴዎስ ዘእልቦጥሪት ነው፤ ጥሪት ቁሪት የሌለው መናኝ ማለት ነው፤ ነቢዩ ኢሳይያስ ያዝያን በሞ ተበት ወራት እግዚአብሔርን በታ ላቅ ዙፋን ላይ አየሁት ያለውን ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር ያለው መንፈስ ቅዱስን ነው ብሎ ተር ጕሞብሃልስ ብሎ ረትቶታል፤ ኢሳ.፮፥፩፣ ግቢሐዋ. ፳፰፥፳፭ በዚህ ጊዜ መናፍቁን መቅዶንዮስን አው ግዘው ሁለተኛውን ክፍል ድርሰት ፩፻፶ ሊቃውንት እንዲህ በማለት ፈጽመውታል፤

«የባሕርይ ገዢ» በሚሆን በመ ንፈስ ቅዱስም እናምናለን፤ ከአብ አካል ከአብ ባሕርይ የሠረፀ ከአብ ከወልድ ጋር እንደ አብ እንደ ወልድ በአንድነት እንስገድለት ከአብ ከወ ልድ ጋርም በነቢያት አድሮ የተ ናገረ እሱ ነውና በአንድነት እና መስግነው፤ ሐዋርያት ባነጽዋት ከምኩራብ አረሚ ከምኩራብ አይ ሁድ በላይ በምትሆን በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናም ናለን፤ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት የሚሠዋባትም የአንድ የወ ልደ እግዚአብሔር አካል ነውና ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀትም እናምናለን። ጥምቀት አንዲት ናትና የሙታንንም ትን ሣኤ እናምናለን፤ እንደ መላእ ክትም ሕያዋን ሆነን ለዘለዓለም እንደምንኖር እናምናለን›› ብለው አስተምረውናልና፤ ስለዚህ አንድ አምላክ ብለን የምናመልከው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንዱ እግ ዚአብሔር ከመናፍቃን ጥርጥር አድኖና በሊቃውንት ያሳደረውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በእኛ ላይም አሳድሮ፤ ሃይማኖታችንን አጽን ቶን፤ ምግባራችን አቅንቶን እንድ ንኖር ይረዳን ዘንድ ቤተ ክርስ ቲያናችን ለወደፊቱም በማኅተመ ጸሎት እምነት አትማ ሰጥታን ስን ጠቀምበት እንገኛለን፤ ከአጋንንት ከአይሁድና ከመናፍቃን ፈተና የም ንድነው ሃይማኖታችን አጽንተን ታሪካችን ጠብቀን ስንኖር መሆ ኑን አምነን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ዘወትር እንጠይቅ። ♦

መልአከ ሰላም ኃይለ ኢየሱስ ከበደ



www.ethiopianorthodox.org

# መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓመተ ምሕረት በደመራ በዓል ላይ በመስቀል አደባባይ ስለተፈጸመው አሳዛኝ ድርጊት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ ከምታከብራቸው ሃይማኖታውያንና ብሔራውያን በዓላት መካከል መስከረም ፲፯ ቀን የሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል አንዱ መሆኑ ይታወቃል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁሉ ድኅነትን ያደረገበት፣ ዕርቅና ሰላምን ያወጀበት፣ የሰላምና የክርስትና ሃይማኖት ዓርማ የሆነው ቅዱስ መስቀል በመስቀል ጠላቶች ከተደበቀ በኋላ የተገኘበት ዕለት፤

- የሀገሪቱ መሪ፣
- ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣
- የውጭ ሀገር መንግሥታት ተወካዮች፣
- አምባሳደሮችና ዲፕሎማቶች፣
- ታዋቂ የሀገር ሽማግሌዎች፣
- ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣
- የታሪክና ባህል ተረካቢ የሆነው ወጣቱ ትውልድ፣
- መላው ሕዝበ ክርስቲያን በተገኙበት ሲከበር የኖረ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

በተለይም በዚህ ዓመት ክቡር የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት፣ ክቡር የአዲስ አበባ ከንቲባ፣ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊና ሌሎች የምክር ቤቱ አባላት በአጠቃላይ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ሕዝበ ክርስቲያን በተገኙበት የዋዜማው ሥርዓተ ጸሎት እየተከናወነ ሳለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ባላወቀችውና ባልተረዳችው ሁኔታ የሥርዓተ ጸሎቱን አካሔድ የሚያሰናክል የበዓሉን ታሪካዊና ባህላዊ ሥርዓት በጥሞና የሚከታተሉ የውጭ ዜጎችንና ምእመናንን የሚያስደነግጥ በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ከታነጸ ኅብረተሰብ የማይጠበቅ አላስፈላጊ የጩኸት ድምፅ ሲስተጋባ ይሰማ ነበር።

ይህም ኢ-ሥነ ምግባራዊ ድርጊት ከተሰማ በኋላ የድንጋይ ውርዋሮን አስከትሏል፤ በዚህም ምክንያት፦

ታሪካዊና የተቀደሰው የ፲፱፻ ፺፰ ዓ.ም የደመራ በዓል በሥርዓተ አልበኞች በተፈጠረ ግርግር ያልተጠበቀ ሁከት ተከስቶበታል።

የባህላችንና የታሪካችን ተከታታዮች የሆኑ በውጭ ሀገር ሰዎች ላይ ድንጋይ ተወርውሮባቸዋል፤

በሰላማዊያን ሥርዓት አስከባሪዎችና በዓሉን በሚያከብሩ ሕዝበ ክርስቲያን ላይ ያልተጠበቀ ችግር ደርሶባቸዋል፤

በራስዋ ሕግ የምትመራዋ በማንም በምንም ጣልቃ የማትገባውና አድልዎ የማታደርገው ቤተ ክርስቲያናችን ዓመታዊውን ሃይማኖታዊ የደመራ በዓል በተለመደው ሥነ ሥርዓት በነፃነት እንዳታከብር ልዩ ተልእኮ ያላቸው በሚመስሉ ሕገ ወጥ ግለሰቦች ተስታሽነት ተደፍራለች።

በዚህ ታላቅ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ በዓል አማካኝነት በዓለም የታወቀችው ኢትዮጵያ እነዚህ ሕገ ወጦች በፈጸሙት አሳዛኝ ድርጊት ስትቸት ተጋልጣለች።

በሃይማኖትና በመልካም ሥነ ምግባር የታወቀው ሕዝብም ለትችት ተዳርጓል።

ቤተ ክርስቲያናችን እስከሁን ድረስ ከማንም ለማንም ሳትወግን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎቷን እየሰጠች መቆየቷ ይታወሳል። [illegible] ተብሎ መቀየሷ [illegible] ማን ሊትታገሰው አልቻለችም።

ስለዚህ በ፲፱፻፺፰ ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል ላይ የተሰነዘረውን ከሃይማኖትና ከሥነ ምግባር ውጪ የሆነ ታሪክ ደምሳሽ ድርጊት በጥብቅ ታወግዛለች።

ተከታዮቿ ምእመናንም የሃይማኖታቸውን ሥርዓትና ሕግ በመጠበቅ ለሰላም በመቆም ሃይማኖትና ሥነ ምግባር ከሚፈቅደው ድርጊት እንዲርቁ ትመክራለች፣ ታስተምራለች።

በሃይማኖት በዓል ሳቢያ የግል ፍላጎትን ለመወጣት መሞከር ሃይማኖተኛነትን የሚገልጽ ሳይሆን በሃይማኖት ሽፋን ስውር ዓላማን ለማራመድ የታቀደ ድርጊት በመሆኑ ከዚህ ዓይነቱ ድርጊት ሁሉም ወገን እንዲቆጠብ ቤተ ክርስቲያን በጥብቅ ታሳስባለች።

ሀገራችን ከድህነትና ከበሽታ፣ ከኋላ ቀርነትና ድንቁርና አዘቅት ወጥታ ሌላው ዓለም ወደ ደረሰበት ለመድረስ ትችል ዘንድ ማንኛውም ወገን ተቻችሎና ተከባብሮ ለሰላምና ለልማት እንዲቆም ቤተ ክርስቲያን መልእክቷን ታስተላልፋለች።

በውጭም በውስጥም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ዓላማ ትታ የሌላውን ዓላማ እንድታራምድና እንድትደግፍ በመሻት ቤተ ክርስቲያንን ጥግ በማድረግ ከማንም ጋር የማትወግነውን ቤተ ክርስቲያን ወገናዊነት ያላት አስመስሎ ያለ ስሟ ስም ያለ ግብሯ ግብር የሚሰጧትን ሁሉ አጥብቃ ትቃወማለች።

የሃይማኖትና የሥርዓቱ ተከታይ ያልሆኑ ሁከት ፈጣሪዎች ዘቤተ ክርስቲያናችን በዓላት ላይ ሃይማኖታውያን መስለው በመግባት ችግር እንዳይፈጥሩ የሁሉንም ወገን ሰላም ለማስከበር ኃላፊነት ያለው መንግሥት ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርግ ቤተ ክርስቲያናችን ጥሪዋን ታቀርባለች።

‹‹እግዚአብሔር አምላክ ለሀገራችንና ለዓለም ሁሉ ሰላሙን ይስጥልን።››

መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም

# ግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም መሐንዋ መስቀሉ ለክርስቶስ

የክርስቶስ ደም የፈሰሰበት ክቡር መስቀል በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባለው ሁሉ የነፃነት ምልክታችንና መመኪያችን መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክር ‹‹በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል እንጂ በሌላ አልመካም›› ብሏል። ሐዋርያው እንዳለው በእርግጥም ክቡር መስቀሉ አለኝታችንና ከኃጢአት ባርነት ነፃ የወጣንበት ዓርማችን መሆኑን በተለይ እኛ ኢትዮጵያዊያን አበክረን እናውቃለን። ክርስቶስ የተሰቀለበት ክቡር መስቀል በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ተጋርዶ የነበረውን የጥል ግድግዳ አጥፍቶ እርቅና ሰላም መፈጠሩንና ዘላለማዊ ሕይወት መገኘቱን ያረጋገጠልን የክርስቲያኖች ሰንደቅ ዓላማችን ነው። የእግዚአብሔር ወዳጆች ለሆን ሁሉ ኃይላችን ነው። አባቶቻችን በመስቀሉ ኃይል ጠላቶቻቸውን ድል አድርገዋል። ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በጥቂት ሠራዊቱ የጦር መሣሪያ ላይ የመስቀል ምልክት አድርጎ በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠር ሠራዊት የነበራቸውን ኢአማንያን (አላውያን) ነገሥታት ዲዮቅል ጥያኖስና መክስምያኖስ የተባሉ የሮም ነገሥታትን ድል አድርጓቸዋል።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ጠላቶቻችንን በሙሉ በመስቀሉ ኃይል እንደምናሸንፋቸው አረጋግጧል። ስለዚህም ነው ኢትዮጵያውያን ነገሥታት አፄ ዳዊትና በኋላም ልጃቸው አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ክቡር መስቀሉን ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ጥረት አድርገውና መሥዋዕትነት ጭምር ከፍለው ወደ አገራችን ያስገቡት ክቡር መስቀሉ ከወርቅና ከእንቍዕ ከአልማዝ እንደሚበልጥ ድኅነተ ሥጋ ብቻ ሳይሆን ድኅነተ ነፍስ የሚገኝበት መሆኑን በማረጋገጣቸው ነው። በዚህ በያዝነው መስከረም ወር ብቻ ቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የክቡር መስቀሉን በዓል ሦስት ጊዜ በደመቀ ሁኔታ ታከብራለች። በዓላቶቹም፦

፩ኛ. መስከረም ፲ ቀን አፄ ዳዊት ክቡር መስቀሉን የተረከቡትን ቀን የአፄ መስቀል ወይም ተቀጸል ጽጌ በማለት፣

፪ኛ. መስከረም ፲፯ ለ፲፮ አጥቢያ ንግሥት እሌኒ በኢየሩሳሌም ተቀብሮ ጠፍቶ የነበረውን መስቀሉን ለማግኘት ጥረት ስታደርግ ቅዱስ ሚካኤል በሽማግሌ ተመስሎ ክቡር መስቀሉ ያለበትን ቦታ ለማግኘት ደመራ ደምረሽ ጢሱ ከሚያመለክትሽ ቦታ ስታስቆፍሪ ታገኝዋለሽ ባላት መሠረት ደመራ አስደምራ በተሰጣት ምልክት ቁፋሮውን ያስጀመረችበትና ክቡር መስቀሉም መጋቢት ፲ ቀን ከተቀበረበት ጥልቅ መሬት ተቆፍሮ ከወጣ በኋላ መስከረም ፲፯ ቀን የክቡር መስቀሉ ቅዳሴ ቤት የተከበረበት የመታሰቢያ ዕለት፣

፫ኛ. አፄ ዘርዓ ያዕቆብ አባታቸው አፄ ዳዊት ተረክበውት በመንገድ ላይ በድንገት በመሞቻው ምክንያት በአደራ እንዲቀመጥ ተደርጎ የነበረውን ክቡር መስቀል ‹‹አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ›› የሚል ራእይ ታይቷቸው ክቡር መስቀሉን በአደራ ከተቀመጠበት አገር ተረክበው መስቀለኛውን ሥፍራ ለማግኘት ለሦስት ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን በአራቱም መአዘናት ከዞሩ በኋላ በ፩ሺ፬፻፵፰ ዓ.ም መስከረም ፳፩ ቀን ክቡር መስቀሉን ወደ መስቀለኛው አምባ ግሸን በማስገባት ያስቀመጡበት ዕለት ናቸው። ግሸን ደብረ ከርቤ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ዘመን ይህ ነው ብሎ ለመግለጽ እንደሚያስቸግር አባቶች ይናገራሉ። ምክንያቱም ምንድነው ቢባል መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ጌታ ለፍጥረቱ ምን ያህል እንደሚያስብ የሚያስገነዝበው ሰው ከመገኘቱ አስቀድሞ አምባዋን በመስቀል አርአያ አድርጎ ቀርፆ ያስቀመጣት በመሆኑ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ ጊዜው እስከሚደርስ ጊዜ ድረስ በጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ለ ጊዜ ለኵሉ›› እንደተባለው ሁሉ እግዚአብሔር ተአምራቱን የሚገልጸው ሥራውን የሚሠራው ጊዜውን ጠብቆ ስለሆነ በዚህች አምባ ላይ መሠረት ሲጣል ቤተ ክርስቲያን ሲታነጽባት ማን ነቷ ሲታወቅ የቻለው በ፭፻፲፬ ዓ.ም በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ነው።

በአምባው ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የማር ጎጆ ቤተ ክርስቲያን በመሥራት የቆረቆሯት አባ ፈቃደ ክርስቶስ የሚባሉ ባህታዊ አባት ነበሩ። ይህች ጥንታዊና ታሪካዊት ደብር በክብር ከኢየሩሳሌም የምትተካከል በቃል ኪዳን የበለጸገች የምሕረት አምባ በመሆኗ ከዓለም ዙሪያ ጭምር ምእመናን ይሳለሟታል። የቃል ኪዳኗንም በረከት ለማግኘት ይሽቀዳደማሉ። ለዚህች መስቀለኛ አምባ የተሰጣትን ቃል ኪዳን ‹‹ጤፉት›› እየተባለች በዓመት አንድ ጊዜ በክብረ በዓሏ ላይ ከምትተረጎመው የግእዝ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ተገለጸው፦



www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በተሰቀለ ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ዑራኤል በብርሃን ጽዋዕ ከጌታ ጎን የፈሰሰውን ደምና ውኃ ተቀብሎ በኢትዮጵያ ምድር ላይ በተለይም በዚህች አምባ ላይ እንደረጨባት፣

፪ኛ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአባቶቻችን ተገልጾ የአምባዋን ክብርና ቃል ኪዳኗን እንዲህ በማለት ገልጾላታል። «በቀራንዮ በተሰቀልሁ ጊዜ ዑራኤል ከጎኔ የፈሰሰውን ደሜን ቀድቶ ይህችን አምባ ሁለንተናዋን ቀድሷታል። ስለዚህ ለጌትነቴ ምስጋና ማደርያ ትሆን ዘንድ ባርኬያታለሁ ቀድሻታለሁም አሁንም ምሥጢረ መለኮቴ እንደተገለጸበት እንደ ደብረ ታቦርና እንደተሰቀልሁበት እንደ ቀራንዮ አደባባይ እንዲሁም ንጹሕ ከሆነ ሥጋዋ ሥጋን ነሥቼ ሰው እንደሆንሁበት እንደ እናቴ አገር ኢየሩሳሌም ይህችም አምባ የእናቴ ርስት አድርጌያታለሁ፣ ማንኛውም ከሩቅም ሆነ ከቅርብ መጥቶ በክብረ በዓሏ ላይ የተገኘ ሰው ሁሉ ከመካነ መቃብሬ ዘንድ ኢየሩሳሌም እንደሄደ ይቆጠርለታል። በዚህች ደብር ውስጥ ሥጋዬንና ደሜን የሚቀበለውን ሰው ከኃጢአት ሞት አድነዋለሁ ዳግመኛም የሲዖልን ባሕር አሻግሬ ጽድቅና ሕይወት ደስታም ካለበት ገነት ውስጥ አኖረዋለሁ» በማለት ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል።

የክቡር መስቀሉ ዙፋን (መቀመጫ) የሆነችው ግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ዘንድሮ መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ቤተ ክርስቲያኗ ከተመሠረተች ፩ሺ፬፻፹፯ኛውን፣ ክቡር መስቀሉ ወደ አምባዋ የገባበትን ፭፻፶፱ኛውን ዓመት በደመቀ ሁኔታ ታከብራለች።

የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነት የመስቀሉ በረከት ይደርብን አሜን። ❖

ቀሲስ በላይ ተገኝ
የስዋስወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ
ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ዲን

# ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ



የጻድቁ አባታችን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አባታቸው ስምኦን እናታቸው አቅሌስያ ይባላሉ፣ የጻድቁ ወላጆች ስምኦንና አቅሌያስ በሕገ እግዚአብሔር የጸኑ ክርስቲያኖች ሲሆኑ ሀገራቸውም በላዕላይ ግብፅ የምትገኝ ንሒሳ የተባለች ናት፣ ስምኦንና አቅሌስያ ልጅ ስለአልነበራቸው ልጅ እንዲወልዱ ዘወትር በጾምና በምልጃ በጸሎት ፈጣሪያቸውን ይለምኑ ነበር።

እግዚአብሔርም የስምኦንና የአቅሌስያን ምልጃና ጸሎት ስለተቀበለ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መጋቢት ፳፱ ቀን ተጸንሰው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ተወለዱ። በተወለዱበትም ዕለት ከጨለማ ወደ ብርሃን ያወጣኸን አምላኬ ሆይ ክብርና ምስጋና ለአንተ ይሁን በማለት እየሰገዱ ፫ ጊዜ ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም ለስምኦንና ለአቅሌስያ ተገልጾ የዚህ ሕፃን ስም ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ ይጠራል ብሎ ከነገራቸው በኋላ ተሰወረ፣ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የእናታቸውን ጡት አልጠቡም፣ ከተወለዱ ሦስት ዓመት ከሆናቸው በኋላ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ስለአዘዘችው መልአኩ በክንፉ ተሸክሞ ወደ ገዳም ወስዶ አስቀመጣቸው ቅዱስ ገብርኤል ለአባ ዘመደ ብርሃን ተገልጾ ትልቅ እንግዳ ሕፃን ይፈልግሃል ወደ ቤትህ (በአትህ) ስትገባም ከበርህ ላይ ተቀምጦ ታገኘዋለህ።

ይህ ሕፃን እግዚአብሔር የመረጠውና ያከበረው ስለሆነ እያስተማርክ አሳድገው ብሎ ከነገራቸው በኋላ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከአባ ዘመደ ብርሃን ተሰወረ፣ አባ ዘመደ ብርሃንም መልአኩ እንደ ነገራቸው ወደ ገዳሙ በር ሲደርሱ እንደ ፀሐይ የሚያበራ ሕፃን በበሩ ላይ ተቀምጦ አገኙት።

አባ ዘመደ ብርሃንም አንተ የእግዚአብሔር እንግዳ ሕፃን ሆይ ወደ ቤት ግባ ብለው ወደ ገዳሙ አስገቧቸው። በዚያም በገዳሙ እያተማሩ በሥርዓተ አበው አሳደጓቸው፣ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም ተልእኮተ አበውን ትሩፋትን ምእናኑን መሠረት አደርገው በጸጋ እግዚአብሔር አደጉ፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጻ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ባረከቻቸው፣ ከዚያም በሥርዓተ ምንኩስና ተወስነው አባ አብርሃም ከተባሉ ሊቀ ጳጳስ የዲቁናንና የቅስናን ሹመት ተቀበሉ።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በአሉበት ገዳም በትምህርት ላይ ትህርምት፣ በትሩፋት ላይ ትሩፋት እየጨመሩ በታላቅ ተጋድሎ ተወስነው ይኖሩ ነበር። የጻድቁ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ልብሳቸው ከአካላቸው የበቀለው ርዝመቱ አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ፀጉራቸው ነበር፣ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በግብፅ አገር መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በአስቀመጣቸው በረሃ በጾም፣ በጸሎት፣ በትሩፋትና በስግደት ተወስነው ፲፰ ዓመታት ከኖሩ በኋላ ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል።

ጻድቁ አባታችን ወደ ሀገራችን የመጡት በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል መሪነት ሲሆን የመጡበት ዘመን በ፩ሺ፬፻፲፪ ዓ.ም ነበር። ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ መጀመሪያ የደረሱት አክሱም ጽዮን ነበር፣ አክሱምን ከተሳለሙና ከአዩ በኋላ ወደ ላስታ ሄዱ፣ በዚያን ጊዜ የሀገራችን ዋና ከተማ በላስታ ነበር፣ የሀገራችንም ንጉሠ ነገሥት ጻድቁ ላሊበላ ነበር።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከንጉሡ ከአፄ ላሊበላ ጋር ተገናኙ፣ ንጉሡ አፄ ላሊበላ ከቋጥኝ ድንጋይ ፈልፍሎ የሠራቸውን ፲፩ አብያተ ክርስቲያናት ጻድቁ ከባረኩና ከጐበኙ በኋላ የአብያተ ክርስቲያናቱ ሥራ እፁብ ድንቅ ነው ብለው አድንቀው ይህን ጥበብ የገለጸ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብለዋል።

ጻድቁ አፄ ላሊበላም ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዚሁ በቤተ መንግሥቱ አጠገብ የጸሎት ቤት ልሥራልዎትና በጸሎትዎ እየረዱኝ እየመከሩኝ አብረውኝ ይቀመጡ አላቸው። ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በዚህ ከአንተ ጋር እንድቀመጥ አይደለም የታዘዝኩት በኢትዮጵያ አገርህ የደብረ ታቦር አምሳል በሆነችው ተራራ በሸዋ በምትገኘው በደብረ ዝቋላ አምባ ነው አሉት፣ ንጉሡም አፄ ላሊበላ ቤተ መንግሥቱን ይባርኩልኝና ከዚያች ከሚሄዱባት ከደብረ ዝቋላ አብሬ ሄጄ አደርስዎታለሁ አላቸው።

ከዚያም አፄ ላሊበላ ሠራዊቱን አስከትሎ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ተከትሎ ወደ ሸዋ መጣ፣ በመጀመሪያ ምድረ ከብድ ደረሱ፣ ከዚያም ተመልሰው ኤረር ከመጡ በኋላ ቆፍቱ ከሚባል ቦታ ደርሰው ነገረ እግዚአብሔር ሲነጋገሩ አድረዋል፣ ቆፍቱ ከምትባል እንስተኛ ኮረብታ ላይ ከአደሩ በኋላ ደብረ ዝቋላ ሄደዋል። ንጉሡ አፄ ላሊበላም ይህች ደብረ ዝቋላ ገዳም ትሁንልዎ ብሎ ገድሞላቸዋል።

አፄ ላሊበላም በዚያው አግረ መንገዱን አዳዲ በተባለች ቦታ ላይ ከቋጥኝ ድንጊያ ላይ ፈልፍሎ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሠርቷል፣ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያኗን ባርከው ታቦቷን ከአስገቡ በኋላ ንጉሡን አፄ ላሊበላን ከቦታህ ታላቅ እንግዳ ስለሚፈልግህ ወደ ቦታህ በአስቸኳይ ተመለስ ብለው ነገሩት።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ይህን ለንጉሡ የነገሩት የንጉሡ የአፄ ላሊበላ ዕረፍት ተገልጾላቸው ስለነበር ነው፣ ንጉሡ አፄ ላሊበላም ብዙ ቀን ሳይቆይ በ፩ሺ፩፻፷፬ ዓ.ም ሰኔ ፲፪ ቀን ዐርፎ በሮሀ ቤተ መቅደስ በጎልጎታ ውስጥ ተቀብሯል። ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በዝቋላ ተራራ ላይ በታላቅ ተጋድሎ ተጸምደው በጾም፣ በጸሎትና በትሩፋት በትህርምት ተወስነው ፈጣሪያቸውን ደጅ ሲጠኑ ብዙ ሰዎች በክፉ ኃጢአታቸው ምክንያት በነፍሳቸው መጐዳታቸው ተገልጾላቸው ዝቋላ ተራራ ላይ በሚገኘው ጥልቅ ባሕር ውስጥ ገብተው ይጸልዩ ጀመር።

ጻድቁ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በዚያ ጥልቅ ባሕር ውስጥ ሆነው መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማርልኝ እያሉ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ሲጸልዩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጾ ስምህን ጠርቶ በስምህ የለመነኝን እምርልሃለሁ፣ ከባሕር ውጣ የሚል ቃል መጣላቸው።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በስምህ የመነኑትን ሁሉ ካልማርክልኝ ከባሕር አልወጣም ብለው አንድ መቶ ዓመትሙሉ በባሕር ውስጥ ሆነው እየጸለዩ ኢጋንንትን ድል ከአደረጉ በኋላ ጥቅምት ፭ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕሩ ተገልጾ በስሜ ያመኑትን በሰጠሁህ ቃል ኪዳን የተማጸኑትን ሁሉ ለአንተ አሥራት አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ከባሕሩ ውጣ አላቸው፣ ጻድቁ ፈጣሪያቸው ኢየሱስ ክርስቶስን እያመሰገኑ ከባሕሩ ወጥተዋል።

ከዚያም በኋላ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ ከብድ ሄደው እጆቻቸውን ዘርግተው ቢጸልዩ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል ተገልጸው አጋንንትን ድል በምታደርግበት ወደ ዝቋላ ሂድ ብለው ስለነገሩአቸው ጻድቁ ወደ ዝቋላ ለመሄድ ወንበር ማርያም ሲደርሱ ሦስት ሽማግሌዎች ከዛፍ ሥር ተቀምጠው አገኙአቸው። እነዚህን ሦስት ሽማግሌዎች አዘለንና ይህን አቀበት አውጣን አሉአቸው፣ ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስም በየተራ ሦስቱንም ለማውጣት አስበው ከሦስቱ አንዱን አዝለው ቢያወጡ ሦስቱም ወጥተው ተገኝተዋል።

ሦስቱ ሽማግሌዎችም የደብረ ታቦር አምሳል በሆነች በዝቋል ተራራ ላይ በመገኘት እግዚአብሔር ራሱ ለአባታችን ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አንድነቱንና ሦስትነቱን ገልጿል። ዝቋላ የደብረ ታቦር አምሳል ናት የምትባለውም ስለ ዚሁ ነው።

ጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድረ ከብድ ተመልሰው ፫ ነምሮችና ፫ አንበሶች እየሰገዱላቸው ይኖሩ ነበር፣ እነዚያም አራዊት የጻድቁን የእግር ትቢያ እየተመገቡ ይኖሩ ነበር፣ ታላቁ ጻድቅ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በምድረ ግብፅ ፭፻ በኢትዮጵያ ፭፻፷፪ በጠቅላላ ፩ሺ፷፪ ዓ.ም በታላቅ ተጋድሎ ተጸምደው ከኖሩ በኋላ መጋቢት ፭ ቀን በሰላመ እግዚአብሔር ዐርፈዋል።

የጻድቁ አባታችን በረከትና ረድኤት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን። ❖

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ


www.ethiopianorthodox.org

# ዘመነ ማርቆስ

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች የሆነችውን ወንጌል የጻፉት አራት ሲሆኑ ሁለቱ ከሐዋርያት ሁለቱ ከሰብአ አርድእት ናቸው። ከሐዋርያት ወገን ዮሐንስና ማቴዎስ ሲሆኑ ከሰብአ አርድእት ደግሞ ሉቃስና ማርቆስ መሆናቸው የታወቀ ነው። የእያንዳንዳቸውም የቅፅል ስም አላቸው፤ ዘብእሲ ማቴዎስ፣ ዘአንበሳ ማርቆስ፣ ዘላህም ሉቃስ፣ ዘንስር ዮሐንስ ነው። የቅፅል ስማቸውንም መተርጕማን መጻሕፍት ሊቃውንት እንደሚከተለው ያብራሩታል።

ማቴዎስ ወልደ ዳዊት ወልደ አብርሃም የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ እያለ ሰው ስለመሆኑ ስለጻፈ ዘብእሲ ማቴዎስ ተብሏል። ማርቆስም ወንጌልን ለማስተማር ወደ ምድረ ግብፅ ተልኮ በትምህርቱ በተአምራቱ ጣዖታቱ ተሰባብረው እንዲወድቁ የወንጌል ቃል በሰፊው እንዲሰበክ ስላደረገ አንበሳ የሚለውን ቅጽል አግኝቷል።

ሉቃስም አምዕኡ መግዝአ ላህም ንዑ ንጥብሖ ወንትፌሣህ ቡቱ በማለት ስለዓለም መሥዋዕት ሆኖ መቅረቡን ስለሚጽፍ ዘላህም ተብሏል። ዮሐንስም ከሌሎቹ ወንጌላውያን ለየት ብሎ ቀዳሚሁ ቃል በማለት በምሥጢረ ሥላሴ ጀምሮ በመጻፍ ዘንስር ተብሏል፤ ንስር ወደ ላይ ወጥቶ ወደ ታች የተመለከተ እንደሆነ ከምድር ላይ የወደቀች የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል ሥጋ እንኳን ብትሆን አይሠወረውም አንስቶ ይመገባል፤ እርሱም ተራቆ በመጻፉ ዘንስር ዮሐንስ ተብሏል።

የአራቱም ወንጌላውያን የየራሳቸው ታሪክ አላቸው፤ በአራቱ ወንጌላዊያን አዝማናት ሲለዋወጡና ሲዘዋወሩ ይኖራሉ፤ በዚሁም መሠረት በ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ዘመነ ማርቆስ ነው ስንል ማረጋገጫ አለው፤ ሰባት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ስምንት ዓመተ ምሕረት ወይም ፯ሺህ፬፻፺፰÷፬ =፩ሺህ፰፻፸፬ ይደርስና ፪ (ሁለት) ይተርፋል፤ አንድ ሲተርፍ ማቴዎስ፣ ሁለት ሲተርፍ ማርቆስ፣ ሦስት ሲተርፍ ሉቃስ፣ አራት ሲተርፍ ዮሐንስ ይባላል።

በዘንድሮው ግን ሁለት ሲተርፍ ፲፱፻፺፰ ዘመነ ማርቆስ እንላለን፤ ፪ተኛ ዘመን መለወጫ ቅዱስ ዮሐንስ እሑድ ቀን ስለመዋሉ ማረጋገጫ አለው። አጽፈ አውራኅ ፪ ጥንተ ኦን ፭ ማለት ፭+፪+፩= ፰-፯=፩ እሑድ ቀን ስለመዋሉ ይህ ማረጋገጫ ነው።

ቅዱስ ማርቆስ የተወለደው በኢየሩሳሌም ነው፤ የመጀመሪያ ስሙ ዮሐንስ ነው፤ የአባቱ ስም አርስጣሉ የእናቱ ስም ማርያም ትባላለች። ቊጥሯ ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ነው፤ ሐዋርያት በቤቷ እየተሰበሰቡ ስለስብከተ ወንጌል ይነጋገሩ ነበር፤ መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን እንደሚያፈራ ከእርሷ ሐዋርያው ማርቆስ ተገኝቷል፤ የአባቱና የእናቱ ሀገረ ትውልዳቸውም ከቤተ እስራኤል ነው፤ ሲጋቡም በሕገ ኦሪት ሥነ ሥርዓት ነው፤ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት በሚለው ትእዛዝ ጸንተው ሕገ እግዚአብሔርን ጠብቀው በጾም በጸሎት ተወስነው ዘወትር ለድሆች ምጽዋት በመስጠት ሳሉ እግዚአብሔር የተባረከ የሃይማኖት አባት የሆነ ልጅ ሰጣቸው፤ ይህም በነቢዩ በዳዊት ዘሩ በምድር ይባረካል መዝ.፩፻፲፩ ተብሎ ተናግሯልና።

ቅዱስ ማርቆስ የጸና ስለነበር መጻሕፍተ ብሉያትን ከመማሩም ከጌታም ወንጌልን ተምሯል፤ በተማረውም መሠረት የጌታችን የኢየሱስን ወ/ጌል የጻፈው በሮማ ይስጥ ቋንቋ ነው፤ ይህም ጌታ ባረገ በአሥራ አንደኛው ዓመት ተፈጽሞ አሥራ ሁለተኛው ሲጀመር ገላውዴዎስ ቄሳር በነገሠ በአራተኛው ክፍለ ዘመን ነው።

ቅዱስ ማርቆስ ከሰባ ሁለቱ አርድእት አንዱ ነው፤ ሐዋርያት ወደ ስብከት በሚሠማሩበት ጊዜ ቅዱስ ማርቆስ በዕጣ ግብፅ ሲደርሰው እስክንድርያ ገብቶ እየተዘዋወረ በእየአውራጃው አስተማረ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሆነ ያሰበው ሁሉ ይቃናለት ነበር። ቅዱስ ማርቆስ በአንበሳ ይመሰላል፤ አንበሳ ኑሮው ከሰው ርቆ በምድረ በዳ ነው፤ ቅዱስ ማርቆስ በግብፅ ወንጌልን ሲሰብክ ቀዳሚሁ ለወንጌለ እግዚእን ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ ባስተማራቸው ጊዜ ምእመናን በደስታ ተቀብለውታል፤ አጋንንት ግን መናፍቃን ከቃሉ አነጋገር የተነሣ ተገስጸው ከሰው ልቡና እየወጡ ይሄዳሉ፤ ቀድሞ ነቢያት ሙሴ፣ አሮን፣ ኤርምያስም ቢያስተምሯቸው አልተቀበሉም፤ ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር እንዳለው ነቢዩ ዳዊት ለግብፅ ሰዎች ፈጽሞ ድኅነታቸው በታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ማርቆስ ስለሆነ በስብከቱ አምነዋል፤ በረከት አግኝተዋል፤ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያደረገውን ፍቅር ሲሰብክ ያዩ ሁሉ ያመኑትም ያላመኑትም በሚያስደንቅ ሁኔታ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየጎረፉ ይገቡ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ማርቆስ ዓለማትን ሁሉ በፈጠረ በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እመኑ፣ ከንቱ ለሆነ ጣዖት አትስገዱ ብሎ እያስተማረ ይሰብክ ጀመር፤ ሰይጣን ልቡናቸውን ያሳወራቸው ሰዎች አምልኮት በየቦታውና በመንገዱ የጣዖት ቤት እየሠሩ ምስል እያቆሙ ሕፃናቱን እንገታቸውን ጠምዝዘው በመግደል በደሙ እየተቀቡ ሳሉ አስማተኞችን መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን አትመኑ ሲል አስተማረ። ቅዱስ ማርቆስ ሕገ ወንጌልን ለማስተማር ለተመረጠበት ሥራ ሁሉ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ጠቅላላ በግብፅ እስክንድርያ ለብዙ ዘመን የነበረውን አምልኮ ጣዖት የላም ምስል አቁመው ሲሰግዱ ስለነበር ሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ ለላም እንዳይሰግዱ አስተምሮ ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ እንዲመለሱ አድርጓል።

ቅዱስ ማርቆስ ያስተማረው በእስክንድርያ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን ሕገ ወንጌል ትምህርት ያስተማረው በእስያ በሩቅ ምሥራቅ በተለይም በርቃ ተብሎ በሚጠራው አገር በአፍሪካ ምድር ከሐዋርያት ጋር በሮም ሲሰብክ እግዚአብሔር ፈጣሪ መሆኑን ግልጽ አድርጎ በማስተማሩ ሕዝቡ እጅግ ከደስታ የተነሣ ቅዱስ ማርቆስን መንፈሳዊ አባት መሆኑን አመኑ።

ሲሰብክም ልዩ ተአምራት ይደረግ ነበር፤ በጽኑ ደዌ ቁራኛ በአጋንንት አሽክላ የታሠሩት ሁሉ መዳናቸውን ያየው ሕዝብ ሁሉ በማድነቅ ይከተለው ነበር፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለጸሎት ያመነውም ያላመነውም ሁሉ ይጎርፍ ነበር፤ ከዚህ በኋላ ያላመኑት በቅናት እየጎተቱ ከአሳት ውስጥ አገቡት፣ እሳቱንም ዝናም መጥቶ አጠፋባቸው እንደገና አንገቱን በገመድ አስረው እየጎተቱ በምድር ላይ ደሙ ይጎርፍ ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ ወንጌልን እየመሰከረ በብዙ ሕዝብ መካከል የሥጋ መከራና ጭንቀት ሞትን ሳይፈራ በመጨከኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕለት ዕለት እየተገለጸ ይታያው ነበር፤ ያጽናናውም ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ ከ፬ ወንጌላዊያን ሁለተኛውን በዘመን ይዞ ይገኛል። ሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ የሃይማኖት አባት የሆነው በግብፅ፣ በእስክንድርያ፣ በኢትዮጵያ ወዘተ. በዚሁ መሠረት በዓለም ያሉት ክርስቲያኖች ሁሉ የታወቀውን የማርቆስ ወንበር ወይም ሹመት በየዘመኑ ዘወትር ሲነገር ይኖራል። ይህም ሹመት በየዘመኑ ለሚነሡት ሁሉ ጳጳሳት የሃይማኖት መመኪያ ክብር የሆነው ቅዱስ ማርቆስ ነው፤ ቅዱስ ማርቆስ የክርስቶስን ወንጌል እየሰበከ እየመሰከረ መከራ ሞትን ሳይፈራ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል መሠረት በማድረግ ሥጋንም የሚገሉትን አትፍሩ ነፍሳችሁን መግደል አይችሉምና ማቴ.፲፥፳፰ የቅዱስ ማርቆስ እረፍቱ ሚያዝያ ፴ ቀን ስለሆነ በየዓመቱ በአገራችን በኢትዮጵያ በሌሎችም ሲከበር ይኖራል።

ሁላችንም ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ እንኳን አሸጋገረን፤ ዘመኑን የሰላም፣ የጤናና የሥራ ያድርግልን። ✦

ሊቀ ካህናት ተሾመ ወ/ሐና

## ድንግል ማርያም...

ከገጽ ፲፰ የዞረ

ርጉም ሄሮድስ በዘመኑ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምንና ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ከቤተ ልሔምና ከገሊላ እንዳሰደደ ሁሉ በአሁኑ ጊዜም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብርና አምላጅነት ምእመናን የሚያስክዱ የመጡ እምነት ቅጥረኞች ስፍር ቁጥር የላቸውም፤ ከእነዚህ መናፍቃን ከንቱ ስብከትና ሐሰተኛ ትምህርት ምእመናንን መጠበቅ ይገባል።

አማናዊቷና ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምንና የተወደደው የልጇን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የስደት መታሰቢያ በወርኃ ጥቅምት በማኅሌትና በምሥጋና ታስባለች።

ወርኃ ጥቅምት አበቦች ደምቀውና ፈክተው የሚታዩበት ጊዜ ነው፤ አበቦች የፍጹም ደስታና የዕርካታ ምንጮችም በመሆናቸው የደስታ የበረከት መሠረት የሆነችውን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የኢትዮጵያ ካህናትና ምእመናን በሚአስደስት አበባ እየመሰሉ ያመሰግኗታል።

በወርኃ ጽጌ በጥቅምት ወር በየአብያተ ክርስቲያናቱ በዕለተ ሰንበት የሚደረገው ያሬዳዊ ማኅሌትና ወረብ የእመቤታችን ስደት የሚአወሳ ቀለም ሲሆን ልዩ የሆነ ጣዕመ ዜማ አለው።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነት የእመቤታችን በረከትና አማላጅነት በሁላችን ላይ ይደር አሜን።✦

መሪጌታ ኤፍሬም በየነ

# ድንግል ማርያም በምድረ ግብፅ

በአራት በነቢያት በተነገረው ትንቢት በተቆጠረው ሱባኤ መሠረት ቃለ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለዱ ሰብአ ሰገል ከሩቅ ምሥራቅ በኮከብ እየተመሩ መጥተው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ወርቅ፣ ዕጣንና ከርቤ ገበሩለት።

በዚያን ጊዜ ሄሮድስ ጌታ የተወለደባት የቤተ ልሔምና የገሊላ ገዥ ስለነበር በአገሩ ንጉሥ እንደተወለደ በመስማቱ የቤተ ልሔምንና የገሊላን ሕፃናት ለማስገደል ፈለገ፤ የእግዚአብሔር መልአክም በሕልም ለዮሴፍ ተገልጾ ተንሥእ ንሣእ ሕፃነ ወእሞ ወሑር ብሔረ ግብዕ እናትና ልጁን ይዘህ ወደ ምድረ ግብዕ ሂድ፤ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልጋልና እስከ ምነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ ብሎ በነገረው ጊዜ ቅዱስ ዮሴፍ በቤተ ልሔም አልዋለም አላደረም ዕለቱን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አስከትሎ ሕፃኑን ይዞ ወደ ግብዕ በስደት ሄደ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድረ ግብዕ የተሰደደው ከሄሮድስ እጅ ለማምለጥና ያለ ጊዜው የሚሞት ሁኖ አይደለም፤ በትንቢተ ነቢያት ጸዋዕክዎ እምግብዕ ለወልድየ ልጄን ከግብዕ ጠራሁት ሆሴዕ ፲፩፥፩ ተብሎ በነቢዩ ሆሴዕ በተነገረውና በነቢዩ በኢሳይያስ «ወይወርድ እግዚእ ውስተ ምድረ ግብዕ እንዘ ይጼእን ዲበ ደመና ብሩህ ጌታችን በብሩህ ደመና ተጭኖ ወደ ምድረ ግብዕ ይወርዳል» ኢሳ. ፲፱፥፩-፬ ተብሎ የተነገረው ይፈጸም ዘንድ ነው።

ጌታ ወደ ምድረ ግብዕ የሄደው ገዳማተ ግብዕን ለመባረክ ታላላቅ ገዳማት እነሲሐት እነ አስቄጥ የሚገኙ በግብዕ ነውና እንዲሁም አዳም አባታችን ከዓለም አፍአ ከምትሆን ከገነት ተባሮ ነበርና ለዚያ ካሣ እንደሆነ ለማጠየቅ ለሰማዕታትም ስደትን ለመባረክ ነው። ለማዕትነት በእሳት መጠበስ፣ በሰለት መቆረጥ ብቻ ሳይሆን በሃይማኖት ምክንያት አገር ጥሎ መሰደድ ሰማዕትነት ነውና፤ ጉየተ ሕፃን አጕየዮ ለዲያብሎስ የሕፃኑ ወደ ግብዕ መሸሽ በግብዕ ጣዖታት አድሮ ያስት የነበረው ሰይጣን ተባረረ ተብሎ እንደተጻፈው አጋንንትን ከሰው ልቡና አስወጥቶ ለማበረር ተሰደደ በማለት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይተረጉማሉ።



ቅዱስ ዮሴፍ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ተከትሎ ስንቋን ይዞ ሕፃኑ ክርስቶስን ተሸክሞ ወደ ምድረ ግብዕ በተሰደደ ጊዜ በነገረ ማርያም እንደተጻፈው የ፺፱ ዓመት ሽማግሌ ነበር፤ ሽማግሌው ቅዱስ ዮሴፍ ጉልበቱ በደከመበት፣ ክንዱ በዛለበት፣ ጧሪ ቀባሪ በሚፈልግበት በዚያ የሽምግልና ዘመን ስደትን ያህል መራራ ነገር በመቀበል ፈጣሪውን ኢየሱስ ክርስቶስንና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እንዲያገለግል በእግዚአብሔር መልአክ ሲታዘዝ በሌሊት ነበር ተነሥቶ ወደ ምድረ ግብጽ የተሰደደው ማቴ. ፪፥፲፫

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከፈጣሪዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በምድረ ግብጽ ፫ ዓመት ከመንፈቅ በስደት ተቀምጣለች፤ በስደቷም ወቅት ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣችና ኢትዮጵያም የአሥራት ሀገር ሁና እንደተሰጠቻት በድርሳነ ዑራኤል ተጽፎአል፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ኢትዮጵያ የመጣችውም በጥቅምት ወር ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድረ ግብዕ ሲሰደድ በቤተ ልሔምና በገሊላ የነበሩ ዕድሜአቸው ከሁለት ዓመት በታች የነበሩትን ሕፃናት ልብስ ቀለብ እሰጣለሁ በማለት አታሎ ከሰበሰበ በኋላ ከዐሥራ አራት እልፍ በላይ ሕፃናትን በጭካኔ አስገድሏል፤ ማቴ.፪፥፲፮-፲፰ እነዚህ ሄሮድስ በጭካኔ የፈጃቸው የቤተልሔምና የገሊላ ሕፃናት በእግዚአብሔር ክብር እንዳሉ ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእዩ ሲገልጽ «በጽዮን ተራራ ላይ ቆሞ አየሁ ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም በግንባራቸው የተጻፈባቸው አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ፤ በማለት ገልጿቸዋል። ጌታን ያገኘሁ መስሎት እነዚህ ሄሮድስ የፈጃቸው ሕፃናት ሰማዕታት ናቸው። በአሁኑ ጊዜም በአርባ ቀን በሰማንያ ቀን የተጠመቁትን ሕፃናት እንደ ሄሮድስ ልብስ ቀለብ እንሰጣለን እያሉ በማታለል እውነተኛዋን ሃይማኖት የሚያስክዱ ወደ ሐሰተኛው እምነት የሚወስዱ የመጤ እምነት አራማጆች ሄሮድሳውያን መናፍቃን ዛሬም በዘመናችን አሉ።

ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል



# አቡነ አረጋዊ

አቡነ አረጋዊ በ፬፻፶፱ ዓ.ም ጥር ፴ ቀን ተወለዱ፤ እኒህ ታላቅ ጻድቅ ሀገራቸው ሮም ሲሆን አባታቸው ይስሐቅ እናታቸው እድና ይባላሉ፤ የእነዚህ ጻድቅ ስመ ክርስትናቸው ገብረ አምላክ ተብሎ ተሰየመ፤ ወላጆቻቸውም የሥጋ ብቻ ሳይሆን የመንፈስም ባለፀጎች ነበሩ፤ እኒህ ሕፃን ከተወለዱበት ጀምሮ የሕፃንነታቸው ወራት እስከ ተፈጸመበት ጊዜ በምግብ እየተንከባከቡ በቁመት ብቻ እንዲያድጉ ሳይሆን በመንፈስ፣ በትምህርትና በሥነ ሥርዓት አሳደጉአቸው።

አቡነ አረጋዊም ይህ ሁሉ እየተፈጸመላቸው ስላደጉ ለሥጋዊ ኑሮ ከማሰብ ይልቅ ለመንፈሳዊ ኑሮ ማሰብ፣ በመንፈሳዊ ሕይወት መመራት፣ በሥጋ መንገድ ከመሄድ ይልቅ መንፈሳዊውን መንገድ መከተል ደስ ይላቸው ጀምር፤ ዓላማቸውም ይህ ሲሆን የወላጆቻቸው ዕቅድ ደግሞ የመንግሥትን ሥነ ሥርዓትና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አጥንተው ከጨረሱ በኋላ ሚስት አግብተው፣ ልጅ ወልደው፣ በአባቱ እግር ተተክቶ፣ የአባቱን ሥልጣን ይዞ፣ ሁብታችንን ንብረታችንን ወርሶ፣ ስማችንን ያስጠራል የሚል ነበር። ግንቦት 14 ቀን አቡነ አረጋዊ ከወላጆቻቸው ጋር ቤተ ክርስቲያን ሄደው ሳለ አንዱ ካህን የማርቆስ ወንጌል ምዕ. ፰፥፴፬-፴፮ ያለውን «በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢገዛ ነፍሱን ካጣ ምን ይጠቅመዋል?» እያለ ሲያስተምር ሰሙ።

በዚያው ወደ ቤታቸው ሳይመለሱ የክብርና የማዕረግ ልብሳቸውን በተቀዳደደና በአሮጌ ልብስ ለውጠው መስቀሉን ተሸክመው ክርስቶስን ለመከተል ወደ ምድረ ግብዕ ሄዱ፤ በዚያ በሚገኘው በታላቁ በአስቄጥስ ገዳም ሥርዓተ ምንኵስናን እየተከታተሉ በጾምና በጸሎት ሰውነታቸውን እየፈተኑ ይኖሩ ጀመር።

ከዚህ በኋላ ከአባ ጳኵሚስ የምንኵስና ማዕርግ ተቀብለው ስማቸው ዘሚካኤል ተባለ፤ ልብሰ ምንኵስና ከለበሱ በኋላ ጾምንና ጸሎትን፣ ስግደትንና አገልግሎትን እየጨመሩ ሄዱ። ስለ ክርስቶስ ፍቅር ዓለምን ወደ ኋላቸው ትተው ገና በወጣትነታቸው ወራት መመንኮሳቸውን የሰሙ ቅዱሳን ሁሉ ወደ እርሳቸው እየመጡ በረከትን ይቀበሉ ጀመር፤ ወደ እሳቸው የመጡት ቅዱሳንም በትምህርት አሰጣጣቸው፣ በምክር አቀራረባቸውና በዕውቀታቸው በልጽገው ስላገኙዋቸው «በዕድሜ ከእኛ ያነስክ ሕፃን ስትሆን በዕውቀት ግን ከእኛ በላይ ሆነህ ስላገኘንህ አረጋዊ ብለንሃል» ስላሉዋቸው ስማቸው አረጋዊ ተባለ።

አቡነ አረጋዊም በዚሁ ገዳም ረዘም ላለ ጊዜ ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ወደ ሀገራቸው ወደ ሮም ተመለሱ፤ ከዚያም ለጥቂት ጊዜ ወንጌል ሲሰብኩ ከቆዩ በኋላ በኬልቄዶን ጉባኤ በተነሣው የሃይማኖት ክርክር ምክንያት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች በየሀገሩ ሲሰደዱ እሳቸውም የዚህ ዕድል ደርሶአቸው በሃይማኖት ምክንያት ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ የሚሉ አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ኢትዮጵያ የክርስትና ደሴት ስለሆነች ወንጌልን ለማስተማርና እግረ መንገዳቸውንም አክሱም ጽዮንን ለመሳለም ነው የመጡት የሚሉም አሉ።

በዚያም ሆነ በዚህ ለመጀመሪያው ጊዜ በ፬፻፹ ዓ.ም አክሱም ጽዮን እንደገቡ የራሳቸው ገድል ይናገራል፤ ክብረ ነገሥትም ይተርካል፤ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው አክሱም የተቀመጡበት በአጼ አልዓሜዳ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ነው። የእሳቸውንም አክሱም መቀመጥ የሰሙ ስምንቱ ቅዱሳን በየጊዜው እየመጡ ከርሳቸው ጋር ተገናኙ።

እኒህም ቅዱሳን የወንጌል መምህራን አቡነ አረጋዊን የበላይ አስተዳዳሪ እንዲሆኑ መርጠው ሥራ ጀመሩ የመጀመሪያም ሥራ ያደረጉት የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም ነበር። የኢትዮጵያንም ሊቃውንት ሰብስበው እየተመካከሩ ብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ወደ ግእዝ፣ አዲስ ኪዳንን ከጽርዕ ወደ ግእዝ ተርጕመው ጽፈው ከጨረሱ በኋላ ተቀማጭ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን አስረከቡ፤ ይህንን ፈጽመው ሀገረ ስብከታቸውን ተከፋፍለው ወንጌልን ለማስተማርና የክርስትናን እምነት ለማስፋፋት በየቦታው ተሰማሩ።

ለአቡነ አረጋዊም የብዙት ወረዳ ደረሳቸው፤ ይህም የሚገኘው በትግራይ ሀገረ ስብከት በአድዋ አውራጃ ነው፤ ይህም ሥፍራ አድዋንና አዲግራትን በሚያገናኘው አውራ ጎዳና አቅራቢያ ይገኛል። ሌሎቹ ወደየሀገረ ስብከታቸው ሲሄዱ አቡነ አረጋዊ ግን ቅዱስ ያሬድን አስከትለው በኢትዮጵያ አውራጃዎች ለማስተማር ሄዱ፤ ያስተማሩባቸውም አውራጃዎች በጣና ደሴትና በዙር አንባ እኒህንና እነዚህን በመሳሰሉት እየተዘዋወሩ ቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ በማዜም እሳቸው ወንጌል በመስበክ ቅዱስ ቃሉን ተጠምቶ የነበረውን ሕዝብ በትምህርት እንደ



www.ethiopianorthodox.org

መስና ውኃ እያጠጡ ከጥሙ አረ ኩት፤ የሚገባ የመንፈስ ፍሬም እንዲያፈራ አደረጉት፤ በዚህ ጊዜ ምእመናን እየበዙ፣ ወንጌል እየተ ስፋፋ፣ ቤተ ክርስቲያን የአስተዳ ደር ዕድገት እያገኘች ከመሄዷ የተ ነሣ አምልኮ ጣዖት ሊጠፋ ችሏል።

እኒህ ጻድቅ በኢትዮጵያ ተዘ ዋውረው ወንጌልን ካስተማሩ በኋላ በደብረ ዳሞ ተራራ ወጥተው ሱባኤ ለመያዝ አሰቡ። በየጊዜው የሚጠ ብቃቸውና ለችግራቸው ሁሉ ከእ ግዚአብሔር እየተላከ የሚረዳቸው ቅዱስ ሚካኤል መጥቶ በራእይ የሚከተለውን እንደ ነገራቸው ከገ ድላቸው ማንበብ ይቻላል። ሱባኤ የገቡበት ዋናው ምክንያት ኃይል አግኝተው ወደ ተራራው ወጥተው እግዚአብሔርን ለማገልገልና በአን ባው ላይ ለሕዝብ ጥቅም ለእግ ዚአብሔር ክብር የሚሆን ታላቅ ሥራ ለመሥራት ነበር። መል አኩም በራእይ የነገራቸው ቃል የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆን ከው አረጋዊ ጻድቅ «አይዞህ አት ፍራ ጸሎትህ ስለተሰማ ከኃይል ወደ ኃይል ትሄዳለህ፤ ታላቅ ሥል ጣን ተሰጥቶሃልና ጽና ታገስ፤ አባቦችን ይይዛሉ የሚገድል ነገር ቢጠጡ አይጐዳቸውም ሲል ክር ስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ባለው መሠረት አንተንም ስለማይጐዳ ወደ ተመኘኸው ተራራ እንዲያወ ጣህ በቀኝ በኩል በገመድ ፈንታ እግዚአብሔር አንድ ትልቅ ዘንዶ ይልክልሃል፤ እርሱም ወደ ፈለግ ኸው ተራራ ወስዶ ያደርስሃል፤ እግ ዚአብሔር ከአንተ ጋር ስለሆነ በዘ ንዶው ላይ ተቀምጦ መሄድን አት ፍራ» አላቸው፤ ቁመቱም ስልሳ ክንድ ሲሆን ውፍረቱም አንድ ክንድ ነው ይላል ገድላቸው።

እንደተባለውም ጻድቁ ሁኔታ ውን ሲጠባበቁ ሳለ ያ ዘንዶ እየተ ወረወረ ከተራራው ወርዶ ከአቡነ


አቡነ አረጋዊ

አረጋዊ ፊት ቆመ፤ አቡነ አረጋ ዊም የእግዚአብሔርን ስም እየ ጠሩ ሦስት ጊዜ በመስቀላቸው ካማ ተቡ በኋላ ዘንዶው ላይ ተቀመጡ፤ ዘንዶውም ተራራ ላይ አውጥቶ ካስቀመጣቸው በኋላ ወደመጣበት ተመለሰ። አቡነ አረጋዊም ከተራ ራው ራስ ላይ ወጥተው ከሜዳው ላይ እንደደረሱ ሦስት ጊዜ ከሰገዱ በኋላ ሃሌ ሉያ ለአብ፣ ሃሌ ሉያ ለወልድ፣ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ እያሉ አመሰገኑ። ትርጓሜውም ቅድመ ዓለም የነበርክ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ጸሎቴን ሰም ተህ ፍላጎቴን ስለፈጸምክልኝ ክብር ምስጋና ለአንተ ይገባል ሲሉ አመ ሰገኑ።

ስለዚህ ደብረ ዳሞ የተባለው ገዳም «ደብረ ሃሌ ሉያ» የሚል የክ ብር መጠሪያ ስም ተሰጠው። በዘ መናቸው የነበሩት ንጉሡ አፄ ገብረ መስቀልም የአቡነ አረጋዊ ሥራ ቸውና ሁኔታቸው ስላስደነቃቸው መጀመሪያ ተራራውን ተዘዋው ረው ጎብኘት አደረጉ፤ ይዞታውም ስለ አስደሰታቸው በዚህ ተራራ ላይ የአክሱምን ጥንታዊ ቤተ ክር ስቲያን የሚመስል አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ታቦት እን ዲገባ አደረጉ፤ ለመነኮሳቱና ለካህ

ናቱ መተዳደሪያ የሚሆን መሬት ለመጀመሪያ ለገዳሙ ሰጡ፤ ለቤተ ክርስቲያኑም መገልገያ የሚሆን ሙሉ ንዋያተ ቅድሳት አበረከቱ።

ጻድቁ አቡነ አረጋዊም ከወን ድሞቻቸው ከስምንቱ ጋር ሆነው ወደ አንባው የሚያወጣና የሚያ ወርድ ዘንዶ መሰል የቆዳ ገመድ ጉንጉነው ከአንባው ከሚገኘው ትልቅ ወይራ ላይ አቆራኙት፤ ይህም እስከ ዘመናችን ድረስ ሲሠ ራበት ይኖራል፤ በዚህ ዘንዶ መሰል ቆዳ ጉንጉን ገመድ ምእመ ናን እየወጡ ትምህርትና ቡራኬ ይቀበሉ ጀመር፤ ቅዱስ ያሬድም ከአክሱም ጽዮን መጥቶ በጉንጉን ገመድ ወደ ተራራው ወጥቶ ከአ ቡነ አረጋዊ ጋር ተገናኝቶ ቡራኬ ተቀበለ።

አፄ ገብረ መስቀል ያሠሩላቸ ውን ቤተ መቅደስ ሥራ ተመል ክቶ «ይሄውጽዋ መላእክት እንተ በሰማያት እስመ ማኅደረ መለኮት ይእቲ ያድክዋ ያድክዎ ያድክዎ ወርኢኩ ሥነ ሕንጼሃ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምስዓል ወምስ ጋድ ወምሥትሥራዩ ኃጢአት ይእቲ ቅድስት ደብተራ» ትርጓሜው በሰ ማያት ያሉ መላእክት ይጎበኙዋ ታል እርሷ የመለኮት ማደሪያ ናት፤ እኔም ዞርኩ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሕንጻ ውበት ተመ ለከቼ አደነቅሁ ብሎ ዘምሮ ወደ አክሱም ተመልሷል።

የጻድቁ አቡነ አረጋዊ ተግባር ይህ ብቻ አልነበረም፤ የውኃ ማጠ ራቀሚያ ከአራት ቦታ ተፈልፍ ለው የማያቋርጥ ውኃ እንዲመ ነጭ አድርገዋል። በየጊዜው ብዙ መነኮሳትንና ባሕታውያንን በትም ህርታቸው እየሳቡ የአንድነትም ገዳም መሥርተዋል።

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



# ክረምት እንዴት ሰለፈ?

የዘመናት ባለቤት ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር እም ላክ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ዘመ ናትን በመለዋወጥ ክረምትንና በጋን በማምጣት፣ ቀንና ሌሊትን በማፈራረቅ ፍጥረቱን ሁሉ ሲመ ግብ የኖረ የሚኖር እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን በሥነ ፍጥረቱ ሁሉ የታመነና የታወቀ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ መል እክቱ ምዕ. ፩፣፲፱-፳፩ እግዚአብ ሔር ስለገለጠላቸው ስለ እግዚአ ብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነ ርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና የማይ ታይ ባህርይ እርሱም የዘለዓለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓ ለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጽ ሆኖ ይታያል በማ ለት አስተምሯል።

ነቢዩ ዳዊትም ቀኑ የአንተ ነው፣ ሌሊቱም የአንተ ነው፣ አንተ ፀሐ ዩንና ጨረቃውን አዘጋጀህ፣ አንተ የምድርን ዳርቻ ሁሉ ሠራህ፣ በጋ ንም ክረምትንም አደረግህ። ይህን ፍጥረትህን አስብ በማለት እግዚአ ብሔርን ሲያመሰግን እኛም እንደ ዳዊት የፍጥረት ሁሉ ጌታ እግዚ አብሔርን እንድናመሰግን ያስተም ረናል። መዝ. ፸፫፣፲፮-፲፯

በመጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት ዘፍጥረት ተጽፎ እንደምናገኘው ከአዳም ከመጀመሪያው ፍጥረት አሥረኛው ትውልድ በሆነ በኖኅ ዘመን የሰው ልጆች ሁሉ በጋንና ክረምትን እያፈራረቀ የሚመግባቸ ውን ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን በመርሳት ለእግዚአብሔር የሚገባ ውን ምስጋና አስራት በኩራት ባለ ማቅረባቸው የእግዚአብሔርን ትእ

ዛዝ አባትህንና እናትህን አክብር፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስ ረቅ፣ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር፣ የባልንጀራህን ቤት አትመኝ የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ በመተላለፍ እንደ አሁኑ ዘመን ዝሙትን በማብዛት ያለ ሕግ ሴቶችን እየመረጡ በማግባት ምድርን በኃጢአታቸው አረከሷት ዘፍ. ፮፣፩-፭፣ ዘጸ. ፳፣፲፪-፲፯፣ ዘጸ. ፳፣፭-፳፪

እግዚአብሔር አምላክም እን ዲያመሰግኑትና በትእዛዙ እንዲ ሄዱ የፈጠራቸውን የሰው ልጆች በሥራቸው ስለአስቆጡት በእግዚ አብሔር ትእዛዝ ከሚሄድ ከጻድቁ ከኖኅና ከነቤተሰቡ በስተቀር እግ ዚአብሔርን የሚፈራ፣ በእግዚአ ብሔር ትእዛዝ የሚሄድ ሰው ስላ ልተገኘ ከሰማይ በታች ከሰው እስከ እንስሳት ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ ለአርባ ቀንና ሌሊት በምድር ላይ በዘነበው ዝናብ ጠፉ ተደ መሰሱ፤ ዘፍ. ፯፣፳፩-፳፪ ጻድቁ ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሦስት ፎቅ ያላት መርከብ ሠርቶ ከነቤተሰቡና ለዘር ከቀሩት እንስ ሳት ጋር በመርከቢ ውስጥ ገብቶ በጥፋት ውኃ ከመደምሰስ ዳነ። ከመርከብ ወጥቶም ለእግዚአብ ሔር መሥዋዕት አቀረበ፤ እግዚአ ብሔር አምላክም ኖኅ ያቀረበውን መሥዋዕት ተቀበለ፤ እንዲህም አለ የሰው ልጆች ሁሉ ልባቸው ክፉ ቢሆንም ከዚህ ቀደም እን ዳደረኩሁት የሰው ልጆችን ሁሉ እንደገና በጥፋት ውኃ አላጠፋም፣ በምድር ዘመን ሁሉ መዝራት፣ ማጨድ፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አያቋር

ጡም፤ ስለዚሁም በምድር ላይ ደመ ናን በጋረድሁ ጊዜ የቃል ኪዳን ምልክት ቀስተ ደመና ትታያለች በማለት ለኖኅ ቃል ኪዳን ሰጥቶ ታል፤ ይህች ሰባት ኅብረ ቀለማት ያላት ቀስተ ደመናም ዝናብም በዘነበ ጊዜ በሰማይ ላይ ትታያለች።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ያን ለጻድቁ ኖኅ የተሰጠውን ቃል ኪዳን መሠረት በማድረግ ዘመኑን በአራት ወራቶች ከፍላ ለምእመ ናን እያስተማረች በየወቅቶቹ ለእ ግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋና ታቀርባለች፤ ወቅቶቹም ከመስከ ረም ፳፮ እስከ ታኅሣሥ ፳፭ ቀን ዘመነ መጸው (የበልግ ወራት) ከታኅሣሥ ፳፮ ቀን እስከ መጋ ቢት ፳፭ ቀን ዘመነ ሐጋይ ይባ ላል፤ ከመጋቢት እስከ ሰኔ ፳፭ ቀን ዘመነ ጸደይ ይባላል፤ ከሰኔ ፳ ፭ ቀን እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ዘመነ ክረምት በመባል ይታወ ቃል። እነዚህ አራት ወቅቶችም የተለያየ የአየር ጠባይ አላቸው፤ ከሰኔ ፳፭ ቀን ጀምሮ እስከ መስ ከረም ፳፭ ቀን ያሉት ወራት የክ ረምት ወራት ይባላሉ፤ በክረምት ወራትም ገበሬዎች እግዚአብሔር አምላክን ተስፋ በማድረግ ልዩ ልዩ የእህል ዓይነቶችን በእርሻቸው ላይ ይዘራሉ፤ እግዚአብሔር አም ላክም ዝናቡን ያወርዳል፣ ይሰጣ ልም፣ ምድርም በእህል ቡቃያ፣ በልምላሜ ተሸፍና ትታያለች። ፍጥረትንም ሁሉ ደስ ታሰኛለች፤ ዳዊትም በመዝሙሩ «ምድርን ጎበኘሃት፣ አጠጣሃትም፣ ብልጽግ ናዋን እጅግ አበዛህ፣ ሸለቆችም በእህል ተሸፈኑ፣ በደስታ ይጮ ሃሉ፣ ይዘምራሉም በማለት የእግ ዚአብሔርን ቸርነት ይናገራል፤ መዝ. ፷፬፣፱-፲፫



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ሕሙማነ ሥጋን በተአምራት፣ ሕሙማነ ነፍስን በትምህርት፣ ሙውታነ ሥጋን በተአምራት፣ ሙውታነ ነፍስን በትምህርት እያዳነ ቅዱስ ወንጌልን በዚህ ዓለም እየዞረ በሚያስተምርበት ዘመን በክረምት ወራት የሚሆነውን ምሳሌ በማድረግ ያስተምረ ነበር፤ ይህውም እነሆ ዘር ሊዘራ ወጣ፣ ሲዘራም አንዳንዱም በመንገድ ዳር የወደቀ ዘር አለ፣ ወፎችም መጥተው በሉት ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፣ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ ሥርም አልነበረውም፣ ደረቀ ሌላውን በእሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾህም ወጣና አነቀው ሌላውም በመልካም መሬት አንዱም መቶ አንዱም ስልሳ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ፤ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ፤ ማቴ. ፲፫፥፫-፱ በማለት አስተምረዋል።

የዚህም ትርጉም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሆኖ በሚያስተምርበት ጊዜ ሰምተው በማያስተውሉ ያደረ ትምህርት አለ፤ በወፎቹ የተመሰሉ አጋንንት ከልቡ ያደረውን የእግዚአብሔር ቃል ይነጥቁታል፣ ሳያፈራም ይቀራል፤ በጭንጫ የተዘራውም የተባለ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ይኸውም ቃሉን ሰምቶ ለጊዜው ይቀበለዋል፤ ነገር ግን ስለ ሃይማኖቱ መከራ ወይም ስደት ባጋጠመው ጊዜ ሃይማኖቱን ይክዳል ማለት ነው፤ ይህም ያለ ፍሬ ቀረ ማለት ነው፤ በእሾህ መካከል ተዘራ የተባለውም ዘር የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ይህም ቃሉን ይሠማል፤ ነገር ግን የዚህን ዓለም ሐሳብና የባለጠግነት መታለል የሰማውን ቃል አንቆ ስለሚይዘው ፍሬ ሳይሰጥ ይቀራል። በመልካም መሬት ማለት ሰምቶ በሚያስተውል ልቡና የተዘራ እህል ወይም ቅዱስ ቃል ግን ፍሬ ይሰጣል፤ ይህም እግዚአብሔር እንደሰጠው ጸጋ መቶ ፍሬ የሚሰጥ አለ፣ ስልሳ ፍሬም የሚሰጥ አለ፤ ሠላሳ ፍሬም የሚሰጥ አለ፤ ልቡና ያለው ያስተውል በማለት አስተምረዋል።

ስለዚህ በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን ምእመናን ሁሉ ክረምትንና በጋን እያፈራረቀ በነፋስ ምሕረት አሳድጎ፣ በፀሐይ አብስሎ ፍጥረትን ሁሉ ለሚመግብ አምላክ የምስጋና ፍሬ ሁልጊዜ ማቅረብ ይገባናል፤ ለገበሬዎችም ለሀገራችንም ለዓለም ሁሉ ሰላምን ዝናበ ምሕረትን ሰጥቶ፣ የተዘሩ አዝርእትን፣ የተተከሉ አትክልትን ለፍሬ እንዲያበቃልን፣ የታመሙትን እንዲያድንልን ሁልጊዜ ወደ ልዑል አምላክ እግዚአብሔር መጸለይ ይገባናል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ፍሬያትን ይባርክልን ምእመናንን በሃይማኖታቸው ያጽናልን አሜን። ✤

መልአከ ምሕረት ብርሃኑ ተስፋዬ

## አቡነ አረጋዊ...

ከገጽ ፳ የዞረ

ዝናቸውና ሥራቸውም ስለተሰማ ገዳሙ እየሰፋና እየገነነ ስለሄደ ወንዶችና ሴቶች መናንያን ይጎርፉ ጀመር። ለሴቶችም ከተራራው ሥር ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አሠርተው የሴቶች ገዳም መሥርተዋል፤ ይህንንም ገድላቸው ብቻ ሳይሆን በየዓመቱ ጥቅምት ፲፬ ቀን የሚነበበው መጽሐፈ ስንክሳር ይናገራል።

ገድላቸው እንደሚለው አቡነ አረጋዊ በዚሁ ገዳም መንፈሳዊ አመራርና መልካም ተግባር ከማካሄዳቸው ሌላ በጾምና በጸሎት፣ በስግደትና በአገልግሎት ተወስነው እያሌ ዘመናትን አሳለፉ፤ በመጨረሻም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳን መላእክትን አስከትሎ በደብረ ዳሞ ገዳም ተገለጸላቸው «ወዳጄ አረጋዊ ሆይ ከሕፃንነትህ ጀምረህ በሚገባ እኔን ስላገለገልክ በዚህ ቦታም ብዙ ስለደከምክ የቅድስናህን ሥራ ሁሉ ተቀብያለሁ ስምህን የጠራ፣ ዝክርህን ያዘከረ፣ አንተ በቆምክበት በዚህች ቦታ የሰገደ ሁሉ ለአንተ አሥራት እንዲሆንህ ሰጥቼሃለሁ፤ ይህ ያገለገልክበት ቦታህ ስለሆነ እስከ ዳግም ምጽአቴ ድረስ ጠለ ምሕረት አክለ በረከት እሰጠዋለሁ፤ ወደፊትም ብዙ ቅዱሳን መጥተው ይጸልዩበታል፤ የብዙ ቅዱሳን መጸለያ አድርጌ የመረጥኩትና የቀደስኩት ስለሆነ በዚህ ደስ ይበልህ» ብሎ ባርኪቸው ከፊታቸው ተሰወረ፤ በዚህ አባባል ገድላቸውና መጽሐፈ ስንክሳር ይስማማል።

አቡነ አረጋዊ ሁኔታው ስላስደሰታቸው ማኅበሩን ሰብስበው በሃይማኖታቸውና በመልካም ምግባራቸው እንዲጸኑ፣ እርስ በርሳቸው እንዲፋቀሩ፣ እንግዳ እንዲቀበሉና የገዳሙ ሥርዓት እንደ ጸና እንዲኖር መክረው እንደፈጸሙ በ፭፻፵፰ ጥቅምት ፲፬ ቀን በ፺፱ ዓመታቸው ተሰወሩ። የአቡነ አረጋዊን መመረጥና የቅድስና ሥራቸውን ተመልክተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ስለዚህም ገድላቸው ይህንን በመከተል አቡነ አረጋዊ ተሠወሩ እንጂ አልሞቱም ይላል፤ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ስለሌለ» አባባሉ የሚደገፍ ነው፤ ምክንያቱም ኤልያስ በእሳት ሠረገላ እንዳረገና ሄኖክም ሞትን እንዳያይ በእግዚአብሔር እንደ ተወሰደ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ነፍሳቸውን ጠልተው ለሚኖሩት ሰዎች በማቴዎስ ወንጌል በምዕ. ፲፯፥፳፮-፳፰ ሲያስተምር «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤ እውነት እላችኋለሁ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያይ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ» ብሏል፤ እኛ በታሪክ የምናውቃቸው እነ ኤልያስ፣ እነ ሄኖክ፣ እነ እዝራ ሞትን ሳይቀምሱ በብሔረ ሕያዋን ይኖራሉ፤ ክርስቶስ እንደ ተናገረው እርሱ የሚያውቃቸው እኛ የማናውቃቸው ሞትን ያልቀመሱ ብዙ ቅዱሳን በብሔረ ብፁዓን ይኖሩ ይሆናል፤ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ነው። ገድላቸው አቡነ አረጋዊ ጥቅምት ፲፬ ቀን መሠወራቸውን ነግሮናል፤ አልተሠወሩም የሚል ሰው ቢኖር ተሳስቷል፤ በዘመናችን እንኳን በአሰቦት ገዳም የነበሩት አባ በላይ ተሠወሩ ስለተባለ ጋዜጠኞች አሰቦት ገዳም ድረስ ሄደው ጠይቀው መሰወራቸውን ተረድተው መጥተው በትንሣኤ መጽሔት በቍጥር ፴፮ ወጥቶ ሕዝቡ ሁሉ እንዲያነበው ተደርጓል። ገድሉስ አቡነ አረጋዊ ተሠወሩ ብሎ ቢጽፍ ከማመን በቀር ምን ያጠራጥራል?

ጴጥሮስ ስለሚወደው ደቀ መዝሙር ይህ እንዴት ይሆናል? ሲል ጌታን በጠየቀው ጊዜ እስከ ምመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ እንዳለው እንረዳለን፤ ላገለገሉትና መስቀሉን ተሸክመው ለተከተሉት ለወዳጁ ለአቡነ አረጋዊ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ ዕድሜ ሰጥቶ ቢያቆያቸው የሚሳነው ነገር ስለሌለ አልተሠወሩም ልንል አንችልም፤ ይልቁንም እንደሳቸው ወንጌልን ሰብከንና መልካም አገልግሎት ሰጥተን እሳቸው ያገኙት ክብር ለማግኘት መሥራት ይፈለግብናል።

አቡነ አረጋዊ ስለፈጸሙት ተግባርና ስለመሠወራቸው ገድለ አባ ኤፍሬም የሚከተለውን ጽፏል። አቡነ አረጋዊ ሱባኤ ገብተው በዋሻ ከመቀመጥ ይልቅ ሰውን ማገልገልና ያልተማሩትን ማስተማር ደስ ይላቸው ነበር። ከዕለታት በአንደኛው ቀን አውልዐ ማኅበር ከሚባል ዛፍ ሥር ተቀምጠው ደብረ ዳሞ ታያቸው፤ ቦታውም ደስ ስላላቸው ወደ ተራራው ለመውጣት አቀዱ፤ ሄደውም ወደ ተራራው ለመውጣት ጉዞ ጀመሩ፤ ተራራውም በእግር ለመውጣት እንደማይቻል በመገንዘባቸው ከተራራው ሥር ሆነው ይጸልዩ ጀመር፤ በዚህን ጊዜ መሬቱን በመቋሚያቸው ቢመቱ ጠበል ፈለቀላቸው የጠበሉም ስም ማየ ምርቃ ይባላል፤ እስከ አሁን ድረስ በጠበሉ ሰዎች ይጠቀሙበታል፤ ለሰባት ቀን ያህል ከጸለዩ በኋላ ጠባቂያቸውና ረዳታቸው የሆነው ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ «ሌት ከቀን የምታገለግለው አምላክ እግዚአብሔር ወደዚህ ተራራ በእግርህ አትወጣም ነገር ግን ወደ ተራራው የሚያወጣህ አንድ ትልቅ ዘንዶ አፉን ከፍቶ ወደ አንተ ይመጣል፤ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ስለሆነ ይውጠኛል ብለህ አትፍራ በመስቀልህ አማትብ፤ ከያዝከው የበሶ ስንቅህ ትንሽ ቆንጥረህ በውኃ በጥብጠህ እርጨው፤ በዚህ ጊዜ መርዙ አልጫ ይሆናል፤ ጅራቱን ይዘህ ጀርባው ላይ ተቀምጠህ እንድትሄድ እንድ ነገርህ እግዚአብሔር ልኮኛል አላቸው» እንደ ተባለውም ዘንዶው መጣ ያላቸውን ሁሉ አደረጉ፣ ጅራቱን ይዘው ጀርባው ላይ ተቀምጠው ተራራው ላይ ወጥተው በሰላም ዐረፉ ገዳሙንም አስፋፉ ይላል።

ይህንኑ መሠረት በማድረግ የአካባቢው ሕዝብ የገብሱን በሶ እንደ መድኃኒት ቆጥሮ ሲጠቀምበት ይታያል፤ በሚጓዝበትም ጊዜ ስንቁ በሶ ነው፤ አቡነ አረጋዊም ከልብ ስለሚወዳቸውና ስለሚያምናቸው ጠበላቸውን ሳይዝ ራቅ ወደ አለ ቦታ አይሄድም። በመንገድም ሆነ በእርሻው ላይ ዘንዶ፣ ጊንጥ፣ ጋዚራ፣ እባብ እነዚህን የመሳሰሉት በነደፉት ጊዜ መርዙ ወደ ሰውነቱ እንዳይሰራጭ ጋቢ ካለው ጋቢውን ከሌለው የነደፈውን በልጥም በገመድም አሥሮ በያዘው በአቡነ አረጋዊ ጠበል በሶውን በጥብጦ ቁስሉን ይቀባዋል፤ ወዲያው ከደዌው ይፈወሳል፤ ይህም ዘመናዊ የሕክምና መድኃኒት ወደ አገራችን ገብቶ እስኪስፋፋ ድረስ ሲጠቀምበት ኖሯል፤ አሁንም ይጠቀሙበታል።

አቡነ አረጋዊ ጥቅምት ፲፪ ቀን ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ የወጡበት ሲሆን ጥቅምት ፲፬ ቀን ደግሞ የተሰወሩበትና ቃል ኪዳን የተቀበሉበት ዕለት ነው። በዚሁ ዕለት አማኝ የሆነ ሁሉ በሶ እየያዘ ጽላታቸው በተተከለበትና በዓላቸው በሚከበርበት ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል፤ ካህን እያስባረከ ለተሳላሚው ሁሉ ያድላል፤ ይህም መልካም ባህልና የተቀደሰ ልማድ በመሆኑ እንዲቀጥል ያስፈልጋል። ጥር ፲፬ ቀን የሚከበረው ደግሞ አቡነ አረጋዊ አመክሮአቸውንና አገልግሎታቸውን ፈጽመው ከአባ ጳኩሚስ ዘንድ ልብሰ ምንኩስና የለበሱበትና አስኬማ የተቀበሉበት እግዚአብሔርንና ሰውን ለማገልገል ቃለ መሐላቸውን የፈጸሙበት ዕለት ስለሆነ ነው። ግንቦት ፲፬ ቀን ደግሞ አንዱ የወንጌል ሰባኪ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያድናታል።

ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል፤ ሲል ወንጌላዊው ማርቆስ በምዕ.፰፥፴፭-፴፯ የጻፈውን ከወላጆቻቸው ጋር ቤተ ክርስቲያን ሄደው ሰባኪው ሲሰብክ ሰሙ፣ ወዲያው ከትልቅ መወሰድ ኃላፊ ጠፊ በመሆኑ ራሳቸውን ከሥራ ለሥራ መውሰድ ይሻለኛል በማለት ከወላጆቻቸውና ከዘመዶቻቸው ተለይተው ሁሉን ነገር ትተው ከዓለም ወደ ገዳም የመነኑበት ቀን ነው። ይህም በመሆኑ ራሳቸውን ከሥራ በመውሰዳቸው ተሰወሩ ባለንበትም ዘመን ሥራቸውና አገልግሎታቸው በሰው ዘንድ እየተገለጸ በመሄዱ በአዲስ አበባ ከተማ የአቡነ አረጋዊ ጽላቶች በአሉበት አብያተ ክርስቲያናት በመስፋፋትና በዓላቸውም በመከበር ላይ ስለሆነ ስማቸውና ታሪካቸው ሕያው ሆኖ እንደሚኖር ለማንም የተሰወረ አይሆንም። ✤

ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ወንድም



www.ethiopianorthodox.org

# በገዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ጠበል ፲፯ ኢአማንያን በክርስትና እምነት ተጠመቁ፤ ፲፩ መናፍቃን ተመለሱ፤

በአዲስ አበባ ልደታ ክፍለ ከተማ በሚገኘው የገዳመ ኢየሱስና መጥምቁ ዮሐንስ ጠበል ብዙ ሕመምተኞች ከልዩ ልዩ ደዌያት ድነዋል፤ ኢአማንያን ተጠምቀዋል፤ መናፍቃን እምነው ተመልሰዋል።

የገዳመ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ያለበት ቦታ ለብዙ ዓመታት የጥምቀት በዓል የታቦታት ማደሪያና ማክበሪያ ሆኖ ከቆየ በኋላ የጸሎት ቤት ተሠርቶ ጽላቶች እንዲገቡበት፤ እንዲቀደስበትና አገልግሎት እንዲፈጸምበት በመጠየቁ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የኢየሱስ፤ የመጥምቁ ዮሐንስና የክርስቶስ ሠምራ ጽላቶች ተባርከው እንደገቡ በጽ/ቤቱ ያለው የጽሑፍ መዝገብ ያስረዳል።

ታቦታቱ ተባርከው ገብተው አገልግሎት ከተጀመረ በኋላ ወቅቱ የእመቤታችን ድንግል ማርያም መታሰቢያ ጾመ ፍልሰታ በመሆኑ የአካባቢው ምእመናን የቅዳሴውን ሥርዓት በማክበር ፲፮ ቀናት ያለ ማቋረጥ የቻሉ ሥጋ ወደሙ በመቀበል፤ ለዚህ ዕድል ያልበቁ ሲያስቀድሱና ትምህርተ ወንጌል ሲከታተሉ ሰንብተዋል። አሁንም አገልግሎቱ በስፋት ይካሔዳል።

በዚህ ጽሑፍ ለመግቢያ ያህል የቤተ ክርስቲያኑን አመሠራረት ጠቀስን እንጂ በአሁኑ ወቅት በዚህ ቅዱስ ቦታ የሚፈጸሙትን ልዩ ልዩ ገቢረ ተአምራት አውቀውና ተረድተው በተለያዩ ደዌያት የሚሰቃዩ ሰዎች ወደ ተቀደሰው ጠበል ሔደው ተጠምቀው ከሕመማቸው ጭንቀት እንዲላቀቁ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዚህ ዓለም ጠበብቶች በዕውቀታቸው የመጠቁ፤ በአነጋገራቸው የተራቀቁ ሁሉ መድኃኒት ያላገኙለትን በሽታ የእምነት ተከታዮቿን ብቻ ሳይሆን ከእምነቷ ውጭ የሆኑ ሰዎች ሁሉ በጠበል እየተጠመቁ በመዳናቸው ወደ አንጋፋዋ እናት ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት ብዙዎች ናቸው።

በገዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ተገኝተን የደብሩን አስተዳዳሪ መልአከ ኃይል ዋካ ድንግል ደስአለኝን በቅድሚያ አነጋግረን ነበር።



መልአከ ኃይል ዋካ ድንግል ደስአለኝ
የገዳሙ አስተዳዳሪ

<u>ልሳነ ተዋሕዶ፡-</u> በቦታው ተገኝተን እንደተመለከትነው በዚህ ቤተ ክርስቲያን በጠበሉ እየተጠመቁ የዳኑ ሰዎች ብዙዎች ናቸው፤ ይህ የጠበል ፈውስ የተገኘው ቤተ ክርስቲያኑ ከተመሠረተ ጀምሮ ነው እንዴት ነው?

<u>መልስ፡-</u> እግዚአብሔር አምላክ ለእያንዳንዱ የተለያየ ስጦታ ይሰጠዋል፤ ለቸርነቱ ወሰን የለውም፤ በዚህ ጠበል ብዙ በሽተኞች እየተጠመቁ የዳኑት ከመጋቢት ወር ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ወዲህ ነው።

<u>ልሳነ ተዋሕዶ፡-</u> ከመጋቢት ወር ወዲህ ጠበል ፈልቆ ነው ወይስ አባቶቻችን እንደሚያደርጉት ቃለ እግዚአብሔር ተነቦና ጸሎት ተደርጐ በእምነት ውሃው ጠበል ሆኖ ነው?

<u>መልስ፡-</u> በመግቢያው እንደገለጽኩት ሊቀ ኅሩያን ኪነ ጥበብ ብርሃኔ የተባሉ እግዚአብሔር መርቶ ያመጣቸው ቤተ ክርስቲያን በትምህርት አበልጽጋ ያሳደገቻቸው አባት አግኝተን ከአንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ ስምንት ሰዓት የተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይነበባሉ፤ ምስባክ፤ ወንጌል፤ ኪዳንና ትምህርት ተሰጥቶ ሲያበቃ ከዚያ ሕዝቡ ይረጫል ይድናል ጠበሉ የፈለቀ አይደለም።

<u>ልሳነ ተዋሕዶ፡-</u> በአንዳንድ አድባራትና ገዳማት ካህናቱ የራሳቸው መሆኑን እየዘነጉ እንደዚህ በአሉት ሰዎች ላይ አንዳንድ ችግር የሚፈጥሩ አሉ፤ በዚህስ ቦታ ምን ይመስላል?

<u>መልስ፡-</u> አስተሳሰብ የጐደላቸው ካህናት ካልሆኑ በቀር እንዲህ ያለውን የራስን ሥራ መተግበር ቀርቶ መመኘት እንኳን ለኅሊና ይከብዳል፤ ምክንያቱም የደመወዝ ዕድገት የሚገኘው ገቢ ሲኖር ነው፤ ይህ ካል ሆነ የገቢ ምንጭ ሊቋረጥ ስለሚችል መነሣት አይገባውም፤ ሆኖም ለሁሉም ትምህርት ስለሚሆን በጥያቄ መቅረቡ መልካም ነው።

<u>ልሳነ ተዋሕዶ፡-</u> ሊቀ ኅሩያን ኪነ ጥበብ ብርሃኔ ወደ እዚህ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊመጡ እንደ ቻሉና አንዳንድ ጊዜ የዚህ ስጦታ ያላቸው ሰዎች እየተዘዋወሩ ማጥመቅ ስለሚወዱ፤ በዚሁ ጸንተው እንዲኖሩ የምታደርጉት እንክብካቤ እንዴት ነው?

<u>መልስ፡-</u> እሳቸው እንዳስረዱኝ ከክፍለ ሀገር መጥተው በማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ማጥመቅ እንደ ጀመሩ ብዙ ሕዝብ ይመጣ ነበር፤ ከዚያ እኔ ይህን ቦታ እንዲጎበኙት ጠራኋቸው፤ ቦታውን ሲያዩት እንዲያውም በራእይ ያየሁት ይህ ነው ብለው ከዚሁ ሥራቸውን ጀመሩ።

እንክብካቤ የምናደርግላቸው ሕዝቡ ተባብሮ አስተዋጽኦ በማድረጉ መኖሪያ ቤት አግኝተዋል። መደረግ የሚገባውንም ተሟልቷል ባንልም ከሚያስገኙት ገቢ መጠነኛ ክፍያ ተስማምተን እንከፍላለን። ሌላው ሳስገነዝብ የምወደው ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ከመጥምቁ ዮሐንስ የተሰጣቸውን ስጦታ አምኖ ሕዝቡ እሳቸውን የሚጠባበቅ ስለሆነ አደራቸውን እንዲወጡ ለማስገንዘብ እወዳለሁ በማለት የቀረበላቸውን ጥያቄ በሰጡት መልስ ለማወቅ ችለናል።

## ሀብተ ፈውስ ከተሰጣቸው ከሊቀ ኅሩያን ኪነ ጥበብ ብርሃኔ ጋር የተደረገ ጥያቄና መልስ

<u>ልሳነ ተዋሕዶ፡-</u> መሪጌታ ኪነ ጥበብ ብርሃኔ ይህንን የማጥመቅ ሥራ ከመጀመርዎ በፊት የቅኔ መምህር ነበሩ ይባላል እውነት ነው?



ሊቀ ኅሩያን ኪነ ጥበብ ብርሃኔ

<u>መልስ፡-</u> ለአሥራ አምስት ዓመታት በታላቁ ገዳም በጉና ቅዱስ ሚካኤል ቅኔ አስተምሬአለሁ፤ ያስተማርኳቸውም ደቀ መዛሙርት በር እስ ከተማው በአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ሆነው አገልግሎት እያበረከቱ የሚገኙ አሉ።

ልሳነ ተዋሕዶ፡- የቅኔ መምህር ከሆኑ የማስተማሩን ሥራ ትተው ወደ ማጥመቁ ተግባር ሊገቡ የቻሉት በምን ምክንያት ነው? ማስተማሩም እጅግ በጣም ታላቅ ሥራ እንደሆነ ያውቁታል፤

መልስ፡- ሁሉም ሥራ ሊከናወን የሚችለው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ እኔም ወደዚህ ሥራ እገባለሁ ብዬ አላሰብኩም፤ የትዳር ጓደኛዬ ወ/ሮ አስከዳር ብርሃን ስለ ታመመችብኝ ጉዛ መድኃኔ ዓለም ገዳም አንድ ታላቅ ባህታዊ አባ ወልደ ሰንበት የሚባሉ የሰሌን ቀሚስ የለበሱ ጉድጓድ ምሰው በዚያ ውስጥ ነው የሚኖሩት፤ ጠበል ማጥመቅ፤ አብያተ ክርስቲያናትን ማሳነጽ፤ ማስተማር፤ የታመሙ የማዳን ሀብተ ፈውስ ተሰጥቶሃል፤ በዚህ ቀጥል ይሉኝ ነበር። ባለቤቴን የሐኪምና የአገር ባህል መድኃኒት አላድናት ብሎ ስጨነቅ ጉዛ መድኃኔ ዓለም በአንዲት ብርሌ ጠበል ዘንዶ የመሰለ አውሬ ከሆዷ ወጥቶ ወደቀ ይህንን ሕመሟን ስከታተል አስቻ ሚካኤል አጥማቂ መጥተዋል ስለተባለ በ፲፱፻፸ ዓ.ም ሔጄ ከተሰበሰበው ጉባኤ መሐል አጥማቂው አጥምቀው ሲያበቁ አስተምር አሉኝ፤ ትምህርቱን እርስዎ አስተምረውታል እኔ ግን የትዳር ጓደኛዬ ታማ ላስጠምቅ ነው የመጣሁት ስላቸው፤ አጥማቂው የእኛ ሥራ እንጓንት ማውጣት ነው ሲሉ ይህ አባት በጎንደር መሠረት ብስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አምሐ ለክሙ ሠራዊተ እንጓንት የዲያብሎስ አሽከሮ በሙሉ ውጡ ብዬ ሳወግዝ በዚሁ ቦታ ግን እንጓንት ከሰው ላይ ሙጉ፤ የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፈርሶ ገና እየተሠራ ስለ ነበር እንሰድህም ብለው ከዚያው ስድስት ወራት አጥምቁ ቤተ ክርስቲያኑን እንዲሠራ ረድቼ ወደነ በርከበት ቦታ ተመለስኩ።

እመቤታችን በራእይ ይህን የማጥመቅ ሥራ አትተው ስለአለችኝ የገብረ ሰላም ካህናትን ፫ ጊዜያት አብልቼ፤ የቃና ዘገሊላ የቅዱስ ሚካኤል ዝክር ስዘክር በሠርጉ ቤት ጌታችን ኢየሱስ፤ እመቤታችንና ደቀ መዛሙርቱ እንደተገኙ ሁሉ እመቤታችን ድንግል ማርያም ተማሪ ማስተማርና በቤተ ክርስቲያን መስበክ ነው የሚሻለኝ ብዬ ወደ ቤቴ ስሔድ የትዳር ጓደኛዬ እንጀቷን ወጋኝ ብላ ወደቀች፤ ይህ የሆነው በ፲፱፻፸፰ ዓ.ም ነው ደብረ ታቦር ሐኪም ቤት ብወስዳት አንችልም ባሕርዳር ውሰዳት አሉኝ፤ ጥር ፳፩ ቀን የእመቤታችን ዕለት ኦፕሬሽን ልትሆን ገብታ ባህታዊት የመሰለች ቀይ መነኩሲት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የእመቤታችን ድንግል ማርያም ቃል አፍርሰሃል የተቀጣኸው ቅጣት ነው፤ ይህን የማጥመቅ ሥራ ካልጀመርክ መከራ ይገጥምሃል አለችኝ።

በራእይ የተገለጠልኝን በባሕርዳር ኪዳነ ምሕረት ቆሜ ተናግሬ የማጥመቅ ሥራ ልጀምር ስል እንዲያምኑህ አስቀድመህ ከሰበካ ጉባኤዎቹ ጋር ተወያይ አለችኝ፤ ከተወያየሁ በኋላ ይህ ሜዳ ይሞላል ብዬ ተናገርኩ፤ በሳምንቱ ወደ ሰባት ሺህ ሰዎች ተሰበሰቡ ቀጥሎ ሥፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ ጐረፈ። በመተት፤ በዛር፤ በጋኔን፤ የሚጥል በሽታ፤ ስኳር፤ አስም፤ ጨጓራ፤ ኩላሊት፤ ኤች አይ ቪ ኤድስ ብዙ ሕመምተኞች ከደዌያቸው ተላቀቁ፤ ከየካቲት ፳፩ እስከ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም አጥምቄ ቀድሞ ወደ ነበርኩበት እሔዳለሁ ስል ሁለት መኪና ሕዝብ በሙሉ ተከትሎኝ ደብረ ታቦር ገባ፤ ቀድሞ ወደነበርኩበት ብወስደው ገጠር ነው፤ ከምን ላይ አስተናግደዋለሁ ከተማው ይሻላል በማለት ከብፁዕ አባታችን አቡነ ኤልሳዕ ሐጄ ሁኔታውን ስለሚያውቁ ደብዳቤ መታወቂያ ስለአለኝ ከደብረ ታቦር ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ





www.ethiopianorthodox.org

ጋር ተነጋግሬ ትልቅ አዳራሽ ስለ አላቸው በዚያ ማጥመቅ ጀመርኩ፤ ዐይኑ የታወረ፣ እጅ እግሩ የታሠረ፤ በልዩ ልዩ ደዌያት የተያዘ፣ ከኤች አይ ቪ. እየዳኑ ለሁለት ዓመታት በዚያ ቆየሁ።

የደብረ ታቦር ሊቃውንትና ሕዝብ ከዚያ እንድቆይ ሲለምኑኝ ባለቤቴ ታመመችብኝ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ነው የምትገላለገል ውሰድ አለኝ፤ በእሷ አማካይነት ወደ አዲስ አበባ መጣሁ።

ከዚህ ስደርስ በራእይ የምሥራች ደስ ይበለን በጣም ደስ ደስ ይበለን የኤድስ በሽታ ተገኘ ገዳመ ኢየሱስ ጣና ኢየሱስ እያለ ሁለቱን ሲያፈራርቅልኝ ለባሕታዊው ለደብረ ታቦሩ ኢየሱስ ብነግራቸው ገዳመ ኢየሱስም ይኸው ነው ጣና የተባለውም ባሕር ነው፤ ከተማው ይህ ነው አትሔድም እያሉ ከበቡኝ፤ መንገዱን ግን እራት መንገድ አድርጉ ወደዚህ አሳይቶኝ ስለነበር የካቲት ፲፪ ቀን የካ ሚካኤል ላይ አቶ ሠዓሊ ካሣን ሥዕል ይዘው የሚዞሩትን አገኘኋቸው፤ እሳቸው እየመሩ ማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን አስገቡኝ ለ፲፩ ቀናት አጥምቄ፣ መልአከ ኃይል አባ ዋካ ድንግል ደስ አለኝ የገዳመ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ቦታውን ይባርኩልኝ ብለው ይዘውኝ መጡ ከዚህ መጥቼ ስጠይቅ ገዳመ ኢየሱስ አሉኝ፣ ይህን ቦታማ ቀደም ብዬ የተላኩበት መሆኑን ነገርኳቸው፤ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በስመ አብ ብዬ ማጥመቅ ስጀምር የኤች አይ ቪ. አጋንንት በሙሉ ጮኹ፤ ከዚያ አንስቶ እስከ አሁን ለአብነት ያህል ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፬ ዐይነ ሥውራን፣ ግንቦት ፫ ቀን ፲፯ ዐይነ ሥውራን፣ ከላሊበላ የመጣ አንድ በሽተኛ በሐኪም ቤት አልድን ብሎ አጋንንት ሲለቁት ከሆዱ ስድስት ሜትር አባብ በሕዝቡ መካከል እየታየ ወጣ፤ የአንዲት ሲስተር ልጅ የደብረ ዘይት ዕለት ንባቡ ተነቦ ኪዳኑን አድርሰን ስረጨው ብድግ አለ፤ ዕውሮች ሲበሩ፣ ሽባዎች ሲነሡ፣ ቡዳው ሲለፈልፍና የያዘው ሲፈወስ በሕዝቡ ዘንድ አልልታ ሲስተጋባ ከዚህ የቆየሁት በዚህ የተነሣ ነው።



ሀብተ ፈውስ የተሰጣቸው ሊቀ ኅሩያን ኪነ ጥበብ ብርሃኑ በማጥመቅ ላይ እንዳሉ።

ልሳነ ተዋሕዶ፦ በአንዳንድ ቦታዎች ሀብተ ፈውስ ለተሰጣቸው ሰዎች በምትሐት ነው እያሉ ወደ ሐሜት ይገባሉ፤ በእርስዎ በኩል ከማጥመቅዎ በፊት የሚያነቧቸው መጻሕፍቶች ምን ዓይነት ናቸው?

መልስ፦ በመጀመሪያ እኔ የግል ጸሎቴ ውዳሴ ማርያም፣ መልክአ ማርያም፣ መልክአ ኢየሱስ፣ መልክአ ሚካኤልና መልክአ ገብርኤል እነዚህን ከጨረስኩ በኋላ ዳዊት እደግማለሁ፤ ከጉባኤው ስገባ ሰይፈ መለኮት፣ ድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ገብርኤል፣ ገድለ ጊዮርጊስ፣ ገድለ አቡነ ገ/መንፈስ ቅዱስ፣ ገድለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ ገድለ አቡነ ሐራ ድንግል፣ ገድለ መርቆሬዎስ ከተነበቡ በኋላ ምህላ፣ ተአምረ ማርያም፣ ምስባክ፣ ወንጌል፣ ኪዳን ከአደረስን በኋላ ትምህርት ይሰጣል፤ በመጨረሻ በስመ እግዚአብሔር የቅዱሳንን ስም እየጠሩ በጠበል እንዲወጣ ማድረግ ነው፤ አጋንንት አጋንንትን ያወጧቸዋል፤ ይህ ጥንታዊ ነው ባሕር ዳርም ደብረ ታቦር ኢየሱስም ሊቃውንቱ እየመጡ እያዩ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ይህ እውነትም ጸሎቱ ነው ባለ ሕግ ነው፤ ብቃት የሌለው ሰው እንዴት ይህን ሊያደርግ ቻለ የሚሉ አሉ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም» ብሎ መናገር ብቻ ነው እያሉ ተመልክተው ተረድተው የሚሔዱ ብዙዎች ናቸው።

ልሳነ ተዋሕዶ፦ ሌላው በየሳምንቱ ከእሑድ አንስቶ እስከ ቅዳሜ ድረስ ፕሮግራሞች አሉ ይባላል። ካጠመቁ በኋላ በእነዚህ ቀናት የሚፈጸሙ ተግባሮች ምንና ምን ናቸው?

መልስ፦ እኛ የምናደርጋቸው፦

ሰኞ፦ በየቀኑ ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ጀምሮ ወረፋ እየያዙ ጥምቀት ይጠመቃሉ፤ ንባቡን ከጨረስን በኋላ የኤች አይ ቪ. ኤድስ ምርመራ ለማድረግ ጠበል በመያዝ የዝሙት አጋንንት ደም እንዳትልሱ፣ ሥጋ እንዳትቀምሱ፣ አጥንት እንዳትከሰክሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሰዎቹ ደም ሬት ኮሶ ይሁንባችሁ ይምረራችሁ በእመቤታችን ድንግል ማርያም በዮሐንስ ስም አጠግባችኋለሁ በማለት እንዲለቁ ይደረጋል።

ማክሰኞ፦ በመተት የተተበተበትን ሁልጊዜ የሚካሔድ ጸሎት ከአበቃ በኋላ የአጋንንት ሥራ ያለበትን አውግገዉ አስለቅቃለሁ፤ የመድኃኒትም ከሆነ በጠበሉ ጠጥተው ይወጣላቸዋል።

ረቡዕ፦ ዐይነ ሥውሮችን በተራ በሠልፍ አድርገን በመመርመር በጠበሉ ሲረጩ ዐይናቸው ይበራል።

ሐሙስ፦ ወንዶችንም ሴቶችንም የጠበሉ ማጥመቅ ሥራ ከተፈጸመ በኋላ ቅብዐ ቅዱስ ይቀባሉ፤ የምንቀባው እሳት ነው እያሉ አጋንንት እየጮሁ ይለቃሉ።

ዓርብ፦ በመስቀሉ መላ ሰውነታቸው እየታሸና እየተዳበሰ ከአለባቸው በሽታ ሁሉ መስቀል መግረሬ ፀር ማለት የአጋንንት ማባረሪያ ስለሆነ እየጮሁ የሚለቁት ስፍር ቁጥር የላቸውም።

ቅዳሜ፦ በዓል ስለሆነ ጸሎቱን ከጨረስን በኋላ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በጠበሉ ፈውስ ያገኙ ምስክርነት ይሰጣሉ፤ ስዕለት ያላቸው ስዕለታቸውን ከምን በሽታ እንደዳኑ እየተናገሩ ያስገባሉ።

እሑድ፦ የቅዳሴውን ሥርዓት ሁሉም ይከታተላል፤ የዕረፍት ቀን ስለሆነች ተአምረ ማርያም አንብበን ጠበሉን ረጭተን መሰነባበት ብቻ ነው።

ልሳነ ተዋሕዶ፦ በአንዳንድ ቦታዎች ሀብተ ፈውስ ያላቸው ሰዎች ሲገኙ በሰበካ ጉባኤውና በካህናቱ በኩል እንክብካቤ አይደረግላቸውም ይባላል፤ በዚህ ያለውስ ምን ይመስላል?

መልስ፦ በገዳመ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ያለውን እንክብካቤ እንደ ዋናው ሕዝቡ ነው አስተዳዳሪውና ሰበካ ጉባኤው ተነጋግረው እንደ ባለቤት ሆነህ ለቦታው አስብለት አሉኝ፤ ከሌላ ቦታ ሆኜ እየተመላለስኩ ነበር የማጠምቀው ባዶ ቦታ ሰጡኝ፣ ተጠማቂውና የአካባቢው ሕዝብ ተረባርቦ የተሟላ ቤት ሠራልኝ፣ አጥሩንም አጥሮ ሰጠኝ፤ ቦታው የቤተ ክርስቲያን ስለሆነ አይሸጥም አይለወጥም ቤቱ ግን እስከ መጨረሻው በሌላ ክፍለ ሀገርም ብትዘዋወር ጠባቂ ቁልፍ ያዥ አድርገህ መጠቀም ትችላለህ ሲሉ ተስማምተናል።

ሌላው ከጠበሉ ከሚገኘው ገቢ የሰበካ ጉባኤው ጽ/ቤት እየተጠቀ ጣጠረ ከማገኘው ትንሽ ገቢ ፴፮ ካህናት የሚያነቡ እንዲሁም የሚያስተናግዱ በመጠነኛ ደመወዝ ተቀጥረው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፤ ሲሉ ለጠየቅናቸው በቂ መልስ ሰጥተውናል።

## በጠበሉ የዳኑ ይናገሩ



ብርዝናሽ ከበደ

ጉራጌ አገር ዞን ቸሀ ወረዳ በሉቄና በኤፓ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ነዋሪ የሆንኩ ከባድ የሆድ ሕመምና ኪንታሮት ነበረብኝ በሐኪም ከብር ፭፻ ሺህ (አምስት ሺህ ብር) በላይ ፈጅቼ ምንም ሳይሻለኝና ምግብ ተከልክዬ ስኖር ነሐሴ ፲ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም በገዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ጠበል ስጠመቅና ስጠጣ ዕለቱን ምግብ በላሁ በቅዱስ መስቀሉ ስታሽ፣ በጠበሉ ስጠመቅና ስጠጣ የአለብኝ በሽታ ስለቀቀኝ በጣም ደስ ብሎኛል።



ሕፃን አብርሃም በለው

የኤች አይ ቪ. ታማሚ ስሆን አባቴን ገሎ እኔና እናቴን አመንምኖን ስለነበር በሐኪም ተመርምሬ አለብህ ተብዬ ዛሬ ግን በጠበሉ ተጠምቄ በመስቀሉ ታሽቼ ድኛለሁ ሲል ምስክርነቱ ሰጥቷል።

አቶ ንጉሤ ተገኝ

ነዋሪነቴ ኮልፌ ቀራንዮ ነው፤ በነቀርሳ በሽታ ፲፰ ዓመታት በሐኪም ቤት ደክሜ አቅቶኝ የነበረውን በገዳመ ኢየሱስና መጥምቁ ዮሐንስ ጠበል ቅብዐ ቅዱስ ተቀብቼ በመስቀል ታሽቼ ከአለብኝ በሽታ መዳን ችያለሁ።



በሻ በቀለ አደራ





www.ethiopianorthodox.org

ግራ ዐይኔን አሞኝ በሕክምና ስመላለስ ቆይቼ ምንም ተስፋ ባለ ማግኘቴ ተስፋ ቆርጬ ስኖር ገዳመ ኢየሱስ ጠበል ተጠምቄ ስለዳንኩ የደስታዬ ብዛት ከመጠን በላይ ስለ ሆነ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው በማለት ምስጋናዬን አቀ ርባለሁ።



ወ/ሮ ወይንሸት እንግዳእሸት

የደም ግፊት በሽታ ስታመም ቆይቼ በገዳመ ኢየሱስ ቤተ ክርስ ቲያን በዮሐንስ ጠበል ተጠምቄ ስለካ በጣም ቀንሶ በመገኘቱ ሕይ ወቴ እንደተመለሰ ቈጥሬዋለሁ ለእ ግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው።



አቶ ጫላ አጀርሳ

ሚስት ላገባ ስል ተመርምሬ ኤች አይ ቪ ኤለብህ ስባል በድን ጋጤ የሚጥል በሽታ ያዘኝ፤ ቀይ ሴትዮ በሕልሜ ታይታኝ በዚህ ጠበል መጥቼ ስጠመቅ የሚጥለኝ በሽታም ለቀቀኝ አለብህ የተባልኩ ትም ለቀቀኝ ለእግዚአብሔር ምስ ጋና ይግባው።



ዘነበች

በሚጥል በሽታ ሽባ ሆኜ በገ ዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ጠበል ስለዳንኩ ሕይወቴ ስለተመ ለሰልኝ ደስ ብሎኛል።



ገብረ ጻድቅ

ኤች አይ ቪ አለብህ ተብዬ ከዚህ ቦታ ተጠምቄ ስለዳንኩ ደስ ስለአለኝ ምስክርነቴን ከነፎቶግ ራፌ አስረክቤአለሁ።

እማሆይ ወለተሥላሴ

በቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቅ/ጴጥ ሮስ ቤተ ክርስቲያን ድኩማን መጠ ለያ እኖራለሁ፤ ከሆዴ ውስጥ እየ ተገለባበጠ ስበላ ስጠጣ እያስጨ ነቀኝ፤ በመነኮስኩ በ፲፭ ዓመቴ ርግዝና በምን መጣ እያልኩ እጨ ነቅ ነበር፤ በዘመኑ በሽታ የታመ መች ልጅ ለለችኝ እርሷ እየመ ጣች በገዳመ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲ ያን በቅ/ዮሐንስ ጠበል ትጠመቅ ነበረ፤ አንድ ቀን እንቺ ቅመሽ ብላ ሰጠችኝ፤ ተናንቆ እንደምጥ ያዘኝ ምንድነው ብዬ ስጨነቅ ሁለት ጭራ ያላቸው ረጃጅም እውሬዎች ዐይናቸውን ያፈጠጡ ወጡልኝ፤ በተለያየ ጊዜያት እንደ ዓሣ የመ ሰሉ ከወጡልኝ በኋላ ይደክመኝ የነበረው ሁሉ ለቅቆኝ አሁን ለም ስክርነት መጥቻለሁ በማለት ቃላ ቸውን ሰጥተዋል፤ ሥዕለታቸው ንም አስገብተዋል።

ሕፃን ሰላማዊት ዋልተር

በወረዳ ፳ ቀበሌ ፵ በቤት ቊጥር ፲፻፺፱ ነዋሪ የሆነች ድን ገት ሳላስብ ታማብኝ በየሆስፒታሉ ሳንክራትታት ጨጓራና የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን ተብሎ ተሰጣት ያገሳት ስለነበር እሱ ብቻ ተዋትና ሌላው የጉን ውጋት ሆኖ ሲተዋት አልቻለም።

የእናቴ ጐረቤት ገዳመ ኢየሱስ ጠበል ብትወስጃት ትድናለች ስለአ ሉኝ ታገዛላ መጣች አሁን የሚያስ ጮኸትም ለቀቃት ተሳስሮ የነበረው እጅና እግሯ ተፈታ ለክብሩ መግ ለጫ ለጥር ኢየሱስ ጃንጥላ አሁን አንድ ኪሎ ዕጣን አስገብቻለሁ ለእኔ የደረሰ ፈጥኖ ለእናንተም ይድረስላችሁ።

በገዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ጠበል የዳኑ ሰዎችና የበሽ ታው ዓይነት



| | |
|---|---|
| ስኳር ፲፩ | ነርቭ ፳ |
| የደም ግፊት ፴ | አስማት ፰ |
| ዐይነ ሥውር ፶፩ | አጋንንት ፵ |
| ጨጓራ ፲፯ | ኩላሊት ፲ |
| የራስ ቁስል ፰ | መተት ፲፫ |
| አልማዝ ባለጭራ ፱ | ኤች አይ ቪ ፮ |
| ቡዳ ፰ | አስም ፲ |
| የሆድ ሕመም ፲፩ | የነርቭ ፲፩ |

እነዚህ በቅርብ ጊዜ የተመ ዘገቡ ናቸው።

ኢትዮጵያዊው ሊቃ ቅዱስ ያሬድ በዝማሬ ድርሰቱ ፣ ዜማው «ንዑ ርእዩ ዘንተ መንክረ ዕፁብ ግብረ ዘገ ብረ መድኃኒነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ ያደረገውን ድንቅ ሥራ መጥታ ችሁ እዩ እንዳለው ሁሉ በገዳመ ኢየሱስና በመጥምቁ ዮሐንስ ጠበል የሚፈጸመውን ልዩ ልዩ ኀብረ ተአ ምር በጆሮ ከመስማት በዐይን ሔዶ መመልከት አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው አምነው ለሚቀርቧት ፍቱን መድኃኒት ናት፤ የረቀቀውን አጉልታ የራቀውን አቅ ርባ፣ የተቸገረውን ተንከባክባ፣ ያላ መነውን አሳምናና አጥምቃ የመን ፈስ ቅዱስ ልጅ ታደርገዋለች፤ ከሥ ጋና ከነፍስ ደዌያት ታድነዋለች።

ይህችን እንጋፋ ቤተ ክርስቲ ያን የሚጠሉ ይጠላሉ፣ የሚነቅፉ ይወድቃሉ፣ የሚያከብሯት ይከብ ራሉ፣ የሚያቃልሏት ራሳቸው ይቀላሉ።

ስለዚህ «ሕመምተኞች ባለመ ድኃኒት ይፈልጋሉ» ተብሎ እንደ ተጻፈው በሥጋና በነፍስ ደዌያት የተያዙ ሁሉ በታወቁት ቅዱሳት መካናት ጠበል እየሔዱ ቢጠመቁ እንደሚድኑ የመጽሔቱ ዝግጅት ክፍል መልእክቱን ያስተላልፋል።

## ‹‹የሚያዝኑና የሚያለቅሱ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው››

ጻድቁ አባ መብዐጽዮን በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከዘመደ ሳሙ ኤል ዘብሔረ እንዳግብጦ ወገን ከሆኑት ካህን ሀብተ ጽዮን ከእና ታቸው ወለተ ጽዮን ተወለዱ፤ ሁለቱም ጻድቃን ደጋግ የዋሆችና በሕገ እግዚአብሔር የሚጓዙ ነበሩ፤ ነገር ግን ልጅ ስለሌላቸው በጾም፣ በጸሎትና በስግደት አምላካቸው እግ ዚአብሔርን ሲጠይቁ ኖረዋል፤ የለ መኑትን የማይነሳ፣ የነገሩትን የማ ይረሳ፣ የተመረጠ ጻድቅ ልጅ መብ ዐጽዮንን ሰጣቸው፤ ጻድቁ መብ ዐጽዮን እስከ ግብረ ዲቁና ድረስ ያለውን መንፈሳዊ ትምህርት እንደ ጨረሱ ማዕረገ ዲቁና ተቀብለዋል። ከዚያ በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቤት አባታቸው ወስደው አባ ዮሐ ንስ ለሚባሉ መምህር እንዲያስተ ምሩላቸው ሰጧቸው።

ጻድቁ መብዐጽዮን በትምህርት ገበታቸው እያሉ የሚያሳዩት ትሕ ትናና ግብረ ገብነት በሰብአ አድ ያመ እንዳግብጦ ባሉ መነኮሳት ዘንድ ከመወደዳቸው የተነሣ ማኅ በሩና መምህራኑ በስብሰባ ከአሁኑ ጀምሮ ተክለማርያም ይባሉ ብለው ወሰኑ።

ከዚያ በኋላ በመነኮሳቱና በመ ምህራኑ ዘንድ ተክለማርያም ተብ ለው ሲጠሩ በእናት በአባታቸው ዘንድ መብዐጽዮን ሲባሉ እንደኖሩ ገድላቸው ያስረዳል፤ ከዚህ በኋላ እናትና አባታቸው በሕገ ቤተ ክር ስቲያን ተጋብተው እንዲኖሩላቸው ጠየቋቸው፤ ጻድቁ ሲመልሱ «አንሰ ኢይፈቅድ ዘንተ ግብረ ወኢይገብዕ ውስተ ዓለም» እኔ ይህን ኃላፊ ውን ዓለም አልፈልገውም፤ «አንሰ በዓዕኩ ድንግልናዬ ለእግዝእትየ ማርያም ወለእግዚእየ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ» ለጌታዬ ለመድኃኔ ዓለም ክርስቶስና ለእመቤቴ ቅድስት ድን ግል ወላዲተ አምላክ ሰውነቴን ብፅ ዓት ወይም ስዕለት አድርጌ አስረ ክቤአለሁ አሉ።

ከዚህ በኋላ ጻድቁ አባ መብዐ ጽዮን ከእኔ ይልቅ አባቱንና እና ቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባ ውም ያለውን ቃለ ወንጌል በመከ ተል ወደ ምንኩስናውና ወደምና ኔው ተጓዙ፤ እናት አባታቸውም ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም የሚለውን ቃለ ወን ጌል ስለሚያውቁና የጻድቁ መብዐ ጽዮን የምናኔ መንገድ ስላስደሰታ ቸው እግዚአብሔር ምናኔህን ያስ ፈጽምህ ብለው መረቋቸው፤ ጻድቁ መብዐጽዮን መስቀሉን ተሸክሞ በኋ ላዬ የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይ ገባውም ሰውነቱን የወደዳት ይጣ ላት፣ የጣላት ሰውነቱን ያገኛታል ማቴ. ፲ የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ እንዲሁም «ምንት ይበ ቁዖ ለሰብእ ለእመ ኰሎ ዓለመ ረብሖ ወነፍሶ ኀጕለ» ሰው ዓለ ሙን ሁሉ ቢያተርፍ፣ ቢነዳ፣ ቢገዛ ነፍሱን ከአጣ ምን ይጠቅመዋል ምን ይረባዋል፤ ሰውስ ጣዕመ መን ግሥተ ሰማያትን ምሬረ ገሃነመ እሳትን ቢያውቅ ኖሮ ሰውነቱን ለተ ራብ እየሠጠ በኖረ ነበር የሚለ ውን የወንጌል ቃል መሠረት በማ ድረግ ወደ ምናኔው ዓለም ገቡ። ጻድቁ መብዐጽዮን ከላይ የተገለጸ ውን የወንጌልን ቃል በተግባር ለመ ግለጽ መጀመሪያ በአበው ሕግ የምንኩስና ተግባር ተማሩ፤ ከዚህ በኋላ ማዕረገ ምንኩስና ተቀበሉ።



www.ethiopianorthodox.org

በምናኔ በአታቸው ተወስነው ሲጸልዩ መጀመሪያ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያቀረቡት ልመና ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በዕለተ ዓርብ ያገኘህን መከራ መስቀል ገልጸህ አሳየኝ አሉት፤ መጀመሪያ ስለራሴ ፈጽሞ አለቅስ ዘንድ ብለው ጸለዩ ወይም ምልጃ አቀረቡ፤ ያንጊዜ ጌታ መከራ መስቀሌን ማየት ትፈቅዳለህን? ብሎ ጻድቁ መብዐጽዮንን ጠየቃቸው፤ ጻድቁም አዎ አይ ዘንድ እወዳለሁ ሲሉ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ መለሱለት፤ ወዲያውኑ በፊታቸው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዕፀ መስቀል ተተከለ፤ በመስቀሉ ላይም እጅና እግሮቹ ተቸንክረውና ተዘርግተው ታዩ፤ በራሱ ላይም የእሾህ አክሊል ተሸክሞ በዘንግ በደበደቡት ጊዜ በአንገቱ የወረደው የደም ጎርፍ ይታያቸው ነበር።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል መከራ ተቀብዬ ይህንን ዓለም ማዳኤን ገልጬልሃለሁ ለእያንዳንዱ ቅዱስ እየተገለጽሁ የማጽናና እኔ ነኝ ብሎ ወበ ዓለምሰ ሕማመ ትረከቡ ጽንዑ እስመ አነ ሞዕክ ለዓለም በዓለም ካላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌላችኋለሁ፤ ዮሐ.፲፮ ብሎ ለሐዋርያትና ለተከታዮቹ የሰጠውን ቃል ኪዳን ጻድቁ አባ መብዐጽዮን ተቀብለው ገድለ ትሩፋታቸውን ጀመሩ።

፩. ጉንደ መስቀሉን አሸክመው በአንገቱ ገመድ አስገብተው እጁን የኋሊት አስረው ሲጎትቱት ላድናችሁ ብመጣ መከራ የምታበዙብኝ በምንዕዳዬ ነው ብሎ መልስ ሳይሰጥ እንደታገሰ ሁሉ ጻድቁ መብዐጽዮን መከራ መስቀሉን እያሰቡ ሲሰግዱ በጀርባቸው ትልቅ ድንጋይ ተሸክመው ሲነሱ በራሳቸው ሌላ ድንጋይ ተሸክመው ዘወትር ይሰግዱ ነበር።

፪. የዝናብና የምንጭ፣ የባሕርና የውቅያኖሶች ፈጣሪ ሲሆን ውሃ ስጡኝ ቢላቸው መራራ ሐሞትን እንዳጠጡት ጻድቁ መብዐጽዮንም ዐርብ ዐርብ ኮሶ ይጠጡ ነበር።

፫. የጌታ ደቀ መዝሙር ዮሐንስ ወንጌላዊ ሰባ ዘመን ሙሉ ዕንባውን እንደ ሰን ውሃ እያፈሰሰ በኀዘን ቁጽረ ገጽ ሆኖ እንደኖረ ሁሉ ጻድቁ አባ መብዐጽዮን አሥራ ሦስቱን ሕማማተ መስቀል እያሰቡ ስለሚያለቅሱ ሁለት ዐይናቸው ጠፍቶ እንደነበር ገድላቸው ያስረዳል።

ጻድቁ የላመ የጣመ አልቀመሱም፤ በአልጋ ላይ አልተኙም፤ መብዐጽዮን ሲጋፋት ሰዎች በቋንቋቸው ወንጌለ ክርስቶስን እንዳስተማሩ ታውቋል፤ ከዚህ በኋላ ቸሪቱ እማላጅቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ከጻድቁ መብዐጽዮን በዓት የብርሃን ጽዋ ይዛ መጥታ ዐይናቸውን ቀብታ አብርታላቸዋለች።

ስለሥጋውና ደሙ ክብር ሲሉ ብዙ መከራ ተቀብለዋል፤ ስለ ጽዋ ማኅበሩም በየቦታው እንዲስፋፋና በማኅበሩ ምክንያት ብዙ ነዳያን ከረሃባቸው እንዲጠቀሙ አድርገዋል፤ ቸሩ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስም ማኅበሩን ሲሻኘው ተገልጾ ለጻድቁ ታይቷቸዋል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጻድቁ ለአባታችን መብዐጽዮን አዳምን ከነልጆቹ ለማዳን በመልዕልተ መስቀል የተቀበልኩትን ፀዋትወ መከራ በማሰብ ሁለት ዓይኖችህ እስኪጠፉ በማልቀስና ግርፋቱን ለማስታወስ ዘወትር ጀርባህን ስትገርፍ በመኖርህ ለአለመርሁ ታውጽእ እሞደይን ፳ሺህ ነፍሳትን ከሲኦል ወለለ ዕለተ ዓርብ ፫፻፵ ነፍሳተ ታውጽእ ብሎ ከሲኦል ነፍሳትን እንዲያወጡ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በጥቅምት ፳፯ ቀን ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል። የጌታችን የመድኃኒተ ዓለም ክርስቶስን ፀዋትወ መከራ እያሰቡ ንስሐ ገብተው በኃጢአታቸው የሚያለቅሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ብሎ ጌታችን የመሰከረላቸው ለአባታችን ጻድቁ መብዐጽዮን ቃል የገባላቸው በፍጡራን ዘንድ የማይቻል በራሱ በፈጣሪያችን ዘንድ ግን ሁሉንም ማድረግ ስለሚቻለው ይህን የመሰለ ለሰዎች ሁሉ ንስሐ ገብቶ ማልቀስ ምን ያህል ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን እንደሚያወርሰን ከጻድቁ መብዐጽዮን ገድልና ትሩፋት ተረድተናል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ምእመናን ይህን የመሰለ የጌታን ቃል ኪዳን ለመቀበል በጥቅምት ፳፯ ቀን በጻድቁ መብዐጽዮን ስም ምጽዋት በመስጠት ጽዋ ምሉዕ ውሃ በማጠጣት የቸሩ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስን ጸዋትወ መከራ በማሰብ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ያብቃን። በኖኅ ዘመን ሰው ከእግዚአብሔር ተለይቶ ብዙ ኃጢአት በመሥራቱ ይህንን ዓለም በጥፋት ውሃ ደመሰሰ፤ ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንስሳትና አራዊት ሳይቀሩ ጠፍተው ኖኅን ከነልጆቹ ስምንት ነፍስ ብቻና ከእንስሳትና አራዊት ተባዕትና እንስት ሁለት ሁለት በመርከብ ውስጥ አድኖ በዚሁ ጥቅምት ፳፯ ቀን ከመርከብ አውጥቶ ለኖኅ ከነልጆቹ ቃል ኪዳን የገባበት ቀን መሆኑንም አውቀን ጥቅምት ፳፯ ቀን የመድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በዓሉን አክብረን ክብሩን እንዲያጎናጽፈን የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን። ዘፍ.፰+፲፯-፲፱ ✦

ሊቀ ካህናት ተሾመ ወ/ሐና

# ሽሮ ሜዳ የፈውስ ሜዳ

## ‹‹እኔ የምደሰተው አንድ በሽተኛ ከሕመሙ ሲድን ነው››

ዛሬ ዛሬ ሽሮ ሜዳ የፈውስ ሜዳ እየተባለች መጠራት ጀምራለች፤ ሰው ስለ እንጦጦ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ጠበል ብዙ መናገር ጀምሯል። ጠጣት አባት መጥተው ሕዝቡን እየፈወሱ ነው፤ የማይድክሙና የማይሰለቹ አይደሉም አጋንንት ከፊታቸው ለመቆም አይቻላቸውም ወዘተ. እየተባለ ይነገራል።



ሊቀ ካህናት ጌታቸው

እኔም ሊቀ ካህናትን ለማወቅ ጓጓሁ እናም ተአምር ወደሚሠራበት ቤተ ክርስቲያን በማምራት ሊቀ ካህናትን አገኘኋቸው፤ እውነትም ሊቀ ካህናት ጠጣት ሊባሉ የሚችሉ ናቸው፤ ገጽታቸው፣ ተክለ ሰውነታቸው፣ ቁመናቸውና ዕሕማቸው ተዳምሮ ከእግዚአብሔር ሀብተ ፈውስ የተሰጣቸው ለመሆኑ እርግጠኛ ሆንኩ። እናም የሊቀ ካህናትን ገጽታና በውስጣቸው ያለውን ጸጋ እግዚአብሔር በማጤን ላይ እንዳለሁ እኛ ከቆምንበት በስተግራ አቅጣጫ ቢያንስ በአምስት ሜትር ርቀት ላይ ቆማ የነበረች አንዲት ወጣት እየጮኸች ወደ ቀች፤ በወደቀችበት ሆናም መወራጨትና መጮህ ጀመረች፤ ሊቀ ካህናት ምንም አልመሰላቸውም እኔ ግን ደነገጥኩኝ፤ ሊቀ ካህናት ወደ ልጅቱ ተጠጉና በላይዋ ላይ ያደረውን ጋኔን ተነሥ አሉት፤ እሺ ብላ ተነሣችና መጮህ ቀጠለች ዝምበል የምን ጩኸት ነው አሏት ዝም አለች፤ እኔ ፈዝዤ የሚሆነውን እከታተል ነበር፤ ሊቀ ካህናት ቀጠሉና ምንድነህ አንተ አሏት፤ አጋንንትና ቡዳ አለቻቸው እጅህን እሰር አሏት እጆቿን ወደ ኋላ አጣምራ ቆመች፤ በመስቀላቸው ግንባሯን መታመታ አደረጉና ልብ መልስ ብለው ግንባሯ ላይ እፍ እፍ አሉባት ልቧ ተመለሰ፤ አይኖቿ በእንባ ርሰው ነበር ማነው ስምሽ አሏት አስቴር አለቻቸው በይ ነገ ነይና ጠበል ተጠመቂ አሏት እሺ ብላ ሄደች፤ እኔም የሊቀ ካህናትን በጸጋ እግዚአብሔር መሞላት አረጋገጥኩኝ እግረ መንገዴንም አጋንንት ከፊታቸው ሊቆም አይቻላቸውም ሲባል የሰማሁት ሐቅ መሆኑን አረጋገጥኩኝ።

ሊቀ ካህናት ጌታቸው ዶኒ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በምሥራቅ ሸዋ ዞን መቂ ከተማ የተወለዱ ሲሆን ዘመናዊና መንፈሳዊ ትምህርታቸውን በዝዋይ ከተማ እንደተማሩ አጫውተውኛል፤ በዚህም የቀዳማይ ጎርጎርዮስ ልጅ ናቸው ማለት ነው።

ሊቀ ካህናት በምሥራቅ ሸዋ ቆይታቸው የአዳሜ ቱሉ አውራጃ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ፣ የሻሸመኔ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ፣ የአደአሊበን ዝቋላ ሥራ አስኪያጅና የመቂ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በመሆን ሠርተዋል።

ሊቀ ካህናት ጌታቸው ወደ አዲስ አበባ ቢመጡ የበለጠ ሥራ ለመሥራት እንደሚችሉ ስለታመነባቸው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳስ ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት መልካም ፈቃድ ወደ እንጦጦ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተዛውረው እንዲመጡ ተደረገ።

ሊቀ ካህናት ለሥራ የተጉ ስለፈውስ የታደሉ አባት በመሆናቸው እንጦጦ ሥላሴ በመጡ በ፳፮ ቀናት ውስጥ ላለፉት ፰ ዓመታት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያልነበረውና በግለሰቦች ፋክክር የተተበተበውን ደብር በማስተካከል የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ባለቤት በማድረግ የ፴፱ሺ.፻፱፻፸፱ ካሬ ሜትር ሕጋዊ ይዞታ ማረጋገጫ እንዲያገኝ አድርገውታል። ሊቀ ካህናት ይህንን ብቻ ሳይሆን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ የሚገኘውን ቦታ ትምህርት ቤት ለማሠራት ፕላን በማዘጋጀት ፕሮጀክት ለማዘጋጀት (በመቅረፅ) ግራውንዱን ለመኖርያ ክራይ ፎቁን ትምህርት ቤት ለማድረግ በዝግጅት ላይ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም አንድ ትልቅ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ለማሠራት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

በአሁኑ ጊዜ ለሊቀ ካህናት ፈጣን የሥራ እንቅስቃሴ እንቅፋት እንዳይሆን ጊዜያዊ ችግር የነበረው በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ የሚገኘው አዳራሽና የሰንበቴ ቤት ጉዳይ ነው። አዳራሹ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ የሚገኝ ይሁን እንጂ ለቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ለመስጠት ገንዘብ የሚጠይቅ የዕድር ቤት መሆኑ የሚያስገርም ነው። አሁን ግን አዳራሹም ሆነ ሰንበቴ ቤቱ በቤተ ክርስቲያኑ ይዞታ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ በሕግ ስለተረጋገጠና ደብሩም ቦታውን ለልማት ሥራ የሚፈልገው ስለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ የአዳራሹና የሰንበቴ ቤት ባለቤቶች ነን ባዮች ቁልፉን እንዲያስረክቡን በሥላሴ ስም እንለምናለን በማለት ሊቀ ካህናት ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል። በዚህም





www.ethiopianorthodox.org

መሠረት በሊቀ ካህናቱ ጥረት ችግሩ ተፈትቶ ቁልፉን ሲረከቡ መቻላቸውን ይህን ጽሑፍ ካጠናከርን በኋላ ሰምተናል።

እንዲህ ዓይነቱን ፈጣን የልማት ሥራ እያከናወኑ ሕሙማንን መፈወሱ የሚከብድ ሆኖ ተሰማኝ እናም ሊቀ ካህናትን ጠየቅኋቸው ለመሆኑ የማጥመቁ ሥራ የአስተዳደሩን ሥራ አይጋፋብዎትም? አልኳቸው። በመሠረቱ እሱ ሊቀ ካህናት የእኔ ሥራ ሠራተኞችን መቆጣጠርና መንፈሳዊ አገልግሎቱ በአግባቡ እንዲከናወን ማድረግ ነው፤ እኔ የማምነው ግን አንድ አለቃ ትልቁ ሥራው ቀድሶ ማቁረብ፣ የተጎዱና የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት፣ ሕሙማንን መጎብኘትና መፈወስ መሆን አለበት የሚል ጽኑዕ እምነት አለኝ። ይህንን የማይቀበሉ ሊኖሩ ይችላሉ ነገር ግን ጊዜን በአንጉል ቦታ ከማሳለፍ የታመሙ ወገኖችን በመርዳት ማሳለፍ ይሻላል። እኔ ይህንን የፈውስ ሥራ ስጀምር ከማኅበረ ካህናቱ ጋር በመመካከር ነው። በመሆኑም ካህናቱ የሚያደርጉልኝ እገዛ እጅግ የላቀ ስለሆነ የበለጠ ለመሥራት እንድነሣሣ አድርጎኛል።

በመሠረቱ ይህንን የፈውስ ሥራ የጀመርኩት ቤተ ክርስቲያኑ ያለበትን የኢኮኖሚ ችግር በመመልከት ነው፤ ስለሆነም ኢኮኖሚውን ለማሳደግ አንድ ነገር ማድረግ ነበረብን ስለሆነም ከአከባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሣት የፈውስ ሥራውን ጀመርነው፤ ፈውስ ካለ ተጠማቂ አለ፣ ተጠማቂ ካለ የተጠማቂ ቤተሰብና ጠያቂ ይኖራል፤ እነዚህ ካሉ ደግሞ ኢኮኖሚ ያድጋል፤ በዚህ አጋጣሚ ተጠቃሚዋ ቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለችም፤ ምእመናን፣ የአከባቢው ነዋሪዎች፣ ንዋየ ቅድሳት ሻጮች፣ ቤተ ክርስቲያንን እምነት የተጠጉ ነዳያንና የመሳሰሉት ሁሉ ተጠቃሚዎች ናቸው።

በአንዳንድ ጠበል ቤቶች መከበር የሚገባቸው ሕግጋቶች አሉ፤ እነዚህ ሕግጋቶች እዚህ ይሠራሉ ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ሲመልሱ በአብዛኛው ጠበል ቤት ዊግ መቀጠል፣ ጥፍር ቀለም መቀባት፣ ቡና መጠጣት ወዘተ እየተከለከለ እያለሁ፤ እኛ ጋር እንደዚህ ዓይነት ነገር የለም፤ እነዚህ ነገሮች የእግዚአብሔርን ተአምርና የፈውሱን ሥራ የሚሸፍኑ አይደሉም፤ እንዲያውም የበለጠ የማዳኑ ሥራ እንዳይሠራላቸው ሰዎችን ማሸሽ ይሆናል ነው የምለው፤ ስለዚህም ሕሙማንን ለመፈወስ ቅድሚያ መስጠት ይገባል እንጂ ከዚያ በፊት መመዘኛዎችን በማውጣት እንዲህ አታድርጉ እንዲህ አድርጉ ማለቱ ሕሙማኑ ወደ ጠበል እንዳይመጡ ማከላከል ነው የሚሆነው እንደ እኔ እንደ እኔ ጥፍር ቀለም አይደለም ብረት ለብሳ ብትመጣ የእግዚአብሔርን ማዳን ሊከላከል የሚችል ኃይል ይኖራል ብዬ አላምንም፤ ስለሆነም ለሕሙማን ቅድሚያ መስጠት፣ ከዚያ በኋላ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት መስተካከል የሚገባውን ማስተካከል ይገባል ብዬ አምናለሁ። በመሠረቱ አብዛኛው ታማሚዎች የሚታመሙት የመንፈስ ሕመም ነው፤ ስለሆነም ከአለባበስ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም እኛ ልንጨነቅ የሚገባን ለዶግማው ነው፤ ስለዚህ አልባሳትን ከፈውስ ጋር ማገናኘት የለብንም።

ሊቀ ካህናት ሲያጠምቁ በመንፈሳዊ ኃይልና ስሜት ተሞልተው ነው እያንዳንዱን ሕመምተኛ በእኩልነት ያጠምቃሉ፤ ሀብታም ድሀ አይለዩም ለሁሉም እኩል ጊዜ ይሰጣሉ እናም እንዲህ ብዬ ጠየቅኋቸው። ጠበል እጥምቀው ሲጨርሱና ሕመምተኛው ሲፈወስ ሲመለከቱ ምን ይሰማዎታል አልኳቸው። ሊቀ ካህናት በጠበሉ ፈውስ አግኝተው ምስክርነታቸውን የሚሰጡትን ሕሙማን ትኩር ብለው እየተመለከቱ ጨጓራዬን፣ ራሴን፣ ደምግፊት፣ ካንሰር፣ እየተባለ የሚታመሙ ሁሉ በርኩስ መንፈስ የተያዙ ናቸው፤ እናም ተጠምቀው ሲድኑና ለፈጣሪያቸው ሲሰግዱ ስመለከት በጣም እደሰታለሁ፤ ደስታዬን ለመግለጽም አልችልም እኔ የበለጠ የምደሰተው እግዚአብሔር በእኛ በደካሞች በኃጢአተኞች ላይ አድሮ አጋንንት ከበሽተኞች እንዲወጡ በማድረጉና ሕሙማንን በመርዳታችን ነው ብለዋል።

ሊቀ ካህናት ሌሊቱን በአገልግሎት ቀኑን በማጥመቁ ሥራ ተጠምደው ነው የዋሉት ቁርስም ምሳም አልበሉም፤ አሁን ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ሆኗል ገጽታቸው ላይ የድካም መንፈስ አይታይም፣ ወዛቸው ግጥም ብሏል። ዐይኖቻቸው ጠንካሮች ናቸው፣ ጥንካሬ አቸው፣ ጽናታቸው አስደሰተኝ ይልቁንም ደግሞ በኑሮ የተመቻቸው በገቢም ሆነ በሌላ ያልተጎዱ በአጠቃላይ ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው በቂ መተዳደሪያ ያላቸው አባት ግን በጣም ደካማዎች፣ ደሀዎችና በሀገራችን ዝቅተኛ ኑሮ ይኖራሉ ተብለው የሚገመቱ ወገኖች በሚኖሩበት አከባቢ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ አባት በዐይነ ሕሊናዬ የእርሳቸውን ኑሮና የሕሙማኑን ኑሮ ሳስተያይ ጥልቅ የሆነ ሐዘን ተሠማኝ፤ እናም ለሊቀ ካህናት የነበረኝ ክብር ጨመረ በትክክል ለደሀ ወገኖቻችን የቆሙ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ የማይሉ አባት ናቸው አልኩና ለመሆኑ የጠበል አረጫጨቱን ሥነ ሥርዓት እንዴት ነው የምታከናውኑት አልኳቸው።

ጠበል የማጥመቁን ሥራ የምናከናውነው ራሳችንን በማዘጋጀት ጸሎት በማድረስና ሊከናወን የሚገባውን መንፈሳዊ ዝግጅት በማከናወን ነው፤ ጠበል ለመጠመቅ ለሚመጡ ሰዎች ከሌሊቱ ፲፩ ሰዓት ጀምሮ ወንበር ተዘጋጅቶ ይጠብቃቸዋል፤ ሕዝቡ ተሰብስቦ ቦታውን ከያዘ በኋላ በቤተ ክርስቲያችን ሥርዓት መሠረት የእመቤታችን መቅድመ ተአምር፣ ተአምረ ኢየሱስ፣ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድልና ድርሳነ ሚካኤል ይነበባል። ከዚያም ቀሳውስቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ማዕጠንት ያደርጋሉ።

በመቀጠል ዘመናዊ በሆነውና አሥር ሜትር ሊወነጨፍ በሚችለው የጠበል መርጫችን አማካኝነት ሕዝቡ እንደተቀመጠና ልብሱን እንደ ለበሰ ግንባሩ ላይ ብቻ ጠበሉ እንዲነካው ያደርጋል፤ ይህ የሚሆነው ክፉ መንፈስ ሰውን የሚያሳምመው አእምሮውን በመሆኑ በቀጥታ ጠበሉ ግንባሩን ሲነካው በ፩ ሴኮንድ ውስጥ ይጮሃል፤ እንደ ጮኸም በሥላሴ፣ በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት ሲገዘት ውግዝ ይሆናል፣ ሲታዘዝ ይታዘዛል።

ከዚህ በኋላ በቀጥታ ወደ ማስገጃ ቦታ ይወሰድና እንዲሰግድ ይደረጋል፤ ይህ በቀን ሁለት ጊዜ የሚደረግ ሲሆን የቆሰለው አካል ይወጋውና ያቃጥለው የነበረው ቦታ ይተወውና በግንባሩ ላይ ይሰበሰባል። ግንባሩ ላይ ተሰበሰበ ማለት ደግሞ ግንባሩ ላይ ተወግዞ ታሰረ ማለት ነው። ይህ ሲሆን በመስቀል ለመምታት በቅብዐ ሜሮን ለማሸት በመቁጠሪያ ለማሸት ይመቻል ማለት ነው። ይህ ሆነ ማለት አጋንንቱን ለማስለቀቅ የሚወስደውን ጊዜ ያሳጥርዋል፤ ስለሆነም በሽተኛው በጠበል ቤቱ የሚቆየው ከሰባት ቀን ባልበለጠ ይሆናል ማለት ነው። በመቀጠል ግንባሩ ላይ የተሰበሰበውን ወደ አፉ እንዲወርድ በእግዚአብሔር ስም እናወግዘዋለን፤ ከዚያ በኋላ ርኩስ መንፈሱ ልውጣ ልሂድ ብሎ ይለማመጣል። ከዚያም ሰባት ጊዜ ጮሆ በሰባተኛው በሲያል ለዘለዓለም እንዲኖር ተገዝቶ በሽተኞቹን እንዴት እንደጎዳቸው ለሕመምተኞቹ በግልጽ አሳይቶ ከውስጣቸው እንዴት እንደሚወጣ ታይቷቸው ይለያቸዋል። በሽተኞቹም ይህን የታያቸውን ወዲያውኑ ይመሰክራሉ። እኔም በስፍራው በነበርኩበት ጊዜ በርካታ ሕሙማን ቅዱስ ሚካኤልና ሥላሴ ቅዱስ ከሰይጣን መንጋጋ ሲያላቅቋቸውና ሰይጣኑም እልም ወዳለ ገደል ሲጣል ማየታቸውን ነግረውኛል። አብዛኞዎቹ ሕሙማን የዳኑት ከልብ ሕመም፣ ከካንሰር፣ ከጨጓራ የዳኑ ሲሆኑ በርካታዎቹ ከርኩስ መንፈስ የተፈወሱ ናቸው፤ ሕሙማኑም አሁን ያላቸውን ጤንነት በሕክምና አረጋግጠዋል።

ከአረብ፣ ከሱዳን፣ ከሕንድ፣ ከሳውድአረቢያና ከሞስኮብ በመጣ መቱት ተተብትበው ሥራ መሥራት ተስኗቸው ለበርካታ ዓመታት ሲሰቃዩ ከኖሩ በኋላ በእንጦጦ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ መጠመቅ በጀመሩ በሰባተኛው ቀናቸው ከተተበተበበት መተት ተገላግለው ወደ ሥራቸው ተመልሰዋል።



ሊቀ ካሕናት ሕሙማኑን እያጠመቁ።

በእንጦጦ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ጠበል በርካታ ሕሙማን የተፈወሱ ሲሆን ከነዚህ በርካታ ሕሙማን መካከል አቶ አበንጋ አስፋጋ ነዋሪነታቸው በሰባት ቤት ጉራጌ ሲሆን ባለፉት ፳፱ ዓመታት በኩላሊት፣ በጨጓራና በአጋንንት ሕመም ሲጨነቁ ኖረው መጠመቅ በጀመሩ በሰባተኛው ቀናቸው ድነዋል።

ሌላዋ ሕመምተኛ ወ/ሮ ትሰሜ አጋ ሲሆኑ ነዋሪነታቸው በቦሌ ክፍለ ከተማ በቀበሌ ፲፱ መጠለያ ሲሆን በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ድርጅት ውስጥ ይሠራሉ፤ ወ/ሮ ትሰሜ ላለፉት ፲፭ ዓመታት በጨጓራ፣ በልብ ሕመምና በኩላሊት ሲሰቃዩ ኖረው በእንጦጦ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ መጠመቅ በጀመሩት በሰባተኛው ቀናቸው ድነዋል፤ ወ/ሮ ትሰሜ በሰጡኝ አስተያየት ለሊቀ ካህናት ረጅም ዕድሜ መልካም ጤና እንዲሰጣቸው ሥላሴን እለምናለሁ ብለዋል።

ሌላዋ የወረዳ ፯ ነዋሪ የሆነችው ወ/ሪት ሙሉ ነጋሽና ወንድሟ

የወረዳ ፲፱ ቀበሌ ፮ መዝናኛ ሠራተኛ የሆነችው ወ/ሮ አዲስ መኰንን ከባለቤቷ እንዳትስማማ፣ ከሰው ጋር እንዳትስማማ፣ የያዘችው ገንዘብ እንዳይበረክት፣ በመተተኛ የተሠራባት ስትሆን በዚሁ ሳቢያም ጡቷ ሥር የጀመራት እብጠት እየባሰ መጥቶ መቆረጥ እንዳለበት በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ስፔሻሊስቶች የተነገራት ሲሆን ከሁለት ዓመት ስቃይ በኋላ ሥላሴ መጥታ መጠመቅ በጀመረች በሰባት ቀኗ ከተተበተበባት መተትና ጡቷ ሥር ያበጠው እብጠት በጠቅላላ ለቋት ዛሬ ለምስክርነት በቅታለች።

በሥላሴ ጠበል በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አጋንንት የሰፈረባቸው፣ የማኅፀን ካንሰር የያዛቸው፣ የሚጥል በሽታ ያለባቸው፣ የጨጓራ





www.ethiopianorthodox.org

ሕሙማን፣ የመናፈቅ መንፈስ ያደረባቸው፣ በመተተኛ የተተበተበ፣ ትምህርትና ሥራ ያስጠላቸው፣ ከቤተሰብ ጋር ስምምነት የሌላቸው መጠመቅ በጀመሩ በሰባተኛው ቀናቸው ድነዋል።

በሥላሴ ጠበል ሳምንት ሙሉ የተጠመቁ ወገኖች የመጨረሻው የፈውስ ሥነ ሥርዓት የሚከናወንላቸው ዓርብ ቀን ነው፤ ይህ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው ብዬ ሊቀ ካህናትን ጠየኳቸው። ዓርብ ዓርብ ኃይለ አጋንንት ሥልጣኑ የተሻረበት፣ መድኃኒታችን ስለመ ተላለፋችን የቆሰለበት፣ ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ የአጋንንት ቀንበር የሰበረበት፣ ዕለት በመሆኑ ዓርብ ቀን ሕሙማን ይቆዩና መጀመሪያ መታመማቸው የተገለጸላቸው በሙሉ የሚድኑበት ነው፤ በዚህም መሠረት በሱዳን፣ በሕንድ፣ በሳውዲ አረብያ፣ በሞስኮብ መተት የተተበተቡ፣ በጨጓራ፣ በኩላሊት፣ በልብ ሕመም፣ በሚጥል በሽታ፣ በካንሰር፣ በልዩ ልዩ በሽታዎች የተያዙ ሕሙማን በዛሬው ዕለት ማለትም በ፲፩-፩-፲፰ ሙሉ በሙሉ ድነዋል ብለዋል።

ሌላዋ በሥላሴ ጠበል ከመናፍቅ መንፈስ የተፈወሰችውና ምስክርነቷን የሰጠችው ወጣት ብዙነሽ ወልዴ ስትሆን የወረዳ ፲፩ ቀበሌ ፳፫ የቤ.ቁ.ዕሺ.ህ፩፱፯ ነዋሪ ነች። ወጣቷ ከዛሬ ፲ ዓመታት በፊት የኦርቶዶክስ ልጅ ስትሆን ላለፉት ፲ ዓመታት በመናፍቅነት ኖራለች።

ብዙነሽ ከመናፍቅነት የወጣሁት በአሁኑ ጊዜ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በሆኑት በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ ትምህርት ነው ትላለች፤ ሁኔታው እንዲህ ነበር በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት በጉራጌ ዞን አርቅጥ ወረዳ ቤተሰቦቼ ጋር እያለሁ የመናፍቃንን መዝሙር እጥንቼ ስመለስ የአርቅጥ አቦ ቤተ ክርስቲያን ሊሠራ የመሠረት ድንጋይ ይጣል ነበር በወቅቱ እኔ ከመዝሙር ጥናት ስመለስ ብፁዕ አባታችን አቡነ መልከጼዴቅና ከሌሎች አባቶች ጋር በመሠረት ማኖሩ ሥነ ሥርዓት ላይ ያስተምሩ ነበር፤ ብፁዕነታቸውን ቀደም ሲል አውቃቸው ነበር፤ መናፍቅ ከመሆኔ በፊት ማለት ነው እናም በአርቅጥ ሲያስተምሩ ልቤ ተነካ፤ ተጠግቼ አዳመጥኩ በተሣሣተ መንገድ መሄዴንም ተረዳሁ፤ ወደ ብፁዕነታቸው ቀርቤ ታሪኬን ነገርኳቸው፤ እርሳቸውም ባርከው ልጄን ሰይጣን ወስዷት ነበር ብለው ለሕዝቡ ከተናገሩ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት አስፈላጊው ሁሉ ተደረገልኝ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የአርቅጥ አቦ መዘምራን በመሆን ማገልገል ጀመርኩ፤ በዚህም መሠረት ብፁዕነታቸው ባለውለታዬ ናቸው ብላለች።

ታዲያ እዚህ ዛሬ ምን ሆነሽ መጣሽ አልኳት፤ እዚህ የመጣችው አሉ ሊቀ ካህናት ቀበል አድርገው እዚህ የመጣችው ርኩስ መንፈስና የመናፍቅ መንፈስ ስላሰባት ነው፤ ልጅቱ በተጨማሪ ቤተ ቦቿ ላይ የተደረገ ሥራይ በልታ በሆዷ እባብ ሠርቶባታል፤ በእናቷ ላይ ሥራይ ያሠራችውም ቀደም ሲል እናቷን አሳብዷቸው ነበር። እናም እነዚህ ተደማምረው ወደ መናፍቅ ቤት እንድትሄድ ያስገድዷት ነበር፤ አሁን ግን በሆዷ ያለው አውሬው ሆነ የመናፍቅ መንፈስ ተገዝተዋል። ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ በጥሩ ሁኔታ ትገኛለች ብለውኛል።

አዲስ አበባ ከመጣሽ በኋላ ወደ መናፍቃን ሄደሽ ታውቂያለሽ ብዬ ስጠየቅኋት ስትመልስ አዎን ስድስት ኪሎ አሴንብል ሄጄ ነበር ካለች በኋላ በአእምሮዬ ግን ዘወትር ብፁዕ አባታችን ያስተማሩት ትምህርት ያቃጭልብኝ ነበር፤ በውስጤ ያለው የርኩስ መንፈስም እየገፋፋኝ ይውሰደኝ እንጂ ዘወትር ሰላም አልነበረኝምና ትቼአቸው መጣሁ፤ አሁን እየተጠመቅሁ ነኝ ብላኛለች ስለመናፍቃንም መናፍቃን የአጋንንት አምላኪዎች ስለሆኑ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ወይም በተከታዮቻቸው ላይ ርኩስ መንፈስ ይሞላሉ ካለች በኋላ ሁሉም ለኦርቶዶክሳዊት እምነቱ ታማኝና ጸሎተኛ መሆን ይጠበቅበታል በማለት ለብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ መልካም የሥራ ጊዜና ረጅም ዕድሜ ፈጣሪ እንዲሰጣቸው እጸልያለሁ ብላለች።

በሥላሴ ጠበል በርካታ መናፍቃን ለመሰለል መጥተው የቀሩ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በጓደኞቻቸውና በዘመዶቻቸው የመናፍቃን መንፈስ የተሞሉ ተመልክቻለሁ፤ ሥላሴ የሚመጡ መናፍቃን ዘወትር ተጋልጠውና ተዋርደው ይወጣሉ። ብዙነሽ ምስክርነቷን በምትሰጥበት ጊዜ የተበሳጩ ሁለት መናፍቃን ወደ ሥላሴ መጥተው ሊቀ ካህናትን ለመፈታተን ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ያነሡላቸው ቢሆንም ሊቀ ካህናት ካለባቸው ብዙ ሥራ አኳያ መልስ ለመስጠት ስላልቻሉ የመናፍቅ መንፈስ ካደረባቸው ጋር በማገናኘት ይህንን የመናፍቅ መንፈስ በጌታ ኢየሱስ ስም መጣል ትችላለህ በማለት ለፈታኙ መናፍቅ የተግባር ፈተና አቀረቡለት፤ እርሱም ለመጣል እንደሚችል በእርግጠኝነት በመተማመን ወደመናፍቅ መንፈሱ ቀረብ ብሎ በጌታ ኢየሱስ ስም ውደቅ ይለዋል፤ የመናፍቅ መንፈስም ማን ማንን ይጥላል ብሎ አሹፎበታል። መናፍቁ በዚህ ጉዳይ እጅግ የተበሳጨ ቢሆንም እንዳልተበሳጨ ለመምሰል ብዙ ታግሏል። በመቀጠል ሊቀ ካህናት እኔ ግን እንዴት እንደምጥለው አሳይሃለሁ በማለት በቅድስት ሥላሴ ስም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውደቅ ሲሉት ወደቀ፤ መናፍቁም እስቲ እኔን ጣለኝ ብሎ ወደ ሊቀ ካህናት ሲጠጋ እንተማ እኛ ነን የምንጥልህ በማለት የመናፍቅ መንፈሶቹ ተረባርበው ደብድበው አባረውታል። በሚቀጥለው ጊዜ በዚህ ዙሪያ ብዙ ለማለት እሞክራለሁ።

እንግዲህ የሊቀ ካህናት ታሪክ፣ የሥላሴ ማዳን ተጽፎ የማያልቅ፣ ተተርኮ የማያበቃ ይሁን እንጂ ለዛሬው ካለን ጊዜ አኳያ ሳቆም ተገድጃለሁ፤ በሚቀጥለው እትማችን ከማኅበረ ካህናቱ ከሕዝቡና ከሕሙማኑ ያገኘነውን አዳዲስ ተአምር ጨምረን ይዘን እንደምንቀርብ ቃል እየገባን ለዛሬ ሊቀ ካህናት ጌታቸው በሚያስተላልፉት መልእክት እንሰናበታለን።

‹‹አሁን ያለንበት ዘመን መናፍቃንና ኃይለ አጋንንት ብዙ ሥራ የሚሠሩበት ዘመን ስለሆነና መጽሐፍም የሰው ጠላቱ ዘመዱ ነው እን ሚለው ዛሬ የሰውን መሻሻል የማይፈልጉ ሰዎች በቅንዓት ተነሳስተው ኃይለ አጋንንትን ለማቆራኘት የሚጥሩበት ጊዜ በመሆኑ የብዙዎቹ ሕይወት፣ የብዙዎቹ ዕድገትና ኑሮ የሚደናቀፍበት ጊዜ በመሆኑ መሥራት እየቻሉ እንዳይሠሩ፣ መማር እየቻሉ እንዳይማሩ፣ ማደግ እየቻሉ እንዳያድጉ፣ ሥራቸውን እንዲጠሉ የሚያደርጉ ሁሉ በርኩስ መንፈስ የተያዙ መሆናቸውን አውቀው ሽሮ ሜዳም ከእንግዲህ ወዲህ የፈውስ ሜዳ መሆኗን ተረድተው ወደኛ ቢመጡ ሙሉ ጤንነታቸውን አግኝተው መንፈስ ቅዱስ እንዲታጠቁ የሚያደረጉ መሆናቸውን በመረዳት ወደ እንጦጦ መንበረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ መጥተው እንዲጠመቁ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ›› ብለዋል።

እስክንድር ገክርስቶስ

## ቅዱሳን መላእክት

ከገጽ ፴፯ የዞረ

የኤልሳዕ ደቀ መዝሙር ጧት ለተልእኮ ሲወጣ ቤቱ በጦር ተከቦ አየ፤ ወደ ኤልሳዕ ገብቶ ወዮ ቤታችን በነፍሰ ገዳይ ሰዎች ተከቧል አለው፤ ኤልሳዕም እባክህ ዐይነ ልቦናውን አብራለት ብሎ ቢጸልይ የኤልሳዕን ቤት ዙርያና ተራራውን ሁሉ ቅዱሳን መላእክት በእፍራስ እሳት በሠረገላ እሳት ሁነው ሞልተውት ነበር፤ ፪ኛ.ነገ.፮+፳-፲፱ ሦስቱ ወጣቶች አናንያ፤ አዛርያና ሚሳኤል በነደ እሳት በተጣሉ ጊዜ የነደደውን እሳት ያበረደላቸው የእግዚአብሔር መልአክ ነው፤ ዳን፫+፳፰ በባቢሎናውያን መሳፍንትና መኳንንት ተንኮል ነቢዩ ዳንኤል ለአንበሶች የዕለት እራት ሆኖ በጥልቅ ጉድጓድ በተጣለ ጊዜ ዳንኤልን ከአንበሳ አፍ ያዳነ የእግዚአብሔር መልአክ ነው፤ ዳን.፲+፮.

### ቅዱሳን መላእክት ለተግሣጽም ይላካሉ!

ንጉሥ ዳዊት ሕዝበ እስራኤልን በመቁጠሩ ምክንያት እግዚአብሔር ስለተቆጣ ከሕዝበ እስራኤል ሰባ ሺህ የሚያህሉ ሰዎችን የእግዚአብሔር መልአክ ፈጅቷል፤ ዳዊትም በመቅሰፍቱ ምክንያት በዓውደ ኦርና መሥዋዕት በሠዋ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ሕዝበ እስራኤልን ሲገድል ተመልክቶ እኔ ጠባቂያቸው እያለሁ እነዚህ በጎች ምን አደረጉ ብሎ በመጸለዩ መቅሰፍቱ ቁሞአል፤ ፪ኛ ሳሙ.፲፰+፳፭

በንጉሥ በሕዝቅያስ ጸሎትና ልመና የዕብራተኛውን የባቢሎን ንጉሥ የሰናክሬምን አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ሠራዊት በአንድ ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ገድሎ አድሯል፤ ፩ኛ ነገ.፲፱+፴፭ እንዲሁም ንጉሡ ሄሮድስ በሐዋርያት ፊት ለእግዚአብሔር ቃል ክብር ስላአልሰጠ የእግዚአብሔር መልአክ በረቂቅ ሠይፍ መታው፤ በትልም ተበልቶ ሞተ ግብ.ሐዋ.፲፪+፳፫

እንግዲህ ቅዱሳን መላእክት በየጊዜው በሕገ እግዚአብሔር የጸኑ ሰዎችን ከክፉ ነገር ለመጠበቅ፣ ሕገ እግዚአብሔር የሚተላለፉትን ለመቅጣት እንደሚላኩ ከላይ በተገለጸው የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ለመገንዘብና ለመረዳት ይቻላል። በየዓመቱ ኅዳር ፲፪ ቀን የሚከበረውን የቅዱስ ሚካኤል በዐል ሕዝበ እስራኤል ለአራት መቶ ሠላሳ ዘመን ያህል በግብፃውያን የግፍ አገዛዝ ሲረገጡ ከኖሩ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት በቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት ነፃ የወጡበት ቀን ነው፤ ልዑለ ባሕርይ ሕያው አምላክ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ያወጣቸው ዘጠኝ መቅሠፍቶችን ፲ኛ ሞተ በኩር አምጥቶ ግብፃውያንን ከአስጨነቀ በኋላ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልን ልኮ ባሕር ከፍሎ፣ ደመና ጋርዶ ሕዝበ እስራኤልን አድኗል፤ ሕዝበ እስራኤልን ሲያስጨንቁ የኖሩትን ግብፃውያን በባሕረ ኤርትራ ሰጥመው እንዲሞቱ አድርጓል።

እስራኤላውያንም ከግብፅ ከወጡ በኋላ ሰባት ደመናዎች ከእግዚአብሔር ታዝዘውላቸው ነበር፤ ‹‹መርሆሙ መዓልተ በደመና ወኵሉ ሌሊተ በብርሃነ እሳት›› ተብሎ እንደተጻፈው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል በፊታቸው እየሄደ ሰባቱ ደመናዎች በፊት በኋላ በራስ በግርጌ በሌሊት ብርሃን በፀሐይ ዋይታ ጊዜ በማቀዝቀዝ መንገድ በመጥረግ ከጠላት በመሠወር ረድቷቸዋል።

ሕዝበ እስራኤል ለ፵ ዘመን ያህል በምድረ በዳ የጠበቀና የአባቶቻቸውን ምድረ ርስት እንዲወርሱ የረዳቸው ከእግዚአብሔር የተላከው የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው፤ ‹‹ፈነወ መልአኮ ወአድኀኖሙ ሠጠቀ ባሕረ ወአሕለፎሙ›› የአባቶቻቸው አምላክ እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ አዳናቸው፣ ባሕር ሰንጥቆ አሻገራቸው ተብሎ የተጻፈው ስለዚህ ነው ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ሆኖ በመላእክት ላይ የተሾመው ኅዳር ፲፪ ቀን ነው።

የመልአኩ የቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት ከሁላችን አይለይ።





www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱሳን መላእክት



ሰማያውያን ፍጥረታት ቅድሳን መላእክት ረቂቃን ኃያላን ሲሆኑ ዐረፍተ ዘመን የማይወስናቸው፣ የማያረጁ፣ የማይራቡ፣ የማይጠሙ፣ ሕልፈት ሽረት፣ ውላጤ የሌለባቸው ናቸው፤ ቅዱሳን መላእክት በልዑል እግዚአብሔር ዙፋን አጠገብ ሁነው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ያለ ድካምና ያለ ዕረፍት ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይኖራሉ፤ ይህ ጽርዓትና አርምሞ የሌለበት ምስጋናቸው ኃይል፣ ጽንዕ፣ ክብር፣ ሕላዌ፣ ሁኖአቸው ለዘለዓለም ይኖራል።

ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት መዝ.፻፫፥፬ ተብሎ እንደተጻፈው ቅዱሳን መላእክት የተፈጠሩት ከእሳትና ከነፋስ ሲሆን የተፈጠሩበትም ቀን ዕለተ እሑድ ነው። ቅዱሳን መላእክት ደቂቀ አዳምን ለመርዳት ከሰማይ ወደ ምድር እንደሚላኩ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ፤ ዮሐ.፩፥፶፩ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ የነበሩት ቅዱሳን አበው ሁሉ በነበራቸው ጽኑእ አምልኮተ እግዚአብሔርና በጎ ምግባር የአጋንንትን ኃይል ድል ነሥተው ጽድቃቸውን ፈጽመው ለክብር የበቁት በቅዱሳን መላእክት ጠባቂነትና ተራዳኢነት ነው።

በብሉይ ኪዳን ከአዳም እስከ ኖኅ፣ ከኖኅ እስከ አብርሃም፣ ከአብርሃም እስከ ሙሴ፣ ከሙሴ እስከ ዳዊት፣ ከዳዊት እስከ ዘመነ ሐዲስ የነበሩትን ቀደምት አበው መሳፍንትን፣ ነገሥታትን፣ ነቢያትን፣ ካህናትን፣ የረዱአቸውና የታደጉአቸው ቅዱሳን መላእክት ናቸው።

በሐዲስ ኪዳንም ‹‹ኃይሉ ለስም ወፍካሬሁ አብጽሐ ቅዱስ መልአክ እምሰማይ››. ተብሎ በሊቁ እንደተነገረው መልአኩ ኢየሱስ የሚለውን ትርጉሙንና ስሙን ከሰማይ ይዞ መጥቶ ለቅዱስ ዮሴፍ ነግሮታል፤ ማቴ.፩፥፳፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው እንደሚሆን የእግዚአብሔር መልአክ አበሠረ፤ ሉቃ.፩፥፳፰

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜም የጌታችንን ልደት ለእረኞችና ለዓለም የተናገረ የእግዚአብሔር መልአክ ነው፤ ሉቃ.፪፥፰-፲፩ ጌታችን በዚህ ዓለም በመዋዕለ ሥጋዌው ይመላለስ በነበረ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት ያገለግሉት ነበር፤ ማቴ.፬፥፲፩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በተነሣ ጊዜ ለማርያም መግደላዊትና ለዓለም የተናገሩ ቅዱሳን መላእክት ናቸው፤ ሉቃ.፳፬፥፩-፲ በዕርገቱም ጊዜ የጌታችንን ዳግም ምጽአት ለሐዋርያት የተናገሩት ቅዱሳን መላእክት ናቸው፤ ግብ/ሐዋ.፩፥፲ ጌታ ለፍርድ ለ፪ኛ ጊዜ ወደ ዓለም የሚመጣው ከቅዱሳን መላእክት ጋር ነው፤ ማቴ.፳፭፥፴፩

ቅዱሳን ሐዋርያት የክርስቶስን ወንጌለ መንግሥት በመላው ዓለም ለማስተማር በሄዱ ጊዜ ሐዋርያትን የጠበቁና የረዱ መላእክት ናቸው፤ ግብ/ሐዋ.፲፪፥፯-፲፪ ከሐዋርያትም በኋላ አርድዕትን፣ ሊቃውንትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን፣ ገዳማውያን አበው ቅዱሳንንና መምህራንን በጠቅላላ ክርስቲያኖችን ሁሉና ቤተ ክርስቲያንን የሚጠብቁ ቅዱሳን መላእክት ናቸው፤ ማቴ.፲፰፥፲

ቅዱሳን መላእክት ለምሕረትም ለተግሳጽም እንደሚላኩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ።

### ሰውንለመርዳትናለመታደግ፦

አጋር የተባለች ሴት ከእመቤቷ ከሣራ ተጣልታ ልጅዋን እስማኤል ይዛ ከአብርሃም ቤት ወጥታ በስደት በበርሃ ከባድ ችግር ላይ ነበረች፤ በተለይ ልጅዋ እስማኤል በጽኑዕ ውሃ ጥም ተጨንቆ ክፉኛ በአለቀሰ ጊዜ ለአጋር የውሃ ምንጭ ያለበትን የገለጠና አጋርንም ያረጋጋ የእግዚአብሔር መልአክ ነው። ዘፍ.፳፩፥፲፯

ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ ከንግሥቲቱ ከኤልዛቤል ተጣልቶ በነበረ ጊዜ ከእንግዲህ ይበቃኛል ከአባቶች አልበልጥም ነፍሴን ውሰድ ብሎ ነቢዩ እንዲሞት በጸለየ ጊዜ በመሶብ እንጀራ በጽዋ ውሃ ይዞ የመገበውና ያረጋጋው የእግዚአብሔር መልአክ ነው፤ ፩ኛ ነገ.፲፱፥፯

ነቢዩ ኤልሳዕ የእስራኤልን ንጉሥ ከሶርያውያን አደጋ እንዲጠበቅ አስቀድሞ በመንፈስ ትንቢት ይናገራል ነበር፤ የሶርያ ንጉሥም ምሥጢራችን የሚያወጣ ማነው ብሎ በጠየቀ ጊዜ ነቢዩ ኤልሳዕ እንደሆነ ሲነገረው ነቢዩ ኤልሳዕን ለማስገደል ጦረኞችንና ፈረሰኞችን ልኮ የኤልሳዕን ቤት አስከብቦ ነበር።

ወደ ገጽ ፴፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org